*ለምሳሌ፣*

| *ስም* | *የአማርኛ ቀጥተኛ ፍች* |
|---|---|
| ሉደጌ /Ludage/ | እፍታዉን ጠጪ! |
| ሎንሶ /Lonso'o/ | አክባሪ |
| አዋኔ /Awwane/ | ተከተይ! |
| ሎምቦ /Lombo/ | የተከበርሽ |
| ማሶ /Maasso/ | በረከት ነሽ |

## 5.3. *በሉዊሻ፤ የሀዲያ ሴቶች የቋንቋ አጠቃቀም ገጽታ*

በሀዲያ ባህል ያገባች ሴት የተለየ የቋንቋ አጠቃቀም ስርአት አላት፤ በተለይም ለአማቾችዋ ያላትን አክብሮት የምትገልጽበት የተሰየ የስም አጠራር ስርኣት አለ። ይህም በቋንቋዉ *በሉዊሻ* /Balluwwishsha/ የሚል መጠሪያ አለዉ። *በል* /Ball-/ የሚሰዉ ቃል አማች የሚል ፍች ሲኖረዉ፣ *በሉዋ* /Ball-uwwa/ የሚለዉ ደግሞ የአማች የብዙ ቁጥር ወይም አማቾች እንደማለት ነዉ። በሌላ በኩል፣ *በሉዊሻ* (Balluwwishsha) ባለትዳር ሴት ለአማችዋ የምትሰጠዉን አክብሮት ገላጭ ቃል ነዉ፤ ቀጥታ ፍችዉም «አማች የማድ ረግ ሂደት» የሚል አንድምታ አሰዉ። /-ishsha/ የሚለዉ ምእላድ አንድ ነገር እንዲሆን ምክንያት የሆነን ነገር አመልካች ነዉ።

በሀዲያ ባህል፣ ባል ያገባች ሴት ባገባችበት ሰሞን አማቾችዋን የምትጠራበትን ስርአት ያስተምሯታል። በባህሉ የባል አባት፣ እናት፣ አጎት፣ አክስትና የባል ጎሳ ስም እንዳለ ወይም ቅርጹን ሳይቀይር አይጠራም፤ በሌላ ቃል ተተክቶ እንጂ። ከዚህ ስርአት ዉጭ መጥራት ለሴት ልጅ ነዉር ወይም አይነኬ (taboo) ነዉ። *የበሉዊሻ* አስተማሪ ብዙ ጊዜ የባል እህት





ስትሆን የማስተማሩ ስርአት ሲደረግም *ቡሎ* /Bullo/ የተባለን ባህላዊ ምግብ በእጇ ላይ በማስያዝ ነዉ። በዚህ ጊዜ በእጇ ላይ *ቡሎ* አስይዘዋት ቡሎዉ ላይ ቅቤ እያፈሰሱላት የማይጠሩ ቃላትን አስተማሪዋ እየጠራች እንዲህ አይባልም፤ እንዲህ ነዉ የሚባለዉ እያለች፣ ቃላቱን እየዘረዘረች፣ አይጠሬ ምቹን ቃላት የሚጠሩበትን ስልት ታስተምራታለች። ሙሽሪቷ በቀጣይ ህይወትዋም ያንን የተማረችበትን መንገድ ተከትላ አማቾችዋን ብትጠራ፣ አማቾችዋን አክባሪና በጥሩ ሁኔታ ያደገችና ስርአት ያላት እንደሆነች ይነገርላታል።

በአንጻሩ ድንገት ተሳስታ እንኳዋን የአማችዋን ስም ወይም የአማችዋ ስም በሚጠራበት ቃል የመጀመሪያ ፊደል (ፊደላት) ጋር የሚገጥም ሌላ ቃል እንኳዋን ብትጠራ ወዲያው ይቅርታ ካልጠየቀች ከቅጣት አታመልጥም። የምትቀጣበት ምክንያት የባሏን ዘመዶች እንዳዋረደቻቸዉ ስለሚቆጠር ነዉ። ለቅጣቱ የሚሆን በሬ የሚታረደዉ እንኳዋን፣ ከባሏ በመዉሰድ ሳይሆን ከወላጆችዋ በመዉሰድ ነዉ። ነገር ግን፣ አስቀድማ ይቅርታ ከጠየቀች ከቅጣቱ እሚታመልጥበት እድል አለ፤የታላቅ ልጅዋን ስም በማንሳት በእገሌ ጠርቻለዉ ካለች ይቅርታ ይደረግላታል። ለምሳሌ፣ የመጀመሪያ ልጅ ስም ሎምቤቦ ቢሆን በሎምቤቦ ጠርቻለሁ (ሎምቤብኔ ዌሻሞ / Lombeebinne weeshaammo/) ትላለች። በቀጣዩ ክፍል በሀዲያ ባህል ሴቶች የባሎቻቸዉን አማቾች ወይም ዘመዶች የሚጠሩባቸዉን ስልቶች ይመለከቷል።

### ሀ. የበሉዊሻ ቃላት ፈጠራ

በዚህ ስልት፣ ሌሎች የቋንቋ ተጠቃሚዎች ወይም ካገቡ ሴቶች ዉጭ ያሉ የባህሉ አባላት ለሚጠቀሙዋቸዉ ቃላት፣ ያገቡ ሴቶች በቀጥታ ስለማይጠሩ በምትኩ ሌላ ቃል ይፈጥራሉ። በዚህ ስልት የሚፈጠሩት ቃላት ሙሉ በሙሉ

አዲስ ቅርጽ የሚይዙ ይሆናሉ:: ተከታዮቹ ምሳሌዎች ለዚህ እንደ አስረጅ የቀረቡ ናቸዉ::

| የወትሮ ቃል | የበሉዋሽ ቃል | የቃሉ ፍቾ |
|---|---|---|
| አዶ<br>Ado | ሺሻ<br>shiisha | ወተት |
| አዶሬ<br>adore | ሺሻሞ<br>shiishaamo | የሰዉ ስም |
| አድቾ<br>addichcho | ለትቾ<br>latichcho | ጥጃ |
| አንሼ<br>aanshshe | ሙሹቃኤ<br>mushuuqaa'e | እጠብ!/እጠቢ!/ |
| አር<br>ar | ኬስ<br>kes | በግን ማባረሪያ ቃል |
| አጌ<br>age | ቶኬ<br>tokke | ጠጣ! |
| አጌሄ<br>agge'he | ቶኬሄ<br>tokke'he | ጠጡ! |
| አጌቦ<br>aggeebo | ቶኬቦ<br>tokkeebo | የሰዉ ስም |
| አፉሬ<br>afuure | ሜሹሬ<br>meeshshuure | ተቀመጥ! |
| አፉሌሄ<br>afuullehe | ሜሹሌሄ<br>meeshshuullehe | ተቀመጡ! |
| አማ<br>ama | ኦጋ<br>ooga | እናት |
| አጠ<br>axo | ጋንጄ<br>Gaanje | አንገት |
| ቡና<br>buna | ሀርቀጫ<br>harqaca | ቡና |
| በላ<br>balla | ለዋ<br>lawwa | ቀን |
| ገላአ<br>gala'a | አሼዳ<br>ashsheeda | ምጣድ |
| ጌሬ<br>geere | ጤሲሄ<br>xesihe | ሩጥ! |
| ጌሬባ<br>gereebba | ሜቴታ<br>meteeta | በግ |





| የወትሮ ቃል | የበሉዋሽ ቃል | የቃሉ ፍቾ |
|---|---|---|
| ጎና<br>goona | ለባላ<br>labbaala | ወንድ |
| ጎጎ<br>googo | ምራዩ<br>miraayye | መንገድ |
| ጎደቦ<br>godabo | ሶሬኤ<br>sore'e | ሆድ |
| ሀፋ<br>hafa | ገዕና<br>ga'nna | ጥላ |
| ኢበዶ<br>Iibbado | ኢብሺሻ<br>iibshiisha | ትኩስ ወተት |
| እሌ<br>ille | እምብራ<br>imbira | አይን |
| ለሞ<br>lamo | ኪቦ<br>kiibo | ሁለት |
| ለንዳ<br>landa | ጌቤታ<br>gebeetta | ሴት |
| ላጋ<br>laaga caa'mma | ጫዕማ | ጨረር |
| ሎካ<br>lookka | ሱንቾ<br>suuncho | የተለፋ ቆዳ |
| ምቄ<br>miqe | ክና<br>kina | አጥንት |
| ሳያ<br>sayya | ለሮ<br>laro | ላም |
| ኡስማኖ<br>usmaano | ሉጋም እና<br>lugaam anna | ጎላ |
| ዋሳ<br>waasa | ጮቃ<br>cooqqa | ቆጮ |
| ዎኦ<br>wo'o | ዳዳሞ<br>daadaamo, qabaabaa | ዉሀ/ባህርይ/ |
| ቡሮ<br>buuro | ሀንደኖ<br>handano | ቅቤ |

ክፍ ሲል ከቀረቡት የበሉዊሽ ቃላት፣ የአብዛኞቹ አመሰራረት ስርአት ለመገመት አመቺ /predictable/ አይደለም። ነገር ግን አልፎ አልፎ በነገሮች መካከል ያለዉን የባህርይ ተመሳሳይነት መሰረት በማድረግ የበሉዊሽ ቃላት ተፈጥረዉ ማየት ይቻላል። ለምሳሌ፣ ምቄ Miqe /አጥንት/ ለሚለዉ ቃል ክና kina /ድንጋይ/ የሚለዉን ቃል መተካቱ የሁለቱን ቃላት የባህርይ ተመሳሳይነት መሰረት በማድረግ ይመስላል። ምክንያቱም በሁለቱም ቃላት፣ ጥንካሬ የጋራ ባህርያቸዉ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በተመሳሳይ ሁኔታ ዎኦ /wo'o/ (ዉሀ የሚለዉና ዳዳሞ ወይም ዳዳንቾ /daadaamo / daadaancho/ "ፈሳሽ") የሚሉ ቃላት በባህርይ ተመሳሳይ ገጽታ አላቸዉ። በሌላ አነጋገር፣ ዳዳሞ /daadaamo/ የሚለዉ ቃል ያንድን ነገር የፈሳሽነት ባህርይ የሚገልጽ በመሆኑ የዉሃን የፈሳሽነት ባህርይዉን ገላጭ ነዉ። በመሆኑም የወትሮ ወይም የተለምዶ ቃልና የበሉዊሽ ቃሉ በባህርይ መመሳሰላቸዉን መገንዘብ ይቻላል።

በሌላ በኩል ለከምባትኛ ቋንቋ ድንበር በሆኑ አካባቢዎች አጦ/ axo/ አንገት ለሚለዉ ቃል የከምባትኛዉን /genano'o/ የሚል ቃል በተዉሶ ሲጠቀም ከድንበር አባቢ ራቅ ባሉት አባቢዎች ደግሞ ጋንጄ /gaanje/ የሚል ተመሳሳይ ቃል ይጠቀማሉ። ላገ /laaga/ በሚል ቃል ምትክም እንዲሁ ጫዕማ /caa'mma/ የሚል ተቀራራቢ ተመሳሳይ /'near synonym'/ የበሉዊሽ ቃል ሆኖ ጥቅም ላይ ዉሏል። ላገ/laaga/ ዉስን የብርሃን ጨረርን ሲያመለክት፣ ጫዕማ /caa'mma/የሚለዉ ደግሞ አጠቃላይ የሆነዉን የጠዋት ብርሃንን ያመለክታል። ጨረር ዉስን የተባለበትም ምክንያት የብርሃን አንዱ ገጽታ በመሆኑ ነዉ። ክዚህም በተጨማሪ፣ የፍች ስፋትንና ጥበትን መሰረት ያደረገ የበሉዊሽ ቃላትን አመሰራረት ምሳሌን መመልከት ይቻላል። ለምሳሌ፣ ሳያ /saaya/ «ላም» ለማለት ላሮ /laro/ «ከብት» መባሉ ለዉስን እሳቤ አጠቃላይ ወይም ሰፊ ፍች ያለዉ ቃል





ስራ ላይ መዋሉን ማሳያ ነዉ። አንዳንዱ ቃል ለምሳሌ፣ ጌሬ /geere/ «ሩጥ!» ለማለት ጤስሄ /xesihe/ የሚለዉ ጥቅም ላይ መዋሉ ክልጆች የእንቅስቃሴ ወይም የሩጫ ባህርይ የተወሰደ ነዉ ማለት ይቻላል።

ሰ. የነባር ቃላትን ክፊል ድምጾችን /ቀለማትን/[87] በሌሎች ድምጾች መተካት

ይህንን ስልት ተከትለዉ የሚመሰረቱ የበሉዊሽ ቃላት አብዛኛዉን ጊዜ የሚተኩት የመጀመሪያዎቹን ድምጾች ወይም ቀለም ነዉ።

| የወትሮ ቃል | የበሉዊሽ ቃል | የቃሉ ፍች |
|---|---|---|
| አይዳራ aydara | ሺሻራ shishara | ቦርዶ |
| በቁቾ baquchcho | ሱንቁቾ suunquchcho | በቅሎ |
| ቅንጣኣሞ qinxaa'aammo | ቁቡራኣሞ quburaa'aammo | እጥፌእለሁ |
| ቅንጣኤ qinxaa'e | ቁቡራኤ quburaa'e | እጠፍ! |
| አማኔዮሶ amaneey ooso | ኦገኔዮሶ oganeey ooso | የጎሳ ስም |
| ሶምቾ soommichcho | ዌሸንቼኤ weeshanchche'e | የጎሳ ስም |
| ጌሬቾ gereechcho | ሜቴቲቾ meteetichcho | በግ (ነጠላ) |
| ጋድራ gaadira | ኡቻድራ uchchaadira | በረት |

[87] ቀለም፣ የአንድ አናባቢ፣ ወይም የአንድ አናባቢና የተናባቢ(ዎች) ቅንጅት ነዉ (ባዬ 2007፡ 452)። በስነልሳን የተናባቢዎችና የአናባቢዎች ስርአታዊ ቅንጅት/አደራደር/ ከቋንቋ ቋንቋ ይለያል ወይም የራሱ ባህርይ አለዉ። ለምሳሌ፣ /ba/ በሚለዉ የአናባቢና ተናባቢ ቅደም ተከተሉ ተአ የሚል የቀለም መዋቅርን ይዟል። በሌላ በኩል ድምጽ የሚባለዉ አንድ የንግግር ድምጽ ሆኖ ተናጠላዊ ባህርይ ያለዉ ነዉ። ለምሳሌ፣ /b/ የተ ባለችዉ ተናባቢ ድምጽ ስትሆን /a / ደግሞ አናባቢ ድምጽ ነች።

| የወትሮ ቃል | የበሉዊሻ ቃል | የቃሉ ፍች |
|---|---|---|
| ጡማ ገተከአ<br>xumma gattakka'a | ጡማ ትርፋካአ<br>xumma tiriffakka'a | ደህና አደሩ? |
| አፉሬ<br>afuure | ሜሹሬ<br>meeshshuure | ተቀመጥ! |
| በቴቦ<br>bateebo | ካቴቦ<br>kaateebo | የሰዉ ስም[88] |
| ሞቼኤ<br>moochche'e | ጎርብቼኤ<br>gorbichche'e | የጎሳ ስም |
| ወዳሞ<br>wodaamo | ሌዳሞ<br>leedaamo | የሰዉ ስም |
| ወነና<br>wonnanna | ሌነና<br>leennanna | መሬት መደቅደቂያ |
| ወደኖ<br>wodano | ሌደኖ<br>leedano | ልብ |
| ወንግራ<br>wongira | ሌንግራ<br>leengira | መርከብ |
| ወንሾአ<br>wonsho'o | ሌንሾአ<br>leensho'o | የቦርዶ መስሪያ |
| ወጭታ<br>wocita | ሌጭታ<br>leecita | ወጭት |
| ላሞሬ<br>laamoore | ክቦሬ<br>kiiboore | የሰዉ ስም |
| ለቤና<br>labena | ኪቤና<br>kiibena | ጥጃ |
| ላንድቾ | ጌቤትቾ | ሴት (ነጠላ ቁጥር) |
| ሉፊማ<br>lufamma | ክላያማ<br>kilaayyamma | የተበሳ |
| ጎድሶ<br>goddiso | ሶሬዕሶ<br>sore'iso | የሰዉ ስም (ጥጋቡ) |
| ጎዳሞ<br>goddaammo | ሶሬአሞ<br>sore'aammo | ጠግቤአለሁ |
| ሀፎአ<br>hafo'o | ሜፎአ<br>meefo'o | የሰዉ ስም (ጥላዬ፣ የሴት ስም) |

88 የሰዉ ስም ተብለዉ የቀረቡት በቅንፍ ዉስጥ የሴት ስም የሚለዉ እስካልተጨመረበት ድረስ የወንድ ስሞች እንደሆኑ ልብ ይሏል፡፡





| የወትሮ ቃል | የበሉዊሻ ቃል | የቃሉ ፍች |
|---|---|---|
| ሀምፎሬ<br>hamfoore | ሜምፎሬ<br>meemfoore | የሰዉ ስም |
| ሀፋጎ<br>hafaago | ሜፋጎ<br>meefaago | የሰዉ ስም |
| እልጎ<br>illiggo | እምብርጎ<br>imbiriggo | የሰዉ ስም |
| እላንቾ<br>illaancho | እምብራንቾ<br>imbraancho | ወንፊት |
| ድሎአ<br>dilo'o | ትቦአ<br>tibbo'o | የሰዉ ስም (የሴት ስም) |
| ድላሞ<br>dilaamo | ትላሞ<br>tilaamo | የሰዉ ስም |
| ጥላጎ<br>xillaago | ኮላጎ<br>kollaago | የሰዉ ስም |
| ለመራ<br>lamara | ክበራ<br>kibara | ሰባት |

ከፍ ሲል ከቀረቡት መረጃዎች መመልከት እንደሚቻለዉ፣ የመጀመሪያዎቹ ቀለማት ወይም የድምጾች የክትትሎሽ ስርአት በበሉዊሻ አነጋገር ወቅት በሌሎች ቀለማት ተተክተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ አንዲት ያገባች ሴት በቴቦ /bateebo / የሚለዉን ስም ለመጥራት ካቴቦ /kaateebo/ ብላ የምትጠራ ሲሆን በዚህ አዉድ ba- የሚለዉ kaa- በሚለዉ መተካቱን መመልከት ይቻላል፡፡ በቁቾ /baquchcho/ በሚለዉ ቃል ያለዉ የመጀመሪያ ቀለም በ /ba-/ ፣ሱን /suun-/ ሱንቁቾ [suunquchcho ] በሚለዉ ተተክቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍ ሲል በቀረቡት በሌሎችም ቃላት ወይም መረጃዎች ይህንን የመተካካት ስርአት በስፋት ማየት ይቻላል፡፡

በአንጻሩ፣ አንዳንድ ጊዜ ቀለማትን ወይም የመጀመሪያዎቹን ድምጾች ከመተካት አልፎ፣ ቃላትም የሚተኩበት ሁኔታ አለ፡፡

እነዚህ ቃላት ግን በተመሳሳይ ቃላት ከመተካት ዉጭ የመጀመሪያዎቹ ድምጾች ወይም ቀለማት አይደግሙም:: ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ ተከታዮቹን ምሳሌዎች መመልከት ይቻላል::

| የወትሮ ቃል | የበሉዊሻ ቃል | የተተካዉ ቃል | የቃሉ ፍቾ |
|---|---|---|---|
| ሀፋሞ<br>Hafaamo | ገዕናሞ<br>ga'nnaamo | haf- > ga'nn- | የሰዉ ስም(ባላ ጥላ) |
| ላጌቦ<br>laageebo | ጫዕሜቦ<br>caa'mmeebo | laag- > caa'mm- | የሰዉ ስም<br>(ብርሀን አምጪ) |
| ምቆሬ<br>miqoore | ክኖሬ<br>kinoore | miq- > kin- | የሰዉ ስም |

እላይ በቀረበዉ መረጃ፣ ሀፍ /haf-/ የሚለዉ ገዕን /ga'nn-/ በሚለዉ፣ ላግ /laag-/ የሚለዉ ጫዕም /caa'mm-/ በሚለዉ፣ ምቅ /miq-/ የሚለዉ ክን /kin-/ በሚለዉ መተካቱን የሚያስረዳ ነዉ:: በመሆኑም በበሉዊሻ ቃላት ዉስጥ የሚተካኩት ቀለሞች ብቻ ሳይሆኑ ቃላትም እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል::

### ሐ. ዉሰት፤ ከከምባትኛና አማርኛ የተወሰዱ ቃላት

ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ያገቡ ሴቶች በበሉዊሻ ከሚጠቀሙባቸዉ ስትራቴጂዎች በተጨማሪ ዉሰት ሌላኛዉ አይነኬ የሆኑ ቃላትን ዞር አድርገዉ የመጥሪያ ስልታቸዉ ነዉ:: ይህን ስልት በሚመለከት ተከታዮቹን ቃላት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል::





| የወትሮ ቃል | የበሉዊሻ ቃል | የቃሉ ፍቾ |
|---|---|---|
| አጦ<br>axo | ጌነኖአ<br>genano'o | አንገት (ከምባትኛ) |
| ሊረንቻ<br>liiranchcha | በጂጋ<br>bajiga | ደስታ (ከምባትኛ) |
| ጤአኮ<br>xee'aakko | መጥናኮ<br>maxxi'naakko | ጣፍጧል<br>(ከምባትኛ) |
| ጤኣሌ<br>xee'aalle | መጣናሌ<br>maxxi'naalle | ጣፋጭ (ከምባትኛ) |
| ሊረሞ<br>liiramo | በጂጋሞ<br>bajigaamo | የሰዉ ስም<br>(ከምባትኛ) |
| ሎኮ<br>lokko | እግራ<br>igira | እግር (አማርኛ) |
| ገላኣ<br>gala'a | ምጣዳ<br>mixaada | ምጣድ (አማርኛ) |

በእነዚህ የበሉዊሻ ቃላት ከከምባትኛና አማርኛ ወደ ሀዲይሳ የገቡ ቃላት የሚነገሩት ከሀዲይሳ ድምጸ-ልሳናዊ ስርአት ጋር ራሳቸዉን አስማምተዉ ነዉ:: ለምሳሌ፣ አጦ /axo/ ለሚለዉ የሀዲይሳ ቃል የካንባትኛ አንገት ከሚለዉ ቃል ጋር ተቀራራቢ የሆነ ቃል ወይም ጌነኖአ/ ጌነኑ /genano'o < genanu/ የበሉዊሻ ቃል ሆኖ አገልግሏል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ደስታ ሊረንቻ /liiranchcha/ ለሚለዉ ቃል የተሻሻለዉ የከምባትኛ ቃል በጂጋ/ በጂጉታ /bajiga < bajiguta/ ጥቅም ላይ ዉሏል:: በሌላ በኩል፣ እግር /igir/ የሚለዉ የአማርኛ ቃል እግራ /igira/ በሚለዉ ተሻሽሎ ለበሉዊሻ ጥቅም ላይ ሲዉል ፣ ምጣድ /mïxad/ የሚለዉ ደግሞ ምጣዳ /mixaada/ በሚለዉ ቅርጽ ይነገራል:: 'ጣፍጧል' ለማለት የገባዉ መጥናኮ / maxxi'n-aakko/ የሚለዉ ቃል በዉሰቱ ስርአት የተወሰነ ልዩነት አሳይቷል፤ ይኸዉም ጣፋጭ የሚለዉን ቃል ከጨዉ

የጣፋጭነት ባህርይ ወይም ከራስ ከጨዉ መጥ'ን /maxxi'n-/ ላይ በመዉሰድ በሀዲይሳ የድምጽ ስርአት ዉስጥ በመስማማት ነዉ:: በሌላ በኩል /-aakko/ የሚለዉ ተጨማሪ ቅጥያ መሆ'ን'ን (በዚህ አዉድ መጣፈጥ'ን) አመልካች ቅጥያ ነዉ::

በአሁኑ ወቅት የበሉዊሻ ህልዉና (existence) ሲቃኝ በመጥፋት ወይም በመረሳት ላይ ያለ ባህላዊ ገጽታ እንደሆነ አብዛኞቹ አዛዉንት ያወሳሉ:: ለዚህም እንደምክንያት የሚጠቀሰዉ የክርስቲና በተለይም የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መስፋፋት ነዉ:: በእድሜ የገፉ አዛዉንት በተለይም እናቶች ለበሉዊሻ ያላቸዉን አመለካከት ተጠይቀዉ እንደሚከተለዉ ገልጸዋል:: ከተጠያቂዎቹ አንዳንዶቹ ሲመልሱ፣ አንዷ ሴት የአማትዋ'ን (የአማችዋን) ስም ወይም በአማት (በአማች) ስም የሚጀምሩ ቃላትን ብትጠራ በባህሉ ነዉር ነዉ፤ ይህ የሚጠራዉን ሰዉ እንደ ማዋረድ ወይም ማቅለል ይቆጠራል:: በሉዊሻ በተለይ በድሮ የሀዲያ ብሄረሰብ ከምንም በላይ ትልቅ ክብር ያለዉ እንደሆነም ገልጸዋል:: አንዳንድ መላሾች በተ ላይም በእድሜ በጣም ያላረጁ ለበሉዊሻ ያላቸዉን አመለካከት ሲገልጹ ደግሞ፣ በዚያ አይነት ዉስብስብ የቋንቋ አጠቃቀም ከመጨናነቅ ክርስቲና ገላግሎናል በማለት ይገልጻሉ:: አንዳንዶቹ ወጣት ሴቶች ደግሞ በሉዊሻ የሚለዉን ቃል ምንነቱን በጭራሽ እንደማያዉቁ ገልጸዋል:: እንደዚህ አይነቱ አመለካከትና የወጣት ሴቶቹ ስለበሉዊሻ ጨርሶ አለማወቃቸዉ፣ የበሉዊሻ ባህላዊ ገጽታዉ በመጥፋት አፋፍ ላይ ያለ መሆኑን አመላካች ነዉ:: በመሆኑም ይህ ሁኔታ፣ ባህላዊ ገጽታዉ ወይም በሉዊሻ በአፋጣኝ የተስፋፋ መረጃ ወስዶ በማጥናትና በመሰነድ ቀርሶ ማቆየት እንደሚያስፈልግ ጠቋሚ ነዉ::





## 5.4. *በላቻ፤* የግርዛት ስነስርአት አፈጻጸም

በሀዲያ ባህል ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የሚገረዙ ሲሆን፣ የግርዛት አፈጻጸም ስርአት *በላቻ* /Ballachcha/ በመባል ይታወቃል:: ልጆች በሀጻንነታቸው ከተገረዙ እድገታቸው ይዘገያል ተብሎ ስለሚታመን ግርዛቱ የሚፈጸመው በእድሜ ከጠነከሩ በሁዋላ ነው:: በዚህ መሰረት በአብዛኛው ግርዛቱ የሚፈጸመው ከ7-18 አመት መካከል ሲሆን አንዳንዴ በተለይም በድሮ ጊዜ ከዚያ በላይ ሊሄድ ይችላል:: ለግርዛቱ ስነስርአት ከ'ነው'ን አብዛኛውን ጊዜ ተመራጭነት ያለው ወር የመስከረም ወር ነው:: የመስከረም ወር የሚመረጥበት ምክንያት በመስከረም የመስቀል በአል በከፍተኛ ወጪና ድምቀት የሚከበር በመሆኑ ለግርዛቱ የሚወጣዉ'ን ወጪ ለመቆጠብ ታስቦ ነው:: ይህም ተጨማሪ ወጪ ሳይኖር ለበአሉ በሚዘጋጀው ምግብና መጠጥ ተገራዡ'ን (ተገራዥዋ'ን) ለመ'ንከባከብ ያስችላል::

የግርዘቱ ቀን ከመድረሱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ የሰፈር ወጣት ሴቶችና ወንዶች በተገራዡ/ዋ ይጋበዛሉ:: ጋባዥ ወጣት/ቷ ጥሪውን ሲያስተላልፍ ወይም ስታስተላልፍ ከሚዜዉ/ዋ/ ጋር በመሆን ነው:: በእድሜ ተለቅ ያሉ ወይም ያገቡ ወንዶች በአባቶች ይጋበዛሉ:: የተጠሩት ወጣት ወንዶችና ሴቶች በዋዜማው ተገራዡን (ተገራዥዋን) በተለያዩ ደማቅ ጨዋታዎችና ዘፈኖች በማጀብ ያበረታቱዋቸዋል፤ አካባቢውንም ያደምቁታል:: በዋዜማው ለግርዛቱ ዝግጅት እንደ በርዴ በወፍራሙ የተበጠበጠ ሬት ሬት የሚል ክሶ (በሀዲይሳ፣ *ሱጦ* /Suuxo/) ይዘጋጃል:: ይህንን የአበሻ ክሶ ተገራዡ ወንድ ብቻውን አልያም ከሚዜው (*ሳዎ* /Saawwo/) ጋር መጠጣት ይጠበቅበታል:: ተገራዧ ሴት ከሆነች ደግሞ

ኮሶውን በፉክክር መልክ ከሴት ጓደኛዋ ጋር ባንድ ትንፋሽ ይጠጣሉ፡፡ ሚዜዎቹ ኮሶ መጠጣት የሚኖርባቸው ተገራኙዋን ለማበረታታት ሲባል ነው፡፡ ኮሶን መጠጣት ለግርዛቱ ስርአት የግድ[89] ስለሆነ ኮሶዉን የማይደፍሩ ካሉ፣ ኮሶው በገንፎ ተጠቅልሎ ሳያላምጡ እንዲዉጡ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ አይነት የኮሶ አወሳሰድ *ምቴኤ* /mitte'e/ በመባል የሚታወቀው ነው፡፡

ተገራዥ/ዧዋ ኮሶ ሲጠጣ (ስትጠጣ) የስነስርአቱ ታዳሚ ወጣቶች *"ካባል ባቦቶ፣ ካበላ ባቦቶ"* /Kaballa baabootto/ የሚለውን ጨዋታ በድምቀት በዜማ ይጫወታሉ፡፡ የጨዋታው ይዘት፣ በፍጹም እንደትባባ/ቢ፣ በፍጹም እንዳትፈራ/ሪ የሚል ፍች አለው፡፡ እንዲህ ተብሎ የሚዘፈነው፣ በግርዛቱ ጊዜ ተገራገሮቹ ከጮኹ ወላጆቻቸውን ብሎም ራሳቸውን እንደሚያስድቡ ለማስጠንቀቅ ነው፡፡

በሀዲያ ባህል የግርዛት ስነስርአት ውስጥ አክብሮት የሚሰጣቸው የተገራገሮቹ ሚዜ *(ሳዎ* /Saawwo/) እና የአይን አባት *(እል ሰና* /Illi anna/*)* ናቸው፡፡ እነዚህ በግብዣው ቀን በተጋባዥ እንግዶች መካከል የተለየ ቦታ፣ አቀባበል እና ክብር ይቸራቸዋል፡፡ በዚያ እለት ከግብዣው በፊትና በሁዋላ ወጣቶቹ ከበሯቸውን ይዘው ባህላዊ ዜማና ጭፈራ ወይም ውዝዋዜ የሚያቀርቡ ሲሆን፣ ያገቡና ተለቅ ያሉ ወንዶች ሴቶች ግን በዜማ በማጀብ በከዋኔው ይሳተፋሉ፡፡ አብዛኞቹ ወንዶችና ሴቶች ሌሊቱን ሙሉ *ሂቦ (ሂቦንጎ)* ተብሎ የሚታወቀዉን ዘፈን በመጨፈርና በመጫወት ያሳልፋሉ፡፡

[89] ኮሶን መጠጣት የሚያስፈልገዉ ተገራዦች እንደተገረዙ ለመጸዳዳት መዉጣትና መግባት አመቺ ስለማይሆን ለተወሰኑ ቀናት ነጻ ሆነዉ ለመቆየት ሆዳቸዉን አስቀድመዉ ለማጽዳት ተብሎ ነዉ፡፡





የሚቀጥለው ቀን ሲነጋጋ ሲል በመግረዝ የተካነ የልምድ ገራዥ *(ፈል-መንቾ* /Fal-mancho/) ወደ ተገራዡ/ዧ/ ቤት ይመጣል፤ ለፈሩ ሩቅ ከሆነ ደግሞ በግርዘኛው/ዋ/ ቤት በዋዜማው መጥቶ ያድራል፡፡ የግርዛቱ ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ግርዘኛው/ዋ/ በሞቀ ውሃ እንዲታጠብ ወይም እንድትታጠብ ይደረጋል፡፡ ተገራዡ ወንድ ከሆነ በአጭር ወንበር ቁጭ ብሎ ይገረዛል፡፡ ተገራዧዋ ሴት ከሆነች አስቀድሞ ታጭዶ ከተከመረ ሳር ከፍ ያለ መደብ ከመኖሪያ ቤቷ ደጃፍ ይሰራል፡፡ በመደቡ ጐንና ጐን ቋሚ እንጨቶች ይተከላሉ፤ ይህም የሚደረገው ልጅቷ በምትገረዝበት ጊዜ እግሮችዋን በቋሚ እንጨቶቹ መካከል በማስገባት ለግርዛት ራሷን እንድታዘጋጅ ታስቦ ነው፡፡ ይህም ተገራዧዋ በመወራጨት ገራዡን እንዳታስቸግር የሚያግዝ አሰራር ነው፡፡ የግርዛት ሰአት ሲደርስ በመደቡ ዙሪያ መጋረጃ ይወጠርና ልጅቱ በደመቀ ጭብጨባና ጭፈራ ለግርዛት ወደ ተዘጋጀላት ስፍራ ትወጣለች፡፡ መደቡ ላይ እንደወጣች የአይን አባት ከሁዋላዋ ሆኖ አይኗን በጨርቅ ሸፍኖ ይይዛል፤ በዚህ ሁኔታም የግርዛቱ ተግባር ይከናወናል፡፡ የግርዛቱ ተግባር ተጠናቆ ግርዘኛዋን ተሸከመው ወደ ቤት እንዳስገቡ ጎረቤቶች ወደ የቤታቸዉ ይሄዳሉ፡፡ ሚዜ ወደ ቤት ሊመለስ/ ልትመለስ የሚችለው (የምትችለው) ግርዛኛው/ዋ ከሸና (ከሸናች) በሁዋላ ነው፡፡ ከግርዛት በሁዋላ የመጀመሪያ ዙር ሽንት መሸናት ቁስሉ ስለሚጠዘጥዝ ቀላል አይሆንም፡፡ ከዚህ በሁዋላ ለሚዜ ምግብ ይቀርብና በልቶ/ታ ይሄዳል (ትሄዳለች)፡፡

ተገራገሮቹ (ወንዶችም ሆኑ ሴቶች) ለአምስት ቀናት መሬት ላይ በጀርባቸው ከተኙ በሁዋላ፣ በአምስተኛ ቀን ሚዜና የተወሰኑ ሰዎች በመተጋገዝ ከአጠና አልጋ በመስራት በዚያ እንዲተኙ ይደረጋል፡፡ በአልጋ ዙሪያ ከቀርከሀ የተሰራ መጋረጃ

መሳይ ከለላ ወይንም *(ዱማ* /duma/) ይደረጋል። በዚያም ወንድ እና ሴት ጓደኞቻቸው ከጕረቤት የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው በመምጣት ያጫውቷቸዋል።

አብዛኛውን ጊዜ ለወንድ ግርዘኞች በጓደኞቻቸው የሚበረከቱ ስጦታዎች ሳንቲምና መርፌቁልፍ ናቸው። ለሴት ግርዘኞችም እንዲሁ የጣት ቀለበት፣ ሳንቲሞችና ከረሜላዎች ይሰጣቸዋል። የአይን አባት *(እል አና)* ለግርዘኛው የሚሆን ድግስ አዘጋጅቶ የበግ ወይም የፍየል ሙክት ይዞ ወደ ግርዘኛ ቤት በመሄድ ያርዳል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በሀዲያ ባህል ለግርዘኞች ከሚሰጠው ስጦታ አንዱ መርፌቁልፍ ነው። ወንድ ግርዘኞች መንገድ ላይ ሆነው፣ ጅራፍ በመያዝ አላፊ አግዳሚ ወጣት ሴቶችን መርፌቁልፍ ስጡን እያሉ ያስፈራሩዋቸዋል። ሴቶቹ መርፌቁልፍ ካላቸው በመስጠት መርፌ ቁልፍ ካልያዙ ደግሞ ሳንቲም ሰጥተው ከመገረፍ መገላገል ይኖርባቸዋል። ይህን ካላደረጉ ግን በጅራፍ መገረፋቸዉ አይቀሬ ነው። በዚህ ሁኔታ አንዲት ልጅ ብትገረፍ፣ ተገረፍኩ ብላ አትከስም፣ ወይም አትጣላም፣ ምክንያቱም ከግርዛት ጋር ተያይዞ በባህሉ ተቀባይነት ያለው ስርአት ነውና። በመጨረሻም ብዙ መርፌቁልፍ የተሰጠው ወጣት ግርዘኛ ከሌሎች ጓደኞቹ ይልቅ በጣም ተወዳጅ፣ ወይም ተፈላጊ እንደሆነ ይረጋገጣል፤ ብዙ የጣት ቀለበት የተበረከተላት ሴትም እንዲሁ።

ሴት ግርዘኛ *ዱማ* ዉስጥ በምትቀይበት ጊዜ የተለያየ የቤት ቁሳቁሶችን ከስንደዶ (ዊጣ /wiixa/) ትሰፋለች። ከነዚህም፣ *ሌማታ* /leemaata/ (ክብ ጠረጴዛ የሚመስል መመገቢያ/ መሶብ)፣ *ሶሮኦ* /soro'o/ (ክብ ጉድጓድ ሳህን መሳይ/ እርቦ)፣





*ወንሾኦ* /wonsho'o/ (ቁና የሚመስል ሆኖ ከመሀል ወንፊት ያለው የቦርዴ ማጥለያ)፣ ወዘተ. የሚጠቀሱ ናቸው። ከእነዚህ ቁሳቁሶች አብዛኞቹን ለወላጆቿ ቀጥሎም ለሚዜዋ የምታበረክት ሲሆን የተቀሩትን ግን ለራስዋ ገቢ ለማግኘት ትሸጣለች።

በሀዲያ ባህል ለግርዛት የሚመረጠው ወር አብዛኛውን ጊዜ መስከረም ነው። በዚህም ምክንያት ባንድ አካባቢ የሚገረዙ ወጣቶች ቁጥር በርካታ ነው እሚሆነው። የአንድ አካባቢ ግርዘኛ ወንድ እና ሴት ወጣቶች ደግሞ በግርዛት ምክንያት የነበራቸው የቆይታ ጊዜያቸውን መጨረሳቸውን የሚያውጁበት ስርአት አላቸው። በዚህ ጊዜ ባንድ ወቅት የተገረዙ ሴቶችና ወንዶች በአንድ ላይ በመሰብሰብ በስፈራቸዉ ወንድና ሴት ወጣቶች ታጅበው ወደ ገበያ ስፍራ ያመራሉ፡፡ ወደ ገበያ እየተጠጉ ሲመጡ አንድ ላይ ባህላዊ ዘፈናቸውን ይዘፍናሉ፤ ይጨፍራሉ። ወጣቶቹ ወደ ገበያ ከመድረሳቸው አስቀድሞ ግርዘኞቹን የሚቀበሉ ከየቤተሰቦቻቸው የተውጣጡ ሴቶች ገበያ ይደርሳሉ። እነዚህ ወጣቶች ወደ ገበያ እንደደረሱ የገበያውን መሀል በጭፈራ እየሰነጠቁ ያልፋሉ። በዚህ ጊዜ አስቀድመው የተዘጋጁ ሴቶች በገበያ መሀል ሆነው በእልልታ ይቀበሏቸዋል። ከዚያም በግርዘኞቹ ሴቶች በእያንዳንዳቸው እግር ላይም ቦርዴ *(አይዳራ* /aydaara/) ያፈሳሉ። ከዚያ በሁዋላ ሁሉም ሴቶች ከገበያ ከ50-100 ሜትር ያህል ራቅ ብለው ዘፈናቸውንና ውዝዋዜያቸውን ይቀጥላሉ። በጭፈራዉ ሂደት የራሳቸዉን ወገን ጀግኖቻቸዉን እያሞገሱ የአባቶቻቸዉንና የአያቶቻቸዉን ብልጽግና እየዘረዘሩ፤ በአንጻሩ ከወገናቸዉ ያልሆኑትን ደግሞ እያንኳሰሱ ባህላዊ ጨዋታቸዉን ያደምቃሉ። የየወገናቸውን ጨዋታ እንደጨረሱ አንድ ላይ ተቀላቅለው ጭፈራቸውን ይቀጥላሉ።

በሌላ በኩል ወንዶችም መገረዛቸውን ለማሳወቅና የእረፍት ጊዜያቸውን መጨረሳቸውን ለማሳየት የሚያከናውኑት ስርአት አለ:: ከተለያዩ ወገን የመጡ ወንዶች በዚህ አውድ/conext/ የሚጫወቱት ጨዋታ *ገሚሻ* /gammishsha/ በመባል ይታወቃል:: የዚህ ጨዋታ እሳቤዉ "ነጻ ትግል" የሚል አቻ ፍች አለዉ:: የገሚሻ ስርአት የሚፈጸመዉ ጥንድ ጥንድ በመሆን ሲሆን አንዱ ጥንድ ከሌላው ጥንድ ጋር ሊወዳደር ይችላል:: ተወዳዳሪዎቹ መጫወት ያለባቸው ትከሻ ለትከሻ በመያያዝ በጭንቅላትና በእግር ብቻ በመጐናተል ነው::

የገሚሻ አላማው፣ ከጓደኞቻቸው መካከል ይበልጥ ጥሩ የተመገበና ሰውነቱ የተገነባ ማን እንደሆነ መለየት ነው:: በጫዋታው አሸናፊው የሚለየው፣ ከተጨዋቾቹ አቅም ያለው ነቅንቆ በመጣል ወይም ይዞ በመውደቅ ነው:: *በገሚሻ* ድል ወይም ሽንፈት በሴት ጓደኞቻቸውና በተወዳዳሪዎቹ ቤተሰቦች ዘንድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያሰው ነው:: ከዚህ ተውኔታዊ ትእይንት በሁዋላ የተለያዩ ወገን ወጣቶች አንድ ላይ ይሆናሉ:: ከዚያም ወንዶችና ሴቶች በጾታ ወገናቸዉ ተለይተ ዉ ይቆማሉ:: በዚህ ጊዜ በሴቶቹና ወንዶቹ መሃል በዘፈንና *በሸርማ* መልክ ምልልስ ይጀመራል:: በዚህ ጨዋታ አንድ የራሱን ጾታ በማሞገስና ጥንካሬያቸዉን በመዘርዘር ሲያሞካሽ በእንጻሩ ተቃራኒዉን ጾታ በማኮሰስ ግጥማዊ በሆነ መልክ ይጫወታሉ::

እላይ የተጠቀሰው ጨዋታ ስነስርአት የሚከናወነው ከ9:00 - 10:00 ሰአት ሲሆን ሰፈራቸው ከገበያ የሚርቅባቸው ከ11:00 ጀምሮ ወደ የቤታቸው ያመራሉ:: ወጣቶቹ ወደ የቤታቸው እየሄዱ እያሉ ወንዶቹ፣ ሴቶቹ የሚተላለፉበትን መንገድ በመዝጋት እነሱን በጨዋታቸውና በጥንካሬያቸው ለመማረክ





ሲሉ *ገሚሻን* ባለ በሌለ ሀይላቸው ያከናውናሉ:: *በገሚሻ* በሳየው ጥንካሬ ወይም በሰውነት እቋሙ የተማረከች ልጅ ለተማረከችለት ወጣት የሉሻ /Looshsha/ (ጨሌ) ስጦታ ታበረክትለታለች:: አንዳንዴም ይህ ድርጊትና አጋጣሚ ሴቷ ይህን መልክ ቀና ወጣት *በላሌእ ሱንቀንች ቤቶ*[90] /Balale'i Sunqanch Beeto/ (የከንፈር ወዳጅ) እንድታደርግ መነሻ ይሆናል:: እነዚህ ስርአቶች ከተጠናቀቁ በሁዋላ ወጣቶቹ ጸሀይ መጥለቂያ ላይ ወደየቤታቸው ይደርሳሉ:: እነዚህ ግርዘኞች ሁለተኛውን ገበያ *ወይንም ለዕም ሜራ* /la'mm meera/ ከደገሙ በሁዋላ የግርዛቱ ጊዜ ስነስርአት ያበቃል::

ግርዘኛዋ *ለዕም ሜራ* እንደ ደገመች *ባጃም ለንድቾ* /Baajaam Landichcho/ ወይንም የደረሳች ልጅ የሚል ማዕረግ ይሰጣታል:: የልጅቷን በእድሜ መብሰል ለማመልከት ሲባልም የጸጉሯ አሰራር ከአፍሮ *(ሀባ* /Haabba/*)* ወደ *ባጃ* /baaja/ ስልት ይቀየራል:: *ባጃ* የተሰኘው የጸጉር አሰራር መሰያው የሴቷን ጸጉር በመሀል በመከፈል እና መንገድ የሚመስል ክፍተት በመተው የሚገለጽ ነው::

አንዲት ሴት *ባጃ'ም ለንድቾ* ስትሆን ለትጭጭት ብሎም ለትዳር እንደደረሰች ይታመናል:: በሀዲያ ባህል አንዲት ልጅ ሳትገረዝ ወይም ባጃም ለንድቾ ሳትሆን ማግባትም ሆነ ከጋብቻውጭ ግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም የተወገዘ ነው:: ምንም እንኳን ጠሰፋ በባህሉ ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም አንዲት ሴት እንደተገረዘች ወደ ገበያ ወይም ሌላ ቦታ ስትሄድ ለጠለፋ የተጋለጠች ትሆናለች፤ በተለይ ቆንጆ

[90] በአሁኑ ጊዜ በክርስቲና እምነት ተጽዕኖ ምክንያት ወጣቶቹ ከጋብቻ ውጭ መሳሳም ወይም መዳራት የተወገዘ በመሆኑ በእነዚህ አይነት አውዶች አይደረጉም::

ከሆነች። በመሆኑም ወደ ገበያ፣ ወደ ግርዘትና ወደ ሰርግ ስነስርአት ወዘተ. ከዘመዶችዋ ጋር በመሆን ነው የምትሄደው። በእነዚህ ሁኔታዎች ልጅቷ በተለይ ቆንጆ ከሆነች ከተለያዩ ወጣት ወንዶች ጋር ባህላዊ መሳሳም ልትሳሳም ትችላለች። ይህ አይነት አሳሳም በሴቷ ከንፈር ላይ ጠባሳ ጥሎ ሲያልፍ ይችላል፤ ምክንያቱም ወንዱ ሲስማት የታችኛው ከንፈሯ መካከል ላይ በስሱ መቁረጥ ወይም መቀርጠፍ አለበትና። ይህ ባህሉ የተቀበለዉ ስርአት ቢሆንም ቅሉ ጨዋ ወጣት ሴት ከንፈር ዉጫዊ ገጽታ ላይ ጠባሳ መታየት የለበትም፤ ለዚህም ብርቱ ጥንቃቄ ታደርጋለች። በከንፈሯ ላይ ጠባሳ የሚታይባት ማንኛውም ሴት ርካሽ ሴት እንደሆነች ያስቆጥራታል፤ ለቤተሰቦችዋም ማፈሪያ ትሆናለች።

የከንፈር ወዳጆች ስጦታዎችን የሚለዋወጡ ሲሆን፣ ሴቷ ለወዳጅዋ ገበያ ሲገናኙ ሎሚ ወይም ስኳር የምትሰጥ ሲሆን፣ የከንፈር ወዳጅዋም እንደ *ሎሻ* (ጨሌ) ያለ ጌጣጌጥ ወይም ማበጠሪያ ይሰጣታል። በጥቅሉ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በግርዛት ስርአት ካለፉ በሁዋላ በእድሜ መብሰላቸው ስለሚረጋገጥ ለማግባት ቢፈልጉ በባህሉ ይበረታታል። በሚቀጥለው ክፍል ስለትጭጭትና ስለ ጋብቻ ስነስርአት አጠቃላይ ገጽታ ለመቃኘት እንሞክራለን።

## 5.5. *ቦሎቾኦ /Bollochcho'o/*፤ የጋብቻና የሰርግ ስነስርአት አፈጻጸም

### 5.5.1. *ጤሀቀንቻ*፤ትጭጭት

በሀዲያ ባህል መሰረት ተለምዷዊው እና ተቀባይነት ያለው ጋብቻ የሚጠነሰሰው በትጭጭት ስርአት ነው። በሀዲይሳ የትጭጭቱ ስርአት *ጤሀቀንቻ* /Xeehaqqancha/ በመባል ይታወቃል። በባህሉ ትጭጭት (ጤሀቀንቻ) የሚጀመረው





ሴቷ ከተገረዘች በሁዋላ ነው። ሆኖም አልፎ አልፎ የወንድ ልጅ ወላጆች አንዲት ልጅ ቆንጆ ከሆነችና በስርአት ያደገች ከሆነ ብሎም ቤተሰቦችዋ በዚያ አካባቢ የተከበሩ ከሆኑ ያልተገረዘች ኮረዳ ሆናም ልትጠየቅ ትችላለች። ይህ የሚደረገው ጠያቂዎቿ ልጅቷ እስከምትገረዝ ከጠበቁ በሌሎች ልጅቿን በሚፈልጉ ሰዎች ሊቀደሙ እንደሚችሉ በማሰባቸው ነው። በዚህ ጊዜ የልጅቷ ወላጆች፣ ገና ለጋ የሆነችውንና ያልተገረዘችውን ልጃችንን (ገና ህጻን ናት ማለታቸው ነው) እንዴት ለትዳር ልትጠይቁ ደፈራችሁ? የሚል ምላሽ መስጠታቸው የተለመደ ነው።

ከፍ ሲል የተጠቀሰዉን አስተሳሰብ አስመልክቶ በሀዲያ ህዝብ ዘንድ ሲነገር የነበረውን አባባል እናንሳ። አንድ ጊዜ ልጃችሁን ለልጃችን ስጡን በማለት ወደ አንድ ቤተሰብ ለሄዱ ጠያቂዎች ወይም ሽማግሌዎች የልጅቷ ወላጆች፣ ልጃቸውን ገና ለጋ ወይም ለትዳር ያልደረሰች ስለሆነ ጥያቄያችሁን እናስተናግድም ብለው ምላሽ ይሰጣሉ። በዚህ ጊዜ ልጅቱ በወላጆችዋ ምላሽ ብዙም ደስተኛ አልነበረችም፤ ቢሆንም ጠያቂዎቿ ወደ የቤታቸው ተሸኝተዋል። ልጅቱ ፍላጎቷን ፊት ለፊት መግለጽ ስላልቻለች ነገሩን እያብሰለሰለች እያለ ከጓሮ ጐመን ሰብስባ በማምጣት በትንሽ የጐመን መቀቀያ ምንቸት፣ ከምንቸቷ አቅም በላይ ትጠቀጥቃለች። ይህንን ያዩ አባቷ "ምነው ልጄ ይሄን ሁሉ ጐመን በዚች ትንሽ ምንቸት ከአቅሟ በላይ እንዴት ትጨምሪያለሽ" ብለው ሲጠይቋት ልጅቷም፣ "አባዬ የሴት ልጅና የምንቸት ትንሽ የለም" ስትል መለሰች ይባላል። ይህ አባባል የሚያሳየው ብዙ ጊዜ ወጣት ሴቶች ማግባት ቢፈልጉም ወላጆች ሴት ልጆቻቸው ሃላፊነትን ለመሸከም ገና እንዳልደረሱ አድርገው እንደሚያስቡ ነው።

ልጃቸዉ ገና እንደሆነች የሚናገሩ ወላጆች ለጠያቂዎችዋ፣ ልጃቸው ከተገረዘች በሁዋላ ወይም የትዳር ሀላፊነትን ለመሸከም ስትበቃ፣ ሌላ ጊዜ መጥተው መጐብኘት እንደሚችሉ ይነገራቸዋል። ምክንያቱም በሀዲያ አንዲት ልጅ ለትዳር የምትጠየቅበት ትክክለኛ ጊዜ ባጃም ለንድቾ (የደረሰች ልጅ) ስትሆን ነው። ይህንን ደረጃ የምታገኘው ደግሞ በምትገረዝበት ጊዜ እንደሆነ ግርዛት *(በለቻ)* በሚለው ክፍል ተጠቅሷል።

ለትዳር የደረሰ ወጣት የትዳር ጓደኛ የምትሆንን ልጅ፣ በተለይ በቀድሞ ጊዜ የሚያጫት አብዛኛውን ጊዜ በቅርብ ሴት ዘመዶቹ ማለትም በእህት ወይም በአክስት አማካይነት ነው። በዚህ ሁኔታ የሚወዳትን ልጅ ካገኘ በሁዋላ በአጐቱ ወይም በሌሎች ዘመዶቹ አማካይነት ለአባቱ፣ ለትዳር የምትሆን ልጅ እንዳገኘ ይገልጻል። ወላጅ አባቱም ለልጅቷ ቤተሰብ ሽማግሌ ከመላኩም በፊት ልጅቷ የማን ወገን እንደሆነች ማጣራት ይጀምራል። አባት እንደዚህ አይነቱን ማጣራት የሚያደርገውም በሁለቱ ወገኖች መካከል ጋብቻ የሚከለክል ዝምድና መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ሲል ነው። አንዳንድ ጊዜ ዝምድና እንኳን ባይኖር በአንዳንድ ጐሳዎች መካከል ጋብቻ የማይፈቀድበት ሁኔታ አለ። ይህን ሁኔታ አስመልክቶ ተስፋዬ (1993፡ 469) በሌሞና በኮንተብ (በአሁኗ ምሻና ግቤ) አካባቢዎች "አሪይአና ሄገንአና" የሚባል እገዳ እንዳለ ያወሳል። በሌላ አነጋገር፣ የአሪይአና ጐሳ ተወላጅ የሆነ ማንኛውም ሰው የሄገንአናን ጐሳ ተወላጅ ማግባት በባህሉ የታገደ እንደሆነ ይጠቁማል። የእገዳውን መንስኤ ተስፋዬ በተከታዩ መንገድ ገልጾታል።





> *... እገዳው የተደረገዉ ሁለቱ ጐሳዎች ቀድሞ በጣም ጥለኞች ስለነበሩና በዚህም ጠብ መንስኤ የብዙ ሰዎች ህይወት ከሁለቱም ወገኖች በኩል በመጥፋቱ ከጊዜ በኋላ በአካባቢው የሚኖሩት ሌሎች ጐሳዎች ተጠሪዎች በሸንጐ ተሰብስበው ባደረጉት የእርቀ መሀላ ቃልኪዳን ምክንያት እንደ ጠላት መተያየታቸውን እርግፍ አድርገው በመተው ከአንድ አባትና እናት እንደተወለዱ ወንድማማቾች እንዲከባበሩና በማንኛውም ነገር እንዳይተሳለፉ በቃለ መሐላ[91] ስላገዱዋቸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጋብቻም ሆነ በሌላ ነገር አይተሳለፉም።*

ከፍ ሲል የተገለጸው የትዳር ጓደኛ ፍለጋ ስልት ለአቅመ አዳም በደረሰ ወንድ ልጅ የሚከናወን ሲሆን፣ በሌላ በኩል አንድ አባት ለልጁ ትዳር የምትሆንን ልጅ ማፈላለጉና ማጥናቱ የተለመደ ስልት ነው። ለልጅ ሚስት ፍለጋ በአባት በኩል የሚከናወን ከሆነ፣ አባት አንዲትን ልጅ አስጠንቶ፣ ለልጁ እንደምትሆን ካሰበ ልጁ ያችን ልጅ ቀርቦ እንዲያያት ይጠቁማል። አባት በልጁ በኩል ማረጋገጫ ካላገኘ ወደ ወላጆችዋ ሽማግሌ አይልክም። ልጁም ለትዳር ሃላፊነት መድረሱ ከተሰማውና በተጠቆመችው ልጅ ውበት ከተማረከ በአባቱ በቀረበው ሀሳብ ላይ መስማማቱን ይገልጻል።

አንዳንድ ጊዜ ወንዱ ልጅ ያላያት ልጅ እንኳን ብትሆን ስለአካላዊ አቋሟና መልኳ፣ ስለአድሜዋ፣ ስለቤተሰቦችዋ ሁኔታ (ሀብት፣ ተሰሚነት፣ የዘር ሀረግ) ገለጻ በዘመዶቹ አማካይነት ይሰጠዋል። ልጅቱን እስኪያያት ድረስ በተነገሩት የልጅቷ ሁኔታዎች (ዳራዎች/background/) የተወሰነ የመዉደድ ዝንባሌ ሊያሳይ ይችላል። ልጅ አምንታዊ

[91] የዚህን ሀሳብ ተጨማሪ ማብራሪያ ህድሮ በሚለዉ ክፍል ይመለከቷል።

ዝንባሌ ሲያሳይ ወይም ሲወዳት አባቱ የልጅቷን አባት ከሽማግሌዎች ጋር ቀርቦ ለማነጋገር የሚችልበት ቀጠሮ አስቀደሞ ይይዛል። ከዚያም የልጅቷ አባትና እናት ብሎም ቤተሰቦችዋ ከተስማሙ ከ1-2 ሳምንት ባለ ጊዜ ዉስጥ ቀጠሮ ይይዛሉ። በዚህ ጊዜ ልጅቷ ጠያቂዋን የምታዉቅ ከሆነ ስለወደፊት ባል ተከለሰውነት፣ መልክና እድሜ እና ስለቤተሰቦቹ ሁኔታ መረጃ ይሰጣታል ወይም ገለጻ ይደረግላታል። ልጅቷም ሲያገባት የሚፈልጋትን ወጣት ማንነቱን ለማወቅ የቀጠሮ እለት ከመድረሱ በፊት የተለያዩ ዘዴዎችን ትጠቀማለች። የልጅቷ እናትም በበኩሏ ለለወደፊቱ የልጇ ባል ሲሆን ስለሚችል ሰው የተለያዩ መረጃዎችን ከምታውቃቸው ሰዎች ሁሉ ትሰበስባለች። በቀጠሮው እለትም የልጅቷ አባት ጥያቄውን ሲቀበል ወይም ሲሰርዝ አልያም ውሳኔውን ሲያዘገይ ይችላል። የተጠያቂዋ ልጅ አባት ዉሳኔዉን የሚያዘገየዉ የሚፈልገዉን ያህል አጥጋቢ መረጃ ሳያገኝ ሲቀር ነዉ።

በተቀጠረው እለት የልጅቷ አባት፣ ከሚስቱ፣ ከልጅቷ አጐቶች እና ከመንደሩ ሽማግሌዎቹ ጋር ሆኖ የእንግዶችን መምጣት ይጠባበቃል። ወንዶቹ ከወለሉ የፊት ለፊት በኩል (በሀዲይሳ *ገጣ* /Gaxa/) የሚቀመጡ ሲሆን፣ እናት በበኩሏ ከወንዶቹ ራቅ በማለት በጓዳ (*ኮሻ* /Kosha/) በሴት ጓደኞችዋ ታጅባ ትቀመጣለች።

የትዳር ጓደኛ ፈላጊ ልጅ አባት ከነገር አዋቂና በአካባቢው ተሰሚነት ካላቸው ሽማግሌዎች ጋር ታጅቦ ወደተጠያቂዋ ልጅ መንደር ሲቀርብ፣ ከልጅትዋ ቤተሰብ ጐረቤት የሆነን አንድ ወጣት ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች በመላክ እንግዶች ወደቤታቸው እየተቃረቡ እንዳሉና ለመግባት የቤተሰቦችዋን





ፈቃድ እንደሚጠባበቁ እንዲነግራቸዉ ይጠይቃሉ። ወላጆቹ ይህን መልእክት ከተቀበሉ በኋላ መልእክት አድራሹን እንግዶቹ ወደ ቤታቸው መዝለቅ የሚችሉ መሆኑን እንዲነግራቸው ይነግሩታል። እንግዶቹም ወደግቢው በመዝለቅ ወደቤት ከመግባታቸው አስቀድሞ (ከ10-20 ሜትር ሲቀራቸው) በራፍ ላይ ይቆማሉ። እንግዶቹ እደጅ የሚቆሙት የልጅቱን ቤተሰብ ፍቃድ ለመጠበቅ ሲሉ ነው። በቤተሰብ አስተናጋጅ አማካይነት ወደ ቤት እንዲገቡ ተደርጐ ለነሱ በተዘጋጀላቸው ስፍራ እንዲቀመጡ ይጋበዛሉ። እንደተቀመጡ ለተወሰነ ደቂቃዎች የአርምሞ (ዝምታ) ድባብ በቤቱ ይነግሳል። ከዚያ ዝምታ በሁዋላ ምንም እንኳን ሰዎቹ ለምን እንደመጡ የሚታወቅ ቢሆንም እንግዶቹ የመጡበት ጉዳይ ይጠየቃል። ከእንግዶቹ መካከል አንድ የነገር አዋቂ ሽማግሌ ጉዳዩን እንዲያቀርብ አስቀድሞ የሚነገረው በመሆኑ በሽማግሌዎቹ መካከል ጉዳዩን ለማቅረብ መጠባበቅ አይኖርም።

የነገር አዋቂው ሽማግሌ ጉዳዩን ሲያቀርብ ልጃቸውን ለልጃቸው እንዲሰጡ መፈለጋቸውን ፊት ለፊት ሳይሆን የሚገልጠው የነገሩን ዳር ዳር በሚነካካ አነጋገር ነው። ይህ አነጋገር በቋንቋው *ቦያንሳ* /Booyyaansa/ ተብሎ ይታወቃል። የተቃራኒ ወገን ምላሽም እንዲሁ በተመሳሳይ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት፣ *በቦያንሳ* ነው የሚሆነው። በዚህ ሁኔታ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ምልልስ ከተደረገ በሁዋላ ጉዳዩን ፊት ለፊት በማምጣት የልጅቷ ቤተሰብ ፈቃደኝነት ይጠየቃል። ለጥያቄው የልጅቷ አባት ምላሽ ቁርጥ ያለ አሽታን የሚገልጽ አይሆንም፤ የልጁን መልካም ፈቃድ ወይም አመለካከት ሳይረዳ የቀረበውን የጋብቻ ጥያቄ እንደማያጸድቅ ይገልጻል። ይህ ተለምዷዊ አባባል የሚነገረው አንድም

ልጅቷ በቀላሉ የምትገኝ ወይም ርካሽ ተደርጋ እንዳትቆጠር ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቤተሰብ አባላቱ ስምምነት መረጋገጥ ስላለበት ነው። በመሆኑም አባት ለእንግዶቹ ጥያቄ የእሽታ ሆነ የእምቢታ ምላሽ ከመስጠት ተቆጥቦ ሌላ ቀጠሮ እንዲያዝ ሀሳቡን ያቀርባል። ይህም በተለምዶ ከ2-4 ሳምንታት ባለዉ ጊዜ ውስጥ የሚሆን ነው። ከዚያም እንግዶቹ በተዘጋጀዉ ምግብና መጠጥ ከተስተናገዱ በሁዋላ ቀጠሮዉን በመቀበል ወደየቤቸዉ ይመለሳሉ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የልጅቷ ቤተሰብ በሙሉ ስለልጁ እና ስለልጁ ቤተሰብ አጥጋቢ መረጃ እስኪያገኙ በየፊናው የተለያዩ ምስክርነቶችን መሰብሰባቸዉን ይቀጥላሉ።

በቀጠሮው እለት የልጅቱ ቤተሰቦች እንግዶችን እንደገና በመቀበል የሁለቱ ወገን በጋብቻ መተሳሰር መልካም መሆኑ ከታመነበት ሁለቱ ቤተሰቦች በልጆቻቸው ጋብቻ የሚዛመዱ ወይም የሚተሳሰሩ መሆኑን ይገልጻሉ። ከዚያ በሁዋላ የጥሎሽ ወይንም *(ቆታ* /qoota/*ወይም ገበራ* /gabara/*)* አይነት ምን መሆን እንዳለበት በመነጋገር ይወስናሉ። በቆታ/ በገበራ አይነት እንዳተስማሙ ሌላ ቀጠሮ ይይዛሉ። የዚህ ጊዜ ቀጠሮ በተለምዶ ከሁለት ወር በሁዋላ ሲሆን የቀጠሮው አላማ ጥሎሽን ለማበርከትና ለቃል ማሰሪያ ስነስርአት *(ጉመእ*[92] *ገና ወይም ጧር ገና* /Guma'a gana/ Xaar gana/*)* ለመፈጸም ሲባል ነው። የልጅቷ ቤተሰብ ለቀጠሮው እለት ሰንጋ በማረድ አስፈላጊዉን ምግብና መጠጥ አሰናድቶ ይጠባበቃል። ይህ እለት የወደፊቱ ሙሽራና ሙሽሪት ፊት ለፊት የሚተያዩበት ቀን ነው፤ ለአጭር ጊዜም ቢሆን።

[92] *ጉመዓ* የሚለዉ ቃል ቀለበት ማለት ሲሆን *ጧራ* ሲባል ቀጥተኛ ፍችው «ብረት»ማለት ነው፤ ይህም ቃል ቀለበትን አመልካች ነዉ። *ጉማዕ-ገና (ጧር-ገና)*፣ ልጅቱ መታጨትዋን የሚያሳይ ምልክት በጣትዋ ማጥለቅዋን የሚያመለክት ቃል ነዉ። ያንን ምልክት በጇ ያየ ሁሉ ያችን ልጅ ለጋብቻ ሊጠይቃት አይችልም፤ የመታጨቷ ምልክት ነውና።





ለትጭጭቱ መገለጫ ስጦታዎች፤ ማለትም የጣት ቀለበት፣ የጆሮ ጌጥና ሌሎች ጌጣጌጦች በሙሽራው ይበረከታል። በሌላ በኩል የሙሽራውን ስጦታ ተከትሎ የሙሽራው አባት ጥሎሽ *(ቆታ/ገበራ)* በጥሬ ገንዘብና በአይነት (ለምሳሌ፣ የአልባሳት ስጦታ) ይከፍላል። ከዚያም የተዘጋጀዉ ምግብ ለእንግዶቹ ቀርቦ መስተንግዶዉ ይጀመራል። መስተንግዶው ሲገባደድ የትጭጭቱ ስርአትም በዚያው ማሳረጊያ ያገኛል።

የእጮኛዉ አባት የትጭጭቱ ስርአት ካለፈ ከአንድ ወይም ከሁለት ወር በኋላ ከጥቂት ወዳጆቹ ጋር የሰርጉን ቀን ወይንም *ለዲሽ በላ* /Ladiishsh balla/ ለመወሰን ይሄዳል። ወደዚያ እንደደረሱም የልጅቷ አባት ከባለቤቱ ጋር ከተማከረ በሁዋላ የሰርጉን ቀን ለእንግዶቹ ይነግራቸዋል። ይህም አብዛኛውን ጊዜ በሁለት ወራት ልዩነት የሚከናወን ይሆናል። ከዚህ በመቀጠል በሀዲያ ህዝብ ባህል የሚታዩ የጋብቻ አይነቶች ወይም ጋብቻ የሚፈጸምባቸዉን መንገዶች እንመለከታለን።

## 5.5.2. የጋብቻ አይነቶች

በሀዲያ ባህል ለአቅመ-አዳምና ለአቅመ-ሄዋን የደረሱ ወጣቶች ወደ ትዳር ህይወት የሚገቡባቸው የተለያዩ በሮች አሏቸው። አብዛኛዎቹ የትዳር በሮች በህዝቡ ወይም በባህሉ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሲሆኑ አንዳንዱ ተቀባይነት ያለው (ህጋዊ) በር አይደለም። እነዚህን ወደ ጋብቻ መግቢያ በሮች በሚከተለው መንገድ መቃኘት ይቻላል።

### 5.5.2.1. *ጐሰኖ፤ ጠለፋ*

*ጐሰኖ*/Gosano/፣ አንዲት ሴት የራሷ አልያም የቤተሰቦቿ ፈቃድ ሳይኖር በግድ የምታገባበት የጋብቻ አይነት ሲሆን በባህሉ

ተቀባይነት ያለው የጋብቻ አይነት አይደለም። በሌላ አነጋገር፣ ሴት ልጅ ራሷ ወይም ቤተሰቦችዋ የልጅቱን ፈላጊ በድህነት፣ በዘር "እናሳነት"፣ በመልክ አስቀያሚነት አልያም ሌላ የተሻለ ጠያቂ በማግኘት እምቢ ማለትዋን ካስተዋለ ጠለፋው ሊከሰት ይችላል። *ጉሰኖ* ብዙ ጊዜ የሚከናወነው፣ ልጅቱ ወደ ገበያ ስትሄድ፣ ስንደዶ *(ምግራ* /Migira/) ለቀማ ላይ እያለች፣ ውሃ ልትቀዳ ወንዝ በወረደችበት አልያም የማገዶ እንጨት ለቀማ ጫካ በሄደችበት ነው። አብዛኛውን ጊዜ በጠለፋ የተወሰደችው ሴት በአግቢዋ (በጠላፊዋ) ቤት አትቀመጥም፤ ለጊዜዉ በጠላፊው ዘመድ ቤት ያኖሯታል። በዚህ መሀል ጠላፊው፣ የልጅቷ ቤተሰብ ልጃቸው የት እንዳለች ባለማወቅ በስጋት ውስጥ እንዳይሆኑና በቀጣይ የእርቁን ርምጃ ለመውሰድ ሲል አንድ ወሬ ነጋሪ ሰው ይላካል። ለዚህም አንድ ብርቱ ሰው ተፈልጎ ጠንካራ ፈረስ ተሰጥቶት ልጅቱ በእነርሱ እጅ እንዳለች ነግሯቸው ጉዳት እንዳይደርስበት አፈትልኮ ይሄዳል ወይም ያመልጣል። ከዚያም በጥቂት ቀናት ሽማግሌዎች ለእርቅ ማር /Marabo/ እና ሳር /Sadda/ ይዘው በመሄድ ምስሶ ስር ካስቀመጡ በሁዋላ ምሰሶዉን በመያዝ ሽምግልና እንዲይዙ ይማጸናሉ። ሽማግሌዎች በባህሉ ከፍተኛ ቦታ ስላላቸዉ ፈቃደኛ መሆናቸውን በመግለጽ ለእርቅ ቀጠሮ ይዘው ይታረቃሉ። ከዚያም ዝምድናቸው ይቀጥላል። ከዚህ በሁዋላ ጠለፊው በቤቱ ድግስ አዘጋጅቶ ዘመድ ቤት ብዙ ሳትቆይ ወደራሱ ቤት በመውሰድ ትዳራቸውን ይቀጥላሉ።

### 5.5.2.2. *ሄረንቻ*

*ሄረንቻ*/Heerancha/ ፣ በትዳር ጓደኛ ምርጫ የሴቷ ቤተሰብ ሳይስማሙ ሲቀርና ልጅቱም በበኩሏ የወደደችውን ልጅ ለማግባት ስትፈልግ ከነሱ ተደብቃ የምታገባበት የጋብቻ አይነት ነው። አንዳንድ ጊዜ አንዲት ልጅ ወላጅ አባት





ወይም እናት ከሌላት ወይም በቤቱ ለድግስ የሚሆን ገንዘብ ሲታጣ *ሄረንቻ* ሲመረጥ ይችላል። በሰርግ ድግስ መጋባት እንደማይችሉ ተጣማሪዎቹ ሲያምኑ ሁለቱም ተስማምተው በወንድ እጮኛዋ ጓደኞች አጃቢነት ወደ እጮኛዋ ዘመዶች በሰላማዊ ሁኔታ ትወሰድና እስከ ሰርጉ እለት ትቀመጣለች። ከዚያም ለሰርጉ የሚሆን ድግስ በወንዱ ቤት ተሰናድቶ ሲጠናቀቅ ወደ እጮኛዋ ቤት ትወሰድና የትዳር ጉዞ ይጀመራል። ቤተሰብ የመዳር አቅም ያላቸው ሆኖ እነሱ የማይፈልጉትን ወንድ ያገባች ሴት በቤተሰቦችዋ የማግለል ዛቻና ርግማን መሰንዘሩ የተለመደ ነው። ቢሆንም በሂደት ሽማግሌዎች ለእርቅ ተልከው ሁለቱ ወገኖች ከተነጋገሩ በሁዋላ እርቀ-ሰላም ወርዶ፣ ዝምድና ተመስርቶ የአብሮነት ኑሮ ተጀምሮ ይቀጥላል።

### 5.5.2.3. *እልገና*[93]

ይህ የጋብቻ አይነት *የሄረንቻ* ተቃራኒ ነው ማለት ይቻላል። *በሄረንቻ*፣ አንዲት ልጅ እንደምታገባ ወላጆች መረጃ አይኖራቸዉም፤ *በእልገና* /*Illgana*/ ግን እንደምታገባ የማታዉቀዉ ልጅቱ ናት። በዚህ የጋብቻ አይነት፣ ጋብቻዉ የሚከናወነዉ በጠለፋ ስም ሲሆን፣ 'ጠለፋዉ'ን የሚያመቻቹት ደግሞ ወላጆችዋ ናቸዉ። *በእልገና ጋብቻ* ለመፈጸም እንደምክንያት የሚጠቀሱ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም፣ የልጅቷ ወላጆች ለድግሱ ገንዘብ ማዉጣት አለመፈለግ፣ ቤተሰቦቿ በምስጢር ከልጁ ገንዘብ መቀበል እና ልጅቷም ወላጆቿ ያቀረቡላትን የትዳር ጓደኛ ለማግባት ፈቃደኛ አለመሆኗ

[93] *እልገና የቃሉ ቀጥተኛ ፍችው "ፊት መስጠት፣ በግንባር መጣቀስ ወይም ምልክት መስጠት" እንደማለት ሲሆን፤ ይህም ወላጆች ልጃቸው ስትወሰድ አውቀው እንዳላወቁ ዝም የሚሉበትን ሁኔታ አመልካች ቃል ነው።*

በምሳሌነት ይጠቀሳል። በዚህ ጊዜ ልጅቷ በጠሰፋ ስም ስትወሰድ ወላጆቿ ጩሀት ቢሰሙ እንኳን ሰምተዉ እንዳልሰሙ ይሆናሉ። ጠላፊዋም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ካገባት በኋላ ያለቤተሰቦቿ እዉቅና ጠልፎ እንዳገባት በማስመሰል ለእርቅ ሽማግሌ ይልካል።

### 5.5.2.4. *ለጐ* ፣ ውርስ

በሀዲያ የውርስ ጋብቻ በሁለት መንገዶች ሊከናወን ይችላል። የመጀመሪያው አይነት፣ አንዲት ሴት ባል ሲሞትባት የባል ወንድም አልያም የባል ወንድም ባይኖር ሌላ በዝምድና ለሟች የሚጠጋጋ ሰው በአካባቢው ሽማግሌዎች ወይም በሟች ቤተሰቦች ውሳኔ እንድታገባ ይደረጋል። ይህ የሚደረግበት ምክንያት አንድም፣ የሟቹ ወንድም የወንድሙን ልጆች እንደራሱ ልጆች እንዲያሳድግ ተብሎ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ወንድሙ ያፈራውን ንብረት ሌላ ባዳ እንዳይወርስ ተብሎ ነው። ሌላኛው *የለጐ* /*Lago*/ አይነት፣ አንድ አባት በባህሉ የተለያዩ ሚስቶች ሊኖሩት ስለሚችሉ፣ ያ አባት ሲሞት ከሟች አባት ታላቅ ሚስቱ የተወለደው የመጀመሪያ ልጅ የአባቱን የመጨረሻውን ወጣት ሚስት ከንብረቷ ጋር በመውረስ ማግባት ይችላል፤ ይህም በሀዲያ የባህል ስርአት የውርስ ጋብቻ *(ለጐ-ገስማ /Lago gassimma/)* ተብሎ ይታወቃል።

ኤርጎጌ (2008፡11)፣ የሀዲያ ሴቶች የዉርስ ጋብቻን በሚመለከት ብዙ ጊዜ ደስተኛ እንደማይሆኑ ጠቁማ አሉታዊ ስሜታቸዉን ፊት ለፊት ባይሆን እንኳን ቀጥለዉ በቀረቡት አይነት አባባሎች እንደሚገልጹ ጽፋለች።





*ሀ.*

| | |
|---|---|
| ለጋንች አሮዕ<br>Lagaanchi aro'i, | ወራሽ ባል |
| ላሜ ቀጤንስ<br>Laamee qaxeensi, | እስኪሰለቸዉ ድረስ |
| ሎሆ ጎሺሶኮ<br>Loho goshiisookoo, | ስድስት የወተት ላም ይሰጣል |
| ላማ ለሰጌ<br>Laamaa lasag, | በሁዋላ ሲሰለቸዉ |
| ሎሽኔ ቀሶኮ<br>Loshinne qasookko | በዱላ ይወጋታል |

*ለ.*

| | |
|---|---|
| ለጋንች አሮዕ<br>Laganchi aro'i | ወራሽ ባል |
| ላሞ ላሚንስ<br>Laamoo lamiinsi | ከመሰልቸቱ በላይ |
| ሌንጮ እል ጆራ<br>Leencoo illi jora | የግልምጫዉ አስቀያሚነቱ |

ከፍ ሲል የቀረቡት አጫጭር ግጥሞች በዉርስ ጋብቻ የሚያገባ ባል ከአንዲት ሴት ጋር የሚኖረዉን ግንኙነት ገላጭ ነዉ። ወራሽ ባል፣ በመጀመሪያዎቹ ወራት ለወረሳት ሚስቱ የሚያሳየዉን እንክብካቤ ሴቷ በግጥሞቹ አንስታ፣ በሂደት ሲሰለቸዉ እንክብካቤዉ ቀርቶ በእይታዉ እስከመገላመጥ እንደሚደርስ ብሎም እንደሚያጣጥላት ገልጻለች። ይህም ግጥም፣ የዉርሰ ጋብቻን አሉታዊ ጎን በተለይም ከሴቷ አመለካከትና ስሜት አንጻር ገላጭ ነዉ።

### 5.5.2.5. *ለዲሻ*

*ለዲሻ*/*Ladiishsha*/ ፣ አንዲት የታጨች ሴት ከወላጆቿ ቤት የሰርግ ቀጠሮ በተያዘበት እለት ህጋዊ በሆነ ወይም በባህሉ ተቀባይነት ባለዉ መንገድ ወደ እጮኛዋ ቤት የምትወሰድበት የጋብቻ አይነት

ነው። በዚህ የጋብቻ አይነት የድግስ ደረጃው ከሰዉ ወደ ሰዉ የተለያየ ቢሆንም በመደበኛ የሰርግ ስነስርአት የሚከናወን ነው። በመሆኑም *ለዲሻ* /*Ladiishsha*/ እንደ ድግሱ ደረጃ የተለያዩ ቅርጾችን (መልኮችን) በውስጡ የያዘ ነው። በመቀጠል *ለዲሻ* (ሰርግ) በዉስጡ የሚይዛቸዉን ዝርዝር ገጽታዎቹን ወይም *የለዲሻ* አይነቶችን አንድ በአንድ እንመለከታለን።

### 5.5.2.5.1. *ሆሻሮ* /Hoshsharo/

*ሆሻሮ*[94] የሚባለው የሰርግ አይነት የቃሉ ስያሜ እንደሚያሳየው፣ አጃቢዎች /ሰፍላ/ በሙሽሪት ቤት በማደር ፈንታ ደርሰው የሚመለሱበት ነው። ቀጥለዉ በሚገለጹት የሰርግ አይነቶች ሙሽራው ከአጃቢዎች *(ሰፍላ/ሀማሞታ)* ጋር አብሮ የሚሄድ ሲሆን በሆሻሮ ግን ወደ ሙሽሪት ቤት አይሄድም።

### 5.5.2.5.2. *ለንድሰንቻ*

በሀዲያ ባህል አንዲት ሴት ያለድግስ *(ለምሳሌ፣ በሄረንቻ)* ብታገባ በባለቤቷ ወገኖች በጎላዋ ላይ የንቀት ቀልድ (ፌዝ) ሊደርስባት ይችላል። በዚህ ጊዜ የተቀለደባትን ሁኔታ መሰረተ-ቢስነት ለማረጋገጥ በግብዣና በስጦታዎች የምታሳይበት ስነስርአት አለ፤ ይህም *ለንድሰንቻ* /landisanchcha/ ተብሎ ይታወቃል። *በለንድሰንቻ* የተቀለደባት ሴት ወገኖችዋ ዘንድ ሄዳ በማስደገስ የቀለደባትን (ለምሳሌ ቀላጁ ዋርሳዋ ሊሆን ይችላል) "ከፈለክ መቶ ሰዉ ይዘህ ና!" "*ኡሼእሶም*" በማለት ትናገራለች፤ ጎላዎችዋም ያንን የንቀት ንግግር ከንቱ ለማድረግ በአስቸኳዋይ ደግሰዉ ስጦታ በማዘጋጀት *ለንድሰንቻን* ይፈጽማሉ። በዚህም የሰርግ ስነስርአቱ እንደ አዲስ ይፈጸማል።

[94] ሆሻሮ /*ሆሽ-ዋሮ*/ ፣ የሚለዉ ጥምር ቃል ሲሆን በቀጥተኛ ፍች "ዉሎ መመለስ ወይም ደርሶ መልስ" ማለት ነዉ።





### 5.5.2.5.3. *አንጋቻ ወይም ቦሎቾኦ* /*Bollocho'o*/

*አንጋቻ* /angachcha/ ፣ የልጅቷ ወላጆች ልጃቸውን ለመዳር ሰፍላ *(ሀማሞታ)* የሚጋብዙበት የሰርግ አይነት ነው። በአንጋቻ ለሚጋቡ ሙሽሮች ድግሱ የሚሰናዳው በሙሽራም በሙሽሪትም ቤት ዉስጥ ነዉ። በሰርጉ እለት ወደ አርባ የሚደርሱ በሙሽራ በኩል የተዘጋጁ አጃቢዎች የተለያዩ የሰርግ ዘፈኖችን እየዘፈኑ ወደ ሙሽሪት ቤት ያመራሉ። በሙሽሪት ቤት በሴት ጓደኞቿ አማካይነት በሙሽራው አጃቢዎች ላይ የተለያዩ ስድቦች የሚደረደር በመሆኑ፣ ከሙሽራው ወገን የሆኑ ሴቶች በቃል ግጥሞቻቸው ከነዚያ ሴቶች ስድብ ፈጣሪ እንዲሰውራቸው መሻታቸውን ይገልጹላቸዋል፤ አጃቢዎቹም በግጥሞቹ ይሸኛሉ። ይህንን አስመልክቶ ተስፋዬ (1993፡ 479) ተከታዩን ግጥም ይጠቅሳል።

ኒየቦ ኑሪ ዋሬ፣
ለንድ አለቦ ቡይሳ ቁቤ

Niyyabbo nuuri waare
Land allabo buyyisa quube

"ወንድማችን በክብር ተመለስልን፣
የልጃገረዶች ምላስ እንደቅጠል ይጠውልግ"

በሚለው የቃል ግጥም አጃቢዎች ይሸኛሉ። ሆኖም አጃቢዎች ጥሩንባ እየነፉና እየጨፈሩ ወደ ሙሽሪት ደጃፍ እንደደረሱ የፈሩት ስድብ አይቀርላቸውም፤ በሴቶቹ ዘፈን መካከል አጃቢዎችን የሚያንቋሽሽ ስድብና ሽሙጥ የተቀላቀለበት ግጥም ይንቆረቆራል። እንዲህ አይነቱ መረር ቀልድና ስድብ

የያዘ ግጥም በሀዲያሳ *ሽርማ*[95] /Sharimma/ ይባላል። እንዲያውም በድሮ ጊዜ ሴቶች ከሸርማ አልፈው የበሰበስ እንቁላል በእጃቢዎቹ ላይ በመወርወር ሊማቱ ይችላሉ። ወንዶቹም እንደሴቶቹ ጠንከር ያለ ባይሆንም ለሸርማ አቻ የሚሆን ቃላዊ ምላሽ በግጥም ይመልሳሉ። በዚህ ሁኔታ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከቆዩ በሁዋላ የሙሽራው አጃቢዎች ወደ ቤት እንዲገቡ ይጋበዙና የተዘጋጀውን የምግብና የመጠጥ ድግስ ይስተናገዳሉ።

የግብዣው ስነስርአት እንዳበቃ ልጅቷ ከቤተሰቦቿ ስጦታዎችን በማሰናዳት ከቤት እንድትሸኝ ይደረጋል። ሙሽሪቷን የሚወስዷት በበቅሎ ሲሆን በመጀመሪያ ፈረስ ላይ ካስቀመጧት በሁዋላ ወደበቅሎ ያሸጋግሯታል። ይህም የሚደረገው በቅሎ የማትወልድ መሆኗ ጥሩ ተምሳሌትነት[96] ባለመኖሩ ነዉ። ሙሽሪትን በተዘጋጀላት በቅሎ ላይ በነጭ ነጠላ ፊቷን በመሸፋፈን ካስቀመጧት በሁዋላ የባሏ ሚዜ ከኋላዋ እበቅሎ ላይ በመቀመጥ ጃንጥላ ይዘላት ደግፎ ይይዛታል። ከዚያም በታላቅ ጭፈራና እልልታ ወደ ሙሽራው ቤት ትወሰዳለች። ሙሽራዉ ቤት እንደደረሰች የሙሽራው ቤተ-ዘመድ፣ ጐረቤትና የተጋበዙ እንግዶች ደማቅ አቀባበል ያደርጉላታል። ሙሽሪቷ በአማቾቿ በራፍ፣ በቅሎ ላይ እያለች ከሙሽራው ቤተሰቦች የተሰያዩ ስጦታዎች ሳይሰጣት አትወርድም። ይህ ስጦታ *እርፎኦ* /Irifo'o/ ወይም *ሀገራፍስማ* /Hagarafissima/

[95] *ሽርማ* ለሚለዉ መግለጫ በ1.6 ስር የቀረበዉን ይመለከቷል።

[96] ተምሳሌት የሚለዉ አንድን ሁኔታ ገላጭ ወይም ወካይ የሆነ ነገር ነዉ። ለምሳሌ፣ እርግብ ለሚመለከት ሰዉ የሰላም ወከይነቱ ጎልቶ ይታየዋል። እንደዚሁም ደግሞ፣ በሀዲያ ባህል በቅሎ የመሀንነት ተምሳሌት ነች። ሙሽሪትን አስቀድመዉ ፈረስ ላይ የሚያስቀምጧት፣ ልጅቱ ወደፊት ልጅ የምትወልድ እንድትሆን መልካም ምኞታቸውን መግለጻቸውን ለማመልከት ነው።





በመባል ይታወቃል፤ ስጦታዉም ተጋቢዎቹ የራሳቸውን ኑሮ ሲጀምሩ እጅጉን አስፈላጊና መሰረታዊ ነው።

ለሙሽሪቷ የሚሰጣት ስጦታ ከመጣ ወይም ቃል ከተገባ በሁዋላ ወደተዘጋጀላት ቤት ከመግባቷ አስቀድሞ ሙሽሪት መሬት ላይ እግሯን ዘርግታ እንድትቀመጥ ይደረጋል። ከዚያም አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ህጻናትን በማምጣት በሁለቱ ጭኖቿ ላይ እንዲቀመጡ ይደረጋል። ይህ የሚደረግበት ምክንያት ተጋቢዎቹ ወደፊት ወንድና ሴት ልጆችን አፈራርቀው እንዲወልዱ መልካም ምኞትን ለመግለጽ ነው። ከዚያ ቀጥሎ ተቆልቶ በተነጠረ ቅቤ ውስጥ የተነከረ ቡና እንድታኝክ ይሰጣታል። የቡናውና የቅቤው ተምሳሌታዊነቱ ወይም ዉክልናዉ /symbolism/፣ በሀዲያ ባህል ክብረ-ንጽህና እጅጉን የተከበረና ትልቅ ቦታ የሚሰጠዉ በመሆኑና ልጅቱ ክብረ-ንጽህና እንደሚኖራት የሚጠበቅ በመሆኑ፣ ለክብረ-ንጽህናዋ እዉቅና መስጠታቸዉን ወይም ማድነቃቸዉን መግለጽ ነዉ።

ከፍ ሲል የተገለጹት ስርአቶች እንዳበቁ፣ ሙሽሪቷ እንደተሸፋፈነች ወደተዘጋጀላት ቤት እንድትገባ ይመሯታል፤ በዚህ ጊዜ ከፍተኛ የእልልታ ድምጽ እቤት ዉስጥ እንደገና ያስተጋባል። ሙሽሮቹም አስቀድሞ በተዘጋጀላቸው እልፍኝ ወይም (*ጀገራ* /Jagara/) ውስጥ ለማረፊያነት ወደተዘጋጀላቸው *ዱማ* (እንደመጋረጃ ያለ ከለላ) ለመግባት ወደዚያ ያመራሉ። ሙሽሮቹ በር ላይ እንደደረሱ የሙሽራው ታላቅ እህት የእልፍኙን በር በመያዝ እንዳይገቡ ትከላከላለች፤ ይህም *ጐጫ አመድማ* /Gooca amadimma/ (በር መያዝ እንደማለት) በመባል ይታወቃል። ሙሽሮቹ ወደ ቤት መግባት የሚችሉትም ለልጅቱ የብር ስጦታ ሲሰጡ ብቻ ነው። ወደቤት

እንዳይገቡ የሙሽራው ታናሽ እህት እንደገና የዱማን በር ሸፍና ትይዛለች። ለታናሽ እህቱም ስጦታ ከተሰጣት በሁዋላ ሙሽሪትን ወደ መጋረጃዉ *(ዱማ)* ያስገቧታል።

### 5.5.2.5.4. *እል-ሞቻ*

*እልሞቻ/Illimoochcha/*፣ የሰርግ ሌላው ገጽታ ሲሆን ሙሽራው ከሰፍላ ጋር ወደ ሙሽሪት ቤት በሰርጉ ቀን አብሯቸው ይሄዳል። ጋብቻ በእልሞቻ ከሆነ ሙሽራው በልጅቱ ቤተሰብ የሚጋበዝ ሲሆን የሰፍላውም ቁጥር ወደ 60 ሰዎች ይጠጋል። ሙሽራው ከሰፍላው ጋር ወደ ሙሽሪቷ ቤት ሲደርስ አንድ ሰንጋ እንዲባርክ ይሰጠዋል። ሙሽራው ከመባረኩ በፊት ሽማግሌዎች ከሁለቱ ወገኖች (ከሙሽራውና ከሙሽሪት) ተመርጠው እንዲመርቁ ይደረጋል። ሙሽራው በቀጣይ ቀን ሙሽሪትን ከሰፍላው ጋር ይዟት ወደ ቤቱ እስኪሄድ ድረስ ሌሊቱን ከሰፍለው ጋር አብሮ ያሳልፋል።

በነጋታው በእልሞቻ የሚያገባ ሙሽራ የተለያዩ ስጦታዎችን በማስከተል ነው ወደ ቤቱ የሚመለሰው። ከስጦታዎቹ በቅሎ ለሙሽሪት፣ ፈረስ ለሙሽራው የሚበረከት ሲሆን የጋማ ከብቶችና ሌሎች ለጉጆ መውጫነት የሚዉሉ ስጦታዎች ይጠቀሳሉ። ይህ ስጦታን የመስጠት ልማድ በባህሉ *አዎንሲማ* /Awwansimma/ ወይም ኡሼእስማ /Ushe'issimma/ በመባል ይጠራል። ይህ የሰርግ አይነት ከኪፋ ቀጥሎ ብዙ ወጪ የሚያስወጣና ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው። በዚህም ምክንያት በዚህ ስርአት ያገባች ሴት እድሜ ልኳን በትልቅ ሰምና አክብሮት ስትታሰብ ትኖራለች።

### 5.5.2.5.5. *ኪፋ*

ይህ የሰርግ አይነት ከሌሎች (ቀደም ሲል ከተጠቀሱት) የሰርግ አይነቶች የበለጠ ውስብስብነት ያለው ነው።





ውስብስብነት እንዲኖረው ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ *በእልሞቻ* /Illimoochcha/ የሚፈቀደው የአጃቢ *(ሰፍላ / ሀማሞታ)* ቁጥር በኪፋ /Kiiffa/ ከፍ ማለቱ ነው። በኪፋ ስርአቱ ሀይሌ (1973፡144) የሰፍላን ቁጥር እስከ 80 እንደሚደርስ ሲገልጽ፣ ኤርሲዶ (2006፡73) ከ100 በላይ እንደሚሆን ይገልጻል። የአጃቢዉ ወይም የሰፍላዉ ቁጥር ከቦታ ቦታ የተለያየ ሊሆን ቢችልም በኪፋ የአጃቢ ቁጥር ከሌሎቹ ማለትም፣ ቀደም ሲል ከተገለጹት የሰርግ አይነቶች ከፍ ማለቱ የሚያግባባ ነዉ። *ኪፋን* ከሌሎቹ የሰርግ አይነቶች ልዩ የሚያደርገው *የአጃቢዉ* ብዛት ብቻ ሳይሆን የድግስ ጥራትም ነው።

በድግሱ ሂደት ለአጃቢዎች*(ሰፍላ ወይም ሀማሞታ)* የተለየ የምግብ ዝግጅትና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። የሙሽሪት እናት አስቀድማ በማንጠር ያዘጋጀችውን ቅቤ በማቅለጥ ለሰፍለው በጀግ (በኩባያ) ቀድታ ትሰጣቸዋለች። የቅቤው አቀዳድ ባንድ ዙር ብቻ አያበቃም፤ የልጅቷ እናት ቅቤው ከኩባያቸዉ ማለቁን በመከታተል ወዲያዉ እየዞረች ዳግም የተነጠረዉን ቅቤ ትሞላለች። በዚህ ሁኔታ ሰፍላዉ ቅቤዉን በመጠጣት መጨረስ ቢያቅተው ለሙሽሪቷ የተለየ አክብሮትና ቦታ በህይወት ዘመኗ ሁሉ ይሰጣታል፤ያንን ሁኔታ የሚገልጽ የጋብቻ ስምም ይሰጣታል። ከሌሎች ሴቶች የተለየች ተደርጋና ተከብራ ትኖራለች።

ሰፍላው ሙሽሪት ቤት የሚቆይበትን ጊዜ ሲጨርስ ለሙሽሮቹ በቅሎና ፈረስ ከተሟላ እቃ ጋር ፣የቀንድ ከብቶች፣ አህያና ሌሎች ነገሮች በስጦታ መልክ ይሰጣታል። ይህ ስጦታ በእልሞቻ ከሚሰጠዉ በደረጃዉ ከፍ የሚል ነው። በሁለተኛ /በሶስተኛ/ ቀን ሙሽሪት ከስጦታዎቿ ጋር

በአጃቢዎቿ ታጅባ ወደ ሙሽራው ቤት ትወሰዳለች፡፡ ወደ ሙሽራው ቤት እንደደረሰችም በሴት ልጆችና እናቶች፣ ብሎም በወጣቶችና ታላላቆች የደመቀ አቀባበል ይደረግላታል፡፡

ሙሽሪቷ ወደ ተዘጋጀላት እልፍኝ *(ጀገራ* /Jagara/) ከመወሰዷ አስቀድሞ በግቢው አስፈላጊው ስነስርአት[97] ይደረጋል፡፡ ከዚያም በእልፍኝ ወደተዘጋጀዉ *መጋረጃ* (በሀዲይሰ *ዱማ* / Duma/) ዉስጥ ትወሰዳለች፡፡ ሙሽሪት ወደ ሙሽራ ቤት ከመወሰዷ በፊት ምግብ እንዳትበላ በማድረግ የአበሻ ኮሶ ያጠጧታል፡፡ ለዚህ በባህሉ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ ጉዳዮች አሉ፡፡ አንደኛው ምክንያት፣ ሙሽሪቷ ለመጸዳዳት በስርጉ ጊዜ መመላለስ ነውር እንደሆነ ስለሚታሰብ ሆዷ ውስጥ ምግብ እንዳይኖር ለማድረግ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፣ በጫጉላ ምሽት ሙሽራው ክብረ ንጽህናዋን ለመገርሰስ በሚደረገው ጥረት በጫጉላ ከባድ ትግል እንዳይገጥመውና በቀላሉ መገርሰስ ይችል ዘንድ እንዲያዳክማት ታስቦ ነው ይባላል፡፡ በተጨማሪም ሙሽሪት አስቀድማ ጥፍሯን በጣም ወደ ውስጥ በማስገባት በምላጭ እንድትቆረጥ የሚደረገው በትግሉ ወቅት ሙሽራዉን እንዳትጐዳዉ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነም ይነገራል፡፡

በጫጉላ ቆይታዋ ሙሽሪት በሙሽራው ቤተሰብ ብዙ እንክብካቤና ክትትል ይደረግላታል፡፡ በዚህ ቆይታ ሙሽሪት ወደ ውጭ እንድትወጣ ወይም ርቃ እንድትሄድ በባህሉ የማይፈቀድ ሲሆን *ዱማ* ውስጥ እያለች ግን የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶችን ከስንደዶ ትሰራለች፡፡ በተጨማሪም *ሙሽሪት* በሀዲይሳ *እዳይቾ* /Idaayyichcho/ የባሏን የቅርብ ዘመዶች

[97] ያንን ስርአት በሚመለከት "አንጋቻ" በሚለው ርእስ ስር የቀረበዉን ይመለከቷል፡፡





(አባት፣ እናት…) በስማቸው መጥራት ስለማትችል የእነሱን ስም ብሎም በስማቸው የሚጀምሩ ሌሎች የሀዲይሳ ቃላትን እንዴት ወይም በምን ተክታ መጥራት እንደሚገባት ትምህርት ይሰጣታል፡፡ ይህንን[98] የምታስተምረው የባሏ እህት ናት፡፡

ሙሽሪት *መጋረጃ (ዱማ)* ውስጥ በምትቆይበት ጊዜ የባሏን ዘመዶችና ጓደኞች ለመጠየቅ በሚመጡበት ጊዜ ቤት ውስጥ እንኳን ሆና ከመጋረጃ ውጭ ብትሆን ርጣ ትደበቃለች፡፡ ፊቷን ለማየትና ለመተዋወቅ የሚፈልግ ሁሉ አስቀድሞ ስጦታ ማበርከት ወይም ስጦታ እንደሚሰጧት ቃል መግባት ይኖርበታል፡፡ ይህም በሀዲይሳ *እርፎኦ* /Irifo'o/ በመባል ይታወቃል፡፡

በ*እዳያና* (በመሞሸሪያ) ጊዜ[99] ሙሽሪት የተለያዩ ከመዳብና ከብረት የተሰሩ የተለየዩ ጌጣጌጦች ለምሳሌ፤ የጆሮ ጉትቻ፣ ቀለበት፣ አምባር የመሳሰሉትን በመልበስ ታጌጣለች፡፡ የጸጉሯ አሰራር ስልትም እንዲሁ ያገባች ሙሽራ መሆኗን የሚያውጅ መሆን ይኖርበታል፡፡ በሌላ አባባል፣ በሀዲያ ባህል የሴት ልጅ አሰባበስና የፀጉር አሰራር ስርአት ያላገባች *(ባጃም ለንድቾ)*፣ ሙሽሪት *(እዳይቾ)* ወይም ያገባች ሴት *(ሜንትቾ)* መሆኗን ወይም አለመሆኗን ገላጭ ነው፡፡ በኤርሲዶ (1999፣ 74) እንደተገለጸው በሀዲያ ባህል አንዲት ልጅ ከማግባቷ በፊት ያለው የጸጉር አሰራር *ባጃ* /baaja/ የሚባለው ሲሆን፣

[98] ይህ የቋንቋ አጠቃቀም *በሉዋሻ* በመባል የሚታወቅ ሲሆን ለተጨማሪ ማብራሪያ በሉዊሻ የሚለውን ይመለከቷል፡፡

[99] በሀዲያ ባህል የመሞሸሪያ ጊዜ *እዳያና* ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ይህም ከ1-2 አመት ባለ ጊዜ ዉስጥ የሚጠናቀቅ ነዉ፡፡

የታጨች መሆኑን ለማመልከት ጸጉሯ ለሁለት ከፊት ወደ ሁዋላ ተከፍሎ ይሰራል፡፡ ያልታጨች ከሆነ ግን ለሁለት ሳይከፊል ይሰራል፡፡ በአንጻሩ የሀዲያ ሴቶች ያገቡ መሆናቸውን የሚያመለክት የፀጉር አሰራር *ድልቦ* /dilibbo/፣ *ኮምቦባ* /kombooba/፣ *ገጅገጆኦ* /gajigajo'o/፣ እና *ቁነና*/qunanna/ የተባሉ ናቸው፡፡ የቀሚስ አለባበስን በሚመለከት፣ አንዲት ልጅ ሳታገባ በፊት አጠር ብሎ ከወደ ኋላዋ በትንሹ ተቀዶ የሚሰራዉን ቀሚስ የምትለብስ ሲሆን ስታገባ እግሯ ድረስ የሚሸፍን ረጅም ቀሚስ ታደርጋለች፡፡

ሙሽሪት በአዳያኖ ከዚያም በህይወት ዘመኗ ሁሉ የምትጠራዉ በድሮ በወላጆችዋ ስም ሳይሆን የምትጠራዉ የሙሽራው ቤተሰብ (አባት፣ እናት...) በሚያወጡለት ስም ይሆናል፡፡ በዚህ ስም የሚጠሯት የሙሽራው አባት ወይም እናት ብቻ ሳይሆኑ ቤተሰቦች ብሎም ሌላው ቤተዘመድ ሁሉ ይሆናል፡፡

## 5.6. *ዊዕሎ*/ *Wi'llo*/ ፤ የልቅሶና የሀዘን ስነስርአት

### 5.6. 1. በሀዲያ ገቀብር ስነስርአት አይነቶችን የሚወስኑ ጉዳዮች

የሰው ልጅ ወደሚኖርበት አለም በየተራው እንደሚመጣ ሁሉ በየተራው ወደ ማይመለስበት በሞት መሄዱ አይቀሬ ነዉ፡፡ ይህ ብሞት የሚደረገው የሰው ልጅ ሽኘት ከባህል ባህል የራሱ የሆነ ስርአት ይኖረዋል፡፡ በሀዲያ ባህል፣ በሟች የእድሜ ክልል ልዩነትና በግለሰቡ ማህበራዊ ርከን ወይም ደረጃ /social status/ የተወሰነ ልዩነት አለው፡፡ የሀዲያ ህዝብ ጥንታዊው የልቅሶና የሀዘን ባህል አንዳንድ ገጽታዎች በአሁኑ ጊዜ ሙሉ በሙሉ እንደተጠበቁ ያሉ ባለመሆናቸዉ ፣ እየጠፉ ያሉ ባህላዊ ገጽታዎችን ቀርሶ ማስቀረቱ /documenting/ ታሪካዊ





ፋይዳውን ከፍ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ እንግዲህ የቀጣዩ ክፍል ትኩረትም በዚሁ ርዕስ ጉዳይ ላይ ይሆናል፡፡ የለቅሶና የሀዘን ስርአቱ፣ እንደሟች የእድሜ ደረጃ እና ማህበራዊ ቦታ /ጀግንነት፣ ሀብት፣ መሪነት.../ የሚለይባቸው ገጽታዎች ስላሉ ተራ በተራ በተከታዩ ክፍል ቀርቧል፡፡

### ሀ. ህጻን ሲሞት

አንድ ህጻን ልጅ በተወለደ ቀን ቢሞት *ጪልች ብኣኮ*/Ciilichch bi'aakko/ (ህጻኑ ጠፍቷል) ወይም *ጪልች ሁሽጣኮ* / Ciilichch huushixxakko) (ህጻኑ አምልጧል) የሚል አነጋገር የተለመደ ነው፡፡ በሌላ በኩል፣ ገና ሲወለድ ያለ ጽንስ ቢጨነግፍ ደግሞ *ጪልች ጉደቦኔ ብኡኮ* /Ciilichch godabonne bi'ukko/ (ህጻኑ ሆድ ውስጥ ጠፍቷል) እየተባለ ይወራል፡፡ ከእነዚህ በአንዱ ወይም በሁለቱም መንገዶች ለሚሞቱ ህጻናት የለቅሶ ሰነሰርአት አይዘጋጅላቸውም፡፡ ወላጆችም ለጥቂት ጊዜ አዝነው ከመተው ባለፈ ህጻኑ ሞቷል ተብሎ አይነገርም፡፡

በሌላ በኩል፣ ከሁለት ቀን ጀምሮ ለሚሞት ህጻን የሚለቀስለት ሲሆን ከሌሎች ይበልጥ ሀዘንና እንባ የሚበረታባት እናት ነች፡፡ እድሜው ወደ አመት እየተጠጋ ለሚሄድ ህጻን የለቅሶ ስነስርአት መከናወን ስለሚኖርበት ሰፈር፣ ዘመድና እድርተኞች ይነገራቸዋል፡፡ ከስድስት ወር በታች ለሚሞት ህጻን አስቀድሞ የሚደርሰው ትንሹ እድር ነው፡፡ ትንሹ እድር የሚባለው ደግሞ ከ30-40 የሚያህሉ አባላት ያሉት ነው፡፡ ከስድስት ወር እድሜ በላይ ላስቆጠረ ሟች ግን ትልቁ እድር ይሳተፋል፡፡ የዚህ እድር ተግባራቱ የመቅበሪያ ጉድጓድ መቆፈር፣ እንጨትን ከየቤቱ ፈልጦ

ማምጣት፣ ለከብቶች በየተራ ሳር ማጨድ ሲሆን አካባቢ ለሚደረጉ የቀብር ዝግጅቶች እንግዳ ተቀባይ የሚሆነው ትንሹ እድር ነው። ይህ እድር፣ ለእንግዶቹ ቡና እያፈላ የሚያቀርብ በመሆኑም እድሩ *ቡዕን ሴራ* /Bu'nn seera/ (የቡና እድር) በመባል ይጠራል። በአጠቃላይ የህጻናት የለቅሶ ስርአት ከዚያ በላይ የሰፋ አይሆንም።

## ለ. ወጣት ሲሞት

በሀዲያ ባህል ከየትኛውም የእድሜ ክልል ይልቅ በወጣትነት ክልል ያለ ሰው ሲሞት ለቅሶው ወይም ሀዘኑ እጅጉን የበረታ ይሆናል። የሟች ቤተሰቦች (የአባት፣ የእናት፣ የወንድምና የእህት) ጥልቅ ሀዘን የሚገለጸው በለቅሶ ስነስርአት ወቅት በሚደረድሯቸው ግጥሞች፣ በመራራ ለቅሶ እና በሚያደርጉት የደረት መድቃት ድርጊት ነው። በተለይ ሴቶች ደረት መድቃታቸውንና ያልተቋረጠ ለቅሷቸውን እንዲተው ሲጠየቁ ለአፍታ እንኳን ዝም ሊሉ ፈቃደኛ አይሆኑም፤ በዚህም ምክንያት ድምጻቸው እስኪዘጋ ድረስ ይደርሳል።

በለቅሶ ስርአቱ ሟች ወንድ ወይም ሴት ስለመሆኑ/ኗ የሚታወቀው በግጥሞቹ በሚነገር የቃላት አጠቃቀም ስልት ነው። ሟች ወንድ ከሆነ *እወርቃ አዬ* /I worqa aayye/ (ዋይ የእኔ ወርቅ) የሚል ሀረግ በየስንኙ ቋጠሮው ሲደጋገም፣ ሴት ከሆነች ደግሞ *እ ባጆ*[100] *አዬ* /I baajo aayye/ (ዋይ የእኔ ቆንጆ ወይም ኮረዳ) የሚል ሀረግ ይደጋገማል። ወንድሞችና እህቶች ለሟች ወንድማቸው *እያባዮ* /Iyyabbaayyo/ (ወንድሜ) እያሉ ሲያለቅሱ ሟች እህታቸው ከሆነች ደግሞ *እያይቼ* /Iyyaayyichche/ (እህቴ) እያሉ ያለቅሳሉ።

[100] *ባጆ የሚለው የተመሰረተው ባጃሜ(የደረሰች ልጅ) የሚለው ቃል* በቁልምጫ አጥሮ ሲጠራ ነው።





እቤት ውስጥ ለወጣት ሟች የቅርብ ዘመድ የሆነ ሁሉ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያለቅስ ሲሆን የእናት ግን በእንጉርጉሮ የሚታጀብ በመሆኑና ሀዘኑም ጥልቅ በመሆኑ ከሌሎች ይልቅ የእናት ለቅሶ የብዙሀንን ትኩረት ይስባል። እናት ራሷን እስከመሳት ስለምትደርስ የሀዘኗ ሁኔታ እሷን ባያት ሁሉ ላይ ከፍተኛ የሀዘን ድባብ ያሰርጻል። እቤት ውስጥ አባት በዋና በር በኩል ከወንድ እኩዮቹ ወይም ዘመዶቹ ወይም ጎረቤቶቹ ጋር ተቀምጦ ሲያለቅስ ሴቷ በጓዳ በኩል እወንበር ላይ ተቀምጣ ስለ ሟች ቁመና፣ መልክ፣ ጸባይ፣ ታታሪነት ወዘተ. እየዘረዘረች ታነባለች፤ ሌሎችንም ታስነባለች፤ ምክንያቱም የምትደረድራቸው የሀዘን እንጉርጉሮዎቿ ይህንን የማድረግ ብቃት አላቸውና። ከዚህ በመቀጠል አንድ እናት ገና የሴትነት ወጓን ሳታይ ላለፈች ልጇ ያለቀሰችበትን ግጥም ከእየለ (1993፣ 14) በምሳሌነት መመልከት ይቻላል።

| *ሀዲይሳ* | *የአማርኛ ቀጥተኛ ፍች* |
|---|---|
| ለሞም አፎዕን እ ባጆ ኣዬ<br>Lamom afo'in i baajo aayye | ሁለቱንም ሳትደርሺ ዋይ የእኔ ቆንጆ |
| ቆታም እቶዕን እ ባጆ ኣዬ<br>Qootam itto'in i baajo aayye | ጥሎሽም ሳልበላ ዋይ የእኔ ቆንጆ |
| ቡሮም ቆሎዕን እ ባጆ ኣዬ<br>Buurom qollo'n i baajo aayye | ቅቤም ሳልቀባ ዋይ የእኔ ቆንጆ |
| መህና ግቦላ እ ባጆ ኣዬ<br>Mahna gibboolla i baajo aayye | ለምን ትሸሽያለሽ ዋይ የእኔ ቆንጆ |
| ኡታ ደበዕሌ እ ባጆ ኣዬ<br>Utta daba'ille i baajo aayye | ትተሽ ተመለሺ ዋይ የእኔ ቆንጆ |

ይህ ግጥም ገና የትዳር ህይወት ያልጀመረችዉን፣ ወግ ማእረግ ያላየችዉን፣ በአጭር የተቀጠፈችዉን ሟች ማንነት ገላጭ ነው። *"ለሞም አፎዕን"* /Lamome afoo'nni/

(ሁለቱንም ሳትደርሺ) የሚለው አገላለጽ በባህሉ የትዳር ወግ ሳታዩ የሚል ፍች ያለው ሲሆን፣ "ቡሮም ቆሎዕን" /Buurom qoloo'nni/ (ቅቤ ሳልቀባ) የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ወላጆች (በተለይ ብዙ ጊዜ እናቶች) ልጆቻቸው ሲያገቡ ደስታቸውን ለመግለጽ ቅቤ የሚቀቡበትን ሁኔታ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም አልቃሿ ይህንን ለማየት አልታደልኩም እያለች ስታንጐራጉር ነው የሚያሳየው፡፡ በአንጻሩ የአባት ለቅሶ የእናትን ያህል ረጅም አይሆንም፤ ምክንያቱም አባት፣ ለቀብሩ ስነስርአት አስፈላጊውን ነገር ከእድር አባላት ወይም መሪዎች ጋር ለማመቻቸት ወጣ ገባ በማለት ሁኔታዎችን የሚቆጣጠረው በይበልጥ እሱ በመሆኑ ነው፡፡

## ሐ. ለጐልማሶች እና ለአዛውንት

በህዲያ ባህል ለጐልማሶችና ለአዛውንት የሚደረግ የለቅሶ ስነ ስርአት ተመሳሳይ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ወደ አዛውንትነት የእድሜ ክልል ሲገባ በተለይ በጣም ሲያረጅ ወደ ሞት እየተቃረበ እንደሆነ ስለሚያስብ ራሱን ያዘጋጃል፤ ሲሞትም ለቤተሰቡ አሟሟቱ ዱብ እዳ ላይሆን ይችላል፡፡

በህዲያ ህዝብ ዘንድ የስጋ ደዌ ህመምተኞች[101] ከጤናማዎች ጋር ተመሳሳይ የቀብር ስነስርአት አይደረግላቸውም፡፡

[101] በአሁኑ ጊዜ በስጋ ደዌ በሽታ የሚታመም ሰው ባይታይም፣ በቀደሙት ዘመናት የዚያ በሽታ አሻራ አርፎባቸው በህክምና የደኑትን እንኳን አብዛኛው የሀዲያ ህዝብ በጋብቻ ለመቀላቀል ፈቃደኛ እንደማይሆን ይነገራል፡፡ አንድ የስጋ ደዌ ተጠቂ የነበረ ሰው የህክምና ርዳታ ቢያገኝ በሽታው በዘር እንደማይተላለፍ የህክምና ሳይንሱ ያረጋገጠ ቢሆንም አሉታዊ አስተሳሰቡ፣ የበሽታው ቀጥተኛ ተጠቂ ባልሆኑ ቤተሰቦች ላይ የስነልቦና ጫና እንደሚፈጥር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኼም ቢያንስ በሰንበት ዘመን ሳይንሳዊ መሰረት የሌለው በመሆኑ መቅረት ያለበት አስተሳሰብ ነው፡፡





የስጋ ደዌ በአሁኑ ዘመን በህክምና የጠፋ ወይም አለ ዚባል እንኳን እንደብርቅ የሚቆጠር ሲሆን የባህሉ አባላት የሆኑ ሽማግሌዎች በሽታው ተስፋፍቶ በነበረበት ዘመን ለህሙማኑ ሲሞቱ ይደረግ የነበረዉን የቀብር ስነስርአት እጅጉን የተለየ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በህዲያ ባህል የስጋ ደዌ ህመምተኛ ሲሞት ሞተ ወይም አረፈ ተብሎ አይነገርም፤ ይልቁን ሰዉዬዉ ተሰብሯል (*መንች ኢቃማኮ* /Manch iiqamaakko/) ተብሎ ይነገራል፡፡ የቀብር ስነስርአቱ አፈጻጸምም እንደሌሎቹ ሟቾች የቀብር ስነስርአት (*ዋሚማ* /Waamimma/) ተብሎ አይጠራም፤ የቀብር ስነስርአቱ *ኢቅማ* /Iiqimma/ (መስበር) ተብሎ ነዉ የሚጠራዉ፡፡ በሌላ በኩል፣ በባህሉ የስጋ ደዌ ህመምተኛ ሲሞት ማልቀስ አይፈቀድም፡፡ ሌላው ቀርቶ ድምጽ ሳያሰሙ፣ እምባ እያፈሰሱ ማልቀስ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚጠቀሰው ለዚያ ሟች የሚለቀስ ከሆነ የስጋ ደዌ በሽታው በዘሮቻቸው እንደሚተላለፍ ስለሚታመን ነው፡፡ ድንገት ከቤተሰቡ መካከል አፈትልኮ የሚያለቅስ ሰው እንዳይኖር ተብሎ ቤተሰቡን የሚመክር ደግሞም የሚያስጠነቅቅ ሽማግሌ ይመደባል፤ እሱም ከቤተሰብ መካከል ለዚያ ሟች የሚያስለቅስ ቢኖር "እርግማን" ወይም በሽታውን በዘሮቹ እንደሚያስተላልፍ በመጥቀስ ይመክራቸዋል፡፡ በቀብር ስርአቱ እንኳን ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው እድሮች ወይም የሟች ዘመዶች ሳይሆኑ ሸክላ ሰሪዎች ወይም *ፋጋዎች* ናቸዉ፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚጠቀሰዉ በባህሉ ለፋጋዎች የሚሰጠው ግምት ዝቅተኛ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም እንዲህ አይነት አስፈሪ ሁኔታ ላይ የሚያሰሯቸው እነሱን ነው፡፡

ከፍ ሲል በተጠቀሰው ምክንያት የቀብር ስነስርአት ሲፈጸም ጉድጓድ ቆፋሪዎች እና አስክሬኑን ተሸክመው ወደ መቃብር ወስደው የሚቀብሩት እድርተኞች ሳይሆኑ ፉጋዎች ናቸው። ከሟች ዘመዶች ውስጥ ወይም ከእድርተኛው አስክሬኑን ለመሸከም የሚፈልግ ቢኖር እንኳን አድናቆት አይቸረውም። ይልቁን በሽታውን ወደ ተከታዩ ጐሳ ወይም ትውልድ ለማስተላለፍ የሚመኝ ርጉም እንደሆነ ይቆጠራል።

የስጋ ደዌ በሽተኛ ሲሞት እቤት ውስጥ በስሎ የነበረ ምግብ እና ሟች ይጠቀምባቸው የነበሩ እቃዎች ለአብነት ጋያ፣ ጦር፣ ጉራዴና የመሳሰሉት ቢኖሩ ከቤት ወጥቶ ይጣላል። እቤት ውስጥ የሚጠጣ ወተት እንኳን ቢኖር ከመድፋት ውጭ አይጠጣም። አስክሬኑ ባንዳንድ ምክንያቶች ቶሎ ባይቀበር መብላት የሚፈቀደው ከጎረቤት የመጣ ምግብ ብቻ ነው። ለዚህም ምክንያቱ የቤቱ ምግብ ቢበላ በሽታው በዚያ ምግብ አስታኮ ወይም አሳቦ ወደሚመገቡት ሰዎች እንደሚተላለፍ ስለሚታሰብ ነው።

የስጋ ደዌ ያለበት ሟች ሲገነዝ እንኳን በጨርቅ ሳይሆን በርጥብ የከብት ቆዳ ተጠቅልሎ ነው። ሲቀበርም ይህ በሽታ ከሟች ወደ ተከታዩ ትውልድ እንዳይተላለፍ የሚደረግ ስነስርአት ወይም ልማድ አለ። አራት ጥቋቁር የበግ ግልገሎች ተገድለው ወይም ታርደው ከአስክሬኑ ጋር በመቅበር ገደብ የማበጀት (ጉዶ /Guddo/) ስነስርአት ይደረጋል። በዚህ ሁኔታ የቀብሩ ስነስርአት ተደርጐ ሲያልቅ፣ ከቀብር በሁዋላ ምንም አይነት የምግብ ዝግጅት አይኖርም፤ ሌላው ቀርቶ የሟቹን ቤተሰብ እግዚአብሄር ያጥናህ (በሀዲይሳ "ዋዕ ሰብራታ ኡዎና") /Waa'i sabiraata uwwona/ እንኳን አይባልም። ከቀብር በኂላ የስጋ ደዌ ህመምተኛ ያልሆነ ሰዉ





ሞቶ ሲቀበር የሚኖር አይነት የሀብት ክፍፍል ጥያቄ ከቤተሰብ አይነሳም። ያ ንብረት የተረገመ እንደሆነ ስለሚታሰብ ለፉጋዎች ይሰጣል፤ ይህም ከፍተኛ ዋጋ ያለን ነገር አያካትትም። እሱ ይኖርበት በነበረው ቤት ዉስጥ አይታደርም፣ ለቤተሰቡ ሌላ ቤት እስኪሰራ ድረስ በጊዜያዊ መጠለያ ወይም ዳስ ዉስጥ እንዲያርፉ ይደረጋል። ሟች የነበረበት የድሮ ቤትም ፉጋዎች አፍርሰው እንዲወስዱ ይደረጋል።

ቀደም ሲል የስጋ ደዌ ህሙማን ሲሞቱ ከሚደረግላቸው የለቅሶና የሀዘን ስነስርአት በተቃራኒ የበሽታው ተጠቂ ላልነበሩት የተለየ የለቅሶ ስነስርአት በባህሉ እንዳለ በግልጽ ተስተውሏል። በዚህ አይነቱ የለቅሶ ስርአት፣ ስነስርአቱ በተረጋጋና ውል ባለ መልኩ እንዲከናወን *ከምሎ* ወይም *ከነፈራ* የሚመረጡ የሽማግሌዎች መማክርት አለ።

ጠቅለል ባለ አገላለጽ፣ በሀዲያ ባህል የለቅሶ አወጣጥ ስነስርአት ሁለት መልኮች አሉት። አንዱ መንገድ ሟች ህይወቱ እንዳለፈ ለወዳጅ ዘመድ ተነግሮ፣ የለቅሶ ስነስርአት ተፈጽሞ የሚጠናቀቅበት ነው። በሌላ በኩል፣ ሟች በጣም ተዋቂ ሆኖ የሞተበት ጊዜ የኢኮኖሚ ችግር ያለበት ወይም እህል የሚዘራበት ወቅት ቢሆን ለጊዜው ቤተዘመድና በአካባቢው ያሉት ሰዎች እንዲቀብሩ ይደረግና አመቺ የሆነ ጊዜ ተመርጦ የለቅሶ ስነስርአት በስፋት የሚፈጸምበት ጊዜ ይቀጠራል። ይሄም ቀጠሮ የሚያዝበት ጊዜ፣ አብዛኛውን ጊዜ እህል ከተሰበሰበ በሁዋላ በጋ ላይ ነው እሚሆነው። ይህ የሚደረግበት ምክንያት ሟች ተዋቂ ሆኖ ከፍተኛ ድግስ ተደግሶ ለቅሶ የሚደርሱ ሰዎች እና አልቃሾች በሚገባ ካልተስተናገዱ ዉርደት ተደርጐ ስለሚቆጠር ነው። በቀጣይ

ክፍል ተዋቂ እና ጀግና የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ የሚደረገውን የለቅሶና የሀዘን ስነስርአት በተከታዩ ሁኔታ ማየት ይቻላል፡፡

## መ. ለተዋቂ ሰዎች እና ለጀግኖች

በቀደመው ዘመን በህይወት እያሉ ጦርነት ዘምተው በመማረክ ወይም በመግደል ወይም አስፈሪ አውሬዎችን አድነው በመግደል የታወቁ ሰዎች ሲሞቱ እንደሌላው የማህበረሰብ ክፍል አይቀበሩም፡፡ ይህ ስርአት በተጨማሪም በመሪነት ችሎታ፣ በሀብት እና በመሳሰሉት ከሌላው ህዝብ ወጣ ያሉትን ያከትታል፡፡ የቀብር ስነስርአቱ ከመከናወኑ በፊት የቀብር ቀንን እና የሟችን ማንነት በሚመለከት በተመረጡ ድምጻውያን በገበያ እንዲለፈፍ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ተግባር የተለያዩ ድምጻውያን (ቢያንስ አራት) ጥሩ አቋም ካላቸው ፈረሶች ጋር ተመርጠው ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህ በየሰፈሩና በየገበያው በፈጣን ፈረስ ግልቢያ እየከነፉ የሚያረዱ ለፋፊዎች *አረዳኖ* /Aradaano/፣ ወይም *አረጃኖ* /Arajjaano/፣ በመባል ሲታወቁ የልፈፋው ሂደት *አረድማ* /Aradimma/ ተብሎ ይጠራል፡፡

*አረጃኖ* /Arajjaano/፣ ወደ ልፈፋ ከመሄዳቸው በፊት የሚበሉት ተስጥቷቸው ይስተናገዳሉ፡፡ ከዚያም መንገድ ላይ እና በገበያ መሀል ሲያልፉ ስለሟች እንዴት እንደሚለፍፉ አፍ ፍተሻ (በሀዲይሳ፣ *ሱሜ ሞእማ)* /Suume moo'imma/ እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ፡፡ እነሱም እዚያው እደጃፍ ላይ እያሉ በተዘጋጀላቸው ውብ ፈረሶች ላይ በመውጣት ቤተዘመድ በተሰበሰበበት ስለሟች የተለያዩ ስንኞችን በመደርደር፣ ስሜታቸው ተወጣጥሮ፣ በፈረስ ላይ ሆነዉ ወዲህና ወዲያ እያሉ ትእይንቱን ያሳያሉ፡፡ *በአረድማ* መሀል





*ዶዩኮ* /Dooyyukko// (ኮበለለ፣ ዳግም ላናየዉ ነጎደ) የሚል ቃል ተደጋግሞ ይነገራል፡፡ *አረዳኖ* (ለፋፊዎች) እንዲህ አይነቱን የሙከራ ወይም አፍ የመፈተሻ ስርአት ካደረጉ በሁዋላ የሟች ቤተዘመዶች መርቀዋቸው በተለያዩ አቅጣጫዎች ሁለት ሁለት እየሆኑ ይበተናሉ፡፡ ሲንቀሳቀሱም፣ተልእኳቸዉን ፈጽመዉ ሲመለሱ እኩል መግባት ስለሚኖርባቸው የመመለሻ ጊዜ ወስነው ነው ጉዞ የሚጀምሩት፡፡

በመንገድ እየሄዱ እያሉ ገና ገበያ ሳይደርሱ በግጥሞቻቸው ውስጥ የሟቹን ስም እየጠቀሱ፣ የቀብሩን ቀን እና ቦታ እያሳወቁ ይጋልባሉ፡፡ ገበያ እንደ ደረሱም *አረጃኖ* እየተቀባበሉ ሲለፍፉ የገበያው መንፈስ ይለወጥና የገበያተኛው ትኩረት ወደነሱ ይሰበሰባል፡፡ በዚህ ጊዜ ብዙዎች የሟችን ማንነት ለማወቅ ስለሚጓጉ ይከቧቸዋል፡፡ በዚህ መሀል የዘመዱን መሞት ያልሰማ ሰዉ ቢኖር ድንገት በድንጋጤ ራሱን ስቶ ሊወድቅ ይችላል፡፡ *አረጃኖ* ከሚደረድሯቸው ግጥሞች ለማሳያነት ተከታዩን ማንሳት ይቻላል፡፡

| *ሀዲይሳ* | *የአማርኛ ቀጥተኛ ፍቾ* |
|---|---|
| ዶዩኮ ዮሞ<br>Dooyyukko yoommo | ሄደ፣ ነጎደ እላለሁ |
| ኤሀዶ ጎንቺ ዶዩኮ<br>Eehido goonchii dooyyukko | እንዲህ አይነቱ ጀግና ሄደ፣ ነጎደ |
| ኡራግ ሆንስ አኒ ዶዩኮ<br>Uraag hons anni dooyyukko | ዘጠኝ ገዳዩ ተሰናብቷል |
| ለንዲ ለንድ አሮኢ<br>Landii land aro'i | ሴት ልጆች ከነባሎቻችሁ |
| ኤ በላ ዊዕሎ ዋሌሄ<br>Ee balla wi'illo waallehe | በዚህ ቀን ለቅሶ ድረሱ |

በዚህ ሁኔታ ለፋፊዎቹ ተልእኳቸዉን ፊጽመው እንደተመለሱ፣ ከቤት እኩል እንደወጡ ወደ ቤት እኩል ይገባሉ። ወደ ለቅሶ ቤት እንደተመለሱም የሟች ቤተሰቦች እንዴት እንደለፈፉ መልሰው እንዲያሳዩ አረዳኖን ይጠይቋቸዋል። እነሱም ፈረሶቻቸው ላይ እንደተቀመጡ ወዲህና ወዲያ እየተመላለሱ ተራ በተራ ያሉትን ይደግማሉ። እንደጨረሉም የሟች ሚስት፣ ልጅ ወይም ወንድም ለያንዳንዳቸው የብር ስጦታ የሚሰጡ ሲሆን ከነዚያ ለፋፊዎች ውስጥ የተሻለ ለፋፊው የብር ስጦታው ከሌሎቹ እጥፍ ይሆንለታል።

## 5.6.2. የቀብር ስነስርአት

ለቀብር ስነስርአት ማከናወኛ በተያዘ እለት ገና በጧት በእድር ተረኞች መቃብር እንዲቆፈር ይደረጋል። የመቃብር ቁፋሮ በሀዲያ ባህል የራሱ ስርአት አለው። ቁፋሮው ከመጀመሩ በፊት ከጧቱ አስራ ሁለት ሰአት ላይ የበኩር ልጅ ቁፋሮዉን ያስጀምራል። ሲያስጀምርም የሚቆፈርበትን ቦታ በመጥረቢያ በመውጋት ምልክት ማድረግ ይኖርበታል። ይህም በባህሉ *በር-ቀሻ* /bar qashsha/ (ጉድጓድ መውጋት) ተብሎ ይጠራል። የመቃብር ቦታውን ሲወጋ እቤት ውስጥ ባለው በሬ ወይም ላም አንዱን ጠርቶ በእንስሳው ስም ወግቻለሁ (ለምሳሌ ፣ *ከሼኤን ቀሳሞ* /Kashe'enne qasaammo/፣ "በከሼ ወግቻለሁ") በማለት ስርአቱን ይፈጽማል። የበኩር ልጅ ባይገኝ በእድሜ የእሱ ተከታይ ወንድም የመቃብር ቦታ የሚወጋ ሲሆን በስሙ የወጋዉን ከብት ግን ታላቅ ወንድሙ እንዲወስድ ይደረጋል። በዚህ ስርአት ሴት ልጅ የመቃብር ስፍራ እንድትወጋ አይደረግም፤ ምክንያቱም ሴት ልጅ አግብታ ስለምትሄድ መቃብሩንና የሚኖረውን ነገር ሁሉ መከታተል አትችልም ተብሎ ይታሰባል። ሟቹ፣ ልጆች የሌሉት ከሆነ ግን





ወንድም ወይም ሌላ የቅርብ ዘመድ የመቃብር ቦታን ሲወጋ ወይም ምልክት ሲያስርፍ ይችላል። በሌላ በኩል፣ ልጅ ሲሞት አባት የመቃብር ቦታ የሚወጋ ሲሆን ልጅ ንብረት ቢኖረው እንኳን በንብረቱ ስም አይወጋም።

ይህ ስርአት እንዳበቃ ወደ በራፍ ይመለሱና እድሩ የተለያዩ ድንኳኖችን ከተከለ በሁዋላ የለቅሶ ስነስርአት ተጠናክሮ ይጀምራል። ይህ ቀን ከሌላው ይልቅ ደማቅ ይሆናል፤ ምክንያቱም ሟች ላይመለስ በቀብር የሚሸኝበት ነውና። ለለቅሶ ስነስርአት ድምቀት የፉጋዎች ሚና እጅጉን ከፍተኛ ነው። በቀብር እለት ፉጋዎች የምግብና የአረቄ ግብዣ ገና በጧቱ ተደርጉላቸው ለለቅሶው ስርአት ማድመቂያነት ይዘጋጃሉ። አረቄ የሚሰጥበት ምክንያት በለቅሶ ስነስርአቱ በሚያሳዩት ትወና ወይም ትርኢት ድፍረት እና ሀይል እንዲሆናቸው ታስቦ ነው።

የለቅሶው ስነስርአት ሲጀመር ሁሉም ሰው በተዘጋጀው ሜዳ ላይ ይሆናል። የሟች ልጅ ጮጮ (*ኦቾ* /Ochcho/)፣ የሟቹን ከፖርት እና ሱሪ እንድትይዝ ይሰጣታል። ሚስትም በበኩሏ ባሏ ገዳይ ከነበረ *ባሌዔ* /Baall'e/ (ነጭ የእርኩም ላባ) ጸጉሯ ላይ በግራ እና በቀኝ ስከታ፣ የጉሬዛ ቆዳ ለብሳ በርጨማ ላይ ትቀመጣለች። ጦር እና የጉሽ ቀንድ አጠገቧ ይሆንና አልቃሾች ሲመጡ እየተነሳች እያለቀሰች ትቀበላቸዋለች። ሚስትም ስታለቅስ የተለያዩ ሟች ባሏን የሚያወድሱ ግጥሞችን በመደርደር ነው።

በቀብር እለት የሚሰበሰበው ሰው ሁሉ ለሟች ከልቡ አዛኝ ላይሆን ይችላል፤ የነጋሪቱን ጉሰማ ሰምተው የሚደረደሩ

የሙገሳ ግጥሞችን ለማድመጥ እና ለማድነቅ ሲሉ ወደ ለቅሶ ስነስርአት መፈጸሚያ ቦታ ሊሄዱ ይችላሉ፡፡ በዚህ ትእይንት ውስጥ አስለቃሾች ፋጉች ብቻ አይሆኑም፡፡ የሟች ዘመድ የሆኑ ሴቶች እወገባቸው ላይ የነጠላቸውን አንድ ጫፍ ቁልቁል በማሰር፣ ሌላኛውን ሁለቱን ጫፎች ወደ ላይ በሁለቱ እጆቻቸው በአንገታቸው ትይዩ አንስተው በመያዝ ጣቶቻቸውን ሰብሰብ አድርገዉ ወደፊት ወደ ሁዋላ ሰበር መለስ፣ ሰበር መለስ እያደረጉ፣ አንገታቸውን መዘዝ ጠለቅ እያደረጉ፣ ከጉልበታቸው በርከክ ብድግ እያሉ ከነጋሪቱ ምት ጋር ተስማምተው አንድ ላይ ይሄዳሉ፡፡ የነጋሪቱ ጉሳማ አጅቧቸው እነሱ በረድፍ ሆነው ወደፊትና ወደሁዋላ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ይህም ስርአት *ነጋሪት ህግማ* /Nagaariita higimma/ (በቀጥታ ፍችው ነጋሪቱን ማለፍ) በመባል ይታወቃል፡፡

በዚህ እለት በአካባቢው የሚሰማ ድምጽ የብዙዎችን ትኩረት ከመሳቡም በላይ የነጋሪቱ ጉሳማ፣ የአስለቃሾቹ የግጥም ድርደራ፣ የወንዶችና የሴቶቹ ባህላዊ ውዝዋዜ ለተመልካች ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ይፈጥርበታል፡፡ በተጨማሪም ወንዶች ጦር ወይም ከወደጫፉ ሾል፣ ቀጠንና ረዘም ያለ ዱላ ይዘው የነጋሪቱን ድምጽ ተከትለው ከፍና ዝቅ እያሉ የደመቀ እንቅስቃሴ ማሳየታቸው ለለቅሶ የመጣውን ሰው ሁሉ ተሳታፊ ወደ መሆን ሊቀሰቅስ ይችላል፡፡

በቀብር እለት ከሚዜሙ ዜማዎች አንዱ *ሆሌ መንቾ* /Hoole mancho/ (አወይ ሰው!) የተሰኘው የለቅሶ ዜማ ነው፡፡ ለማስለቀስ የተሳተፉ ወንዶች ወገብ ለወገብ ተያይዘው በመሰለፍ፣ ፊት ለፊት እየተያዩ በመወዛወዝ ያዜማሉ፣ ያስለቅሳሉ፡፡ "*ሆሌ መንቾ*" የሚለዉ ጠንካራውና ጀግናው ሰው





በሞት ተረታ፣ አረፈ የሚል ፍች የያዘ ሀረግ ነዉ፡፡ አቀራረቡም፡-

ሆ - ሆ - ዶዩኮ /ho – ho - dooyyukko/

ሆሌ - ሆሌ - ዶዩኮ /hoole – hoole - dooyyukko/

በማለት እንደ አዝማች የሚደጋገሙት ሲሆን፣ በመሀል የተለየዩ ስንኞችን ያስገባሉ፡፡ ይህ ሲደረግ ግጥሞቹን የሚያወጣ አንድ ሰው በሁለቱ ሰልፎች መካከል ቆሞ፣ ጦር በቀኝ እጁ በመያዝ፣ ጦሩንና ቀኝ እግሩን ከግጥሞቹ አደራደርና ከዜማዉ ጋር እኩል በማስማማት ብድግ እያደረገ ያወጣል፡፡ ሰልፈኞቹ አስለቃሾችም እሱን ተከትለው *ሆሌ መንቾን* እንደ አዝማች ይደጋግሙታል፡፡ ይህንን የሚያደርጉት የአውጪውን በየመሀሉ የሚያደርገውን ቆምታ እየተከታተሉ፣ እግራቸውን ብድግ፣ ረገጥ፣ ራመድ እያደረጉ በማዜም ነው፡፡ ጀግና አባት የሞተባቸው ልጆችም የአባቱን ጀግንነት የሚገልጽ ጦርና ጋሻ በማወዛወዝ ለቅሶውን ያደምቃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሌሎች ሀዘንተኞች ተከታዩን አይነት የሙገሳ ግጥም በመደርደር ለሟች ያለቅሳሉ፡፡

| *ሀዲይሳ* | *የአማርኛ ቀጥተኛ ፍች* |
|---|---|
| አዬ ወርቃ /Aayye worqa/ | ዋይ ወርቅ ነበር |
| አዬ ሞራ /Aayye moora/ | ዋይ መሪ ነበረ |
| አዬ ህጋ /Aayye higa/ | ዋይ ተወዳዳሪ የለሽ ነበረ |

እያሉ ሲያለቅሱ፣ ሟች ውድ፣ ጠንካራ እና ተወዳዳሪ የሌለው መሪ እና ጀግና እንደነበረ በማስታወስ ጸጸታቸውን በግጥሞቹ ይገልጻሉ፡፡ *ወርቃ* (ወርቅ)፣ *ሞራ* (ኮርማ)[102]፣

[102] ኮርማ የሚለዉ በዚህ አገባቡ መሪ የሚል ፍች አለዉ፡፡

እና *ሀጋ* (ወደር የለሽ) የሚሉት ቃላት ሟች በህይወት እያለ የነበረዉን ማህበራዊ ርከን/social class/ እና ተወዳጅነቱን አመልካች ቃላት ናቸው፡፡ እንዲህ አይነቱን ዜማ እያዜሙ ቤተዘመድ የሆኑ ሰዎች ሲያለቅሱ በራሳቸው ላይ አካላዊ ጉዳት ሲያደርሱ ይችላሉ፡፡ በተለይ በቀድሞ ጊዜ ሴቶች የሚችን ውለታ እያውጠነጠኑ ፊታቸውን በቆንጥር (እሾህ በመሰለ ነገር) ይቧጭራሉ፤ ቆዳቸው እስኪደማ ድረስ በመቧጨር ራሳቸውን ይጎዳሉ፡፡ ወንዶችም በተለይ ሟች ውለታ የዋለላቸው ከሆነ ጀርባቸውን በጉማሬ አለንጋ በመግረፍ ለሟች ያላቸውን ጥልቅ ፍቅርና ክብር ይገልጻሉ፡፡

የለቅሶ ስነስርአት በዚህ መልኩ እየቀጠለ እያለ የእድር መሪዎች አስክሬኑ ወደ ቀብር የሚወሰድበት ጊዜ መድረሱን ሲናገሩ የሟች ቤተሰብ የአስክሬኑን ሽኝት ሲያስቡ ትኩስ ለቅሶ የተለማ አይነት/ያህል/ ከፍተኛ ጩኸት ያስተጋባሉ፤ ምክንያቱም ያች ጊዜ ሟችን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ የሚለናበቱበት አፍታ ናት፡፡ በዚህ ጊዜ የግብአተ መሬቱን መዳረስ ለመግለጽ ፉጋዎቹ የነጋሪቱን አመታት ድምጹን ጎላ ያደርጋሉ፡፡ የሟችን ስራዎች በሚዘክሩ ግጥሞችና ዜማዎች ብሎም በህዝቡ ጩኸትና እምባ አስክሬኑ[103] ታጅቦ ወደመቃብር ቦታ ተወስዶ ይቀበራል፡፡ ከቀብር በኋላም ሚስት እስከ አርባ ቀን ድረስ የሰው ቤት አትገባም፤ ጸጉሯን ትላጫለች፤ ጥፍሯን አትቆረጥም፤ ጥቁር ልብስ ለብሳ ሀዘን

[103] አስክሬኑ የሚለብሰዉ ቀይ ልብስ ወይም ከፈን ሲሆን በሀዲይሳ *መዳ* /Madda/ በመባል ይታወቃል፡፡ አስክሬኑ ለቀብር እየተወሰደ እያለ ፈረሰኞች ከአስክሬኑ ፊት ለፊት በመሆን የሚጋልቡ ሲሆን፣ ፉጋዎቹ የነጋሪቱን ድምጽ ያጎላሉ፡፡ የሟችን ስራ ነጋሪዎችም የህዝቡ ለቅሶ ድምጽ ከፍ ስለሚል ከዚያ አጉልቶ ለማዉጣት ሲሉ በከፍተኛ የድምጽ ቃናና ስሜት የሙገሳ ግጥሞቻቸዉን ያሰማሉ፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ አስክሬኑ ወደቀብር ቦታ ተሸኝቶ ስነስርአቱ ይፈጸማል፡፡





ላይ መሆኗን ትገልጻለች፡፡ በዚህ መሀል ሌላ ሰው ቢሞት፣ ጀግና ካልሆነ በቀር ለቅሶ ቤት አትሄድም፤ ጀግና ሰው ሲሞት እንኳን ገባ ብላ ነው የምትመለሰው፡፡

## 5.6.3. ድህረቀብር

ከቀብር ስነስርአት ፍጻሜ በሁዋላ ሰው ወደ ሟች ደጃፍ ተመልሶ በተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ድግስ ይስተናገዳል፡፡ ይህም በሀዲይሳ *ወኦ-አግሻ* /Wo'o agishsha/ ተብሎ ይጠራል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ *ሰብራታ አዕማ* /Sabiraata aa'imma/ ('ሰብራታ መቀበል') የሚባል ስርአት ይደረጋል፡፡ ይህም 'የማጽናኛ ቃል መቀበል' የሚል አቻ ፍች አለው፡፡ *የሰብረታ አዕማ* ስርአት ሳይፈጸም ህዝብ አይለናበትም፡፡ የሰብራታ አፈጻጸም ሲከናወን፣ የሟች ወንድም ወይም ታላቅ ልጅ ወይም ልጁ በእድሜ ለጋ ቢሆን ከሟች ወንድም ጋር አብሮ በህዝቡ ፊት በመቆም ህዝቡን ሲያለናብት ህዝቡም የማጽናኛ ቃል አንድ ላይ ይናገራል፡፡ ምልልሱም በተከታዩ መልክ ይሆናል፡፡

የሟች ወንድም ወይም ልጁ ----- *ዋሚተኮኦኮ ዋሞካ ሆገኮቴ*
Waamitakko'ookko
waamma hooggakkotte
"ቀብራችኋልና ቀባሪ አትጡ"
ብሎ ሲናገር፣

ህዝቡ ------- *ዋዕ ሰብራታ ኡዎና*
Waa'i sabiraatta uwwona
"እግዚአብሄር ያጽናችሁ"
ብሎ አንድ ላይ ይመልሳል፡፡

ከቀብር ስነስርአቱ ዘግይቶ ለቅሶውን የሚመጣ ሰውም ለቅሶውን ደርሶ ሲወጣ የማጽናኛ ቃል በመናገር ይሆናል፡፡ የማጽናኛ ቃሉም በተከታዩ ቅርጽ የሚነገር ይሆናል፡፡

| | |
|---|---|
| *ተናጋሪው* (ለቅሶ ደራሽ) | ዮንተኬዕ መንና ዋዕ ሰብራታ ኡዎና<br>Yoontakke'i maninnaa waa'i sabiraatta uwwona<br>"ያላችሁትን እግዚአብሄር ያጽናችሁ"<br><br>ሌሂ ስጐና<br>Lehi siggona<br>"ሞት ይቀዝቅዝ"<br><br>ሊረመትና ኤደሞና<br>Liirammattina edammona<br>"ደስታ ያገናኘን" |
| *ምላሽ* (የሟች ቤተሰብ) | ጆራ አፈኮቴ<br>Jora affakkotte<br>"ክፉ አይድረስባችሁ" |

ህዝቡ እንደተሸኘ ቤተዘመድ እና ጐረቤት የሚሆን ለቅሶው ሰፈር ይቀርና ያስተዛዝናል። ይህም የሚደረገው ከሰላሳ ቀናት ላልተናነሰ ጊዜ ይሆናል። ይህ በሰቅሶ ቤት በቤተዘመድና በጐረቤት የሚደረግ የማጽናኛ ወይም የማስተዛዘኛ ስርአት *በካራ* /bakkaara/ ተብሎ ይታወቃል።

ከቀብር ስነስርአት በሁዋላ የሀዘኑ ስርአት የሚደመደመው ከአንድ አመት በኋላ *ጋባ ፍስማ* /gaabba fissimma/ ወይም *ቦሃ ፍስማ* /Boha fissimma/ (የሀዘን ማንሻ) ተብሎ በሚታወቅ ስነስርአት አፈጻጸም ውስጥ በማለፍ ነው። ስርአቱ የሚፈጸመው፣ ከአንድ እስከ አራት የሚደርሱ በሬዎችን በማረድ፣ ጠጅ እና ጠላ በማዘጋጀት ለቤተዘመድ ጥሪ ወይም ግብዣ በማድረግ ነው። ከዚህ ስርአት በተጨማሪ የሟች





ዘሮች እስከ ሶስት አመት ድረስ በየአመቱ እየተሰባሰቡ ቀንዷን ወደ ጐን ከፊት እና ከብብ ያደረገች ላም ገዝተው ያርዳሉ። የቀንዱ ቅርጽ ወደጐን ሰፋ ማለት የሚያመስከተው የሟች ዘር እንዲስፋፋ መሻትን ነው። በሌላ በኩል የሚታረደው ላም የመልክ ምርጫ ነጭ፣ ዳለቻ ወይም ቀይ ከመሆን ውጭ ጥቁር[104] አይሆንም። ከታረደው ስጋ ተበልቶ የሚተርፍ ቢኖር እንኳን ለሟች ተብሎ የተዘጋጀ በመሆኑ ወደ ቤት አይወሰድም።

በአጠቃላይ በሀዲያ ባህል የለቅሶ እና የሀዘን ስነስርአት ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ውስጥ እየቀሩ ወይም እየተለወጡ የመጡ ባህላዊ ገጽታዎች አሉ። ከነዚህም በመቃብር ላይ የሚደረግ ውትትና ደም መርጨት፣ ፊት መንጨትና ደም ማፍሰስ፣ አካላትን መጉዳት እየቀሩ ከመጡ ባህላዊ ገጽታዎች እንደምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። በአንጻሩ እስከ ዛሬ ቀጥሰው ካሉት ስርአቶች ለሟች የሚደረግ ሰፊ የሀዘን ስነስርአት (ቢያንስ እስከ አንድ ወር የሚደረግ *በካራ*) እና ሰፊ ድግስ ደግሶ ብዙዎችን ማስተናገድ በማህበረሰቡ ኢኮኖሚና ጊዜ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ አይቀሬ ነው። እንዲህ አይነቱ ስርአት በቀጣዩ የሟች ቤተሰብ ኑሮ ወይም መተዳደሪያቸው ላይ የሚያሳርፈው ጠባሳ የሚናቅ አይደለም። በተጨማሪም ሰፊ ጊዜን በሀዘን ስነስርአቱ ማሳለፍ ቀጣዩ ትውልድ ለጊዜ ውድነት የሚኖረው እሳቤ እንዲወርድና ዳተኛ እንዲሆን ማድረጉም ሊያሳስብ የሚገባ ጉዳይ ነው። መጪዉ ትውልድ የሚመሰረተው በዛሬው ማህበረሰብ የእሴት ስርአት /value system/ ላይ ነውና።

[104] በሀዲያ ባህል ብዙ ጊዜ ጥቁር የመጥፎ አጋጣሚ ወይም ነገር ምሳሌ ነዉ። በመሆኑም ለሟች ቤተሰብ /ለተተኪ ትዉልድ/ ብሩህ ነገ '/bright future/'ን ለመመኘት ጥቁር ያልሆነ ወይም ፊካ ያለ ቀለም በባህሉ ተመራጭነት አለዉ።

# ክፍል 6፤ ቃላዊ ሀብቶችና ጨዋታዎች

የሀዲያ ብሄረሰብ ታሪኩን፣ እምነቱን፣ ባህሉንና የተለያዩ ወጉቹን ቀጣይነት ባለው መልኩ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሻገር የሚጠቀምባቸው የስነ ቃል አይነቶች አሉት። ከነዚህ የስነቃል አይነቶች አንዳንዶቹን ለመዝናኛ ፋይዳ፣ አንዳንዶቹን ደግሞ የስነምግባር ማስተማሪያ፣ የጠማማ ነገር ማረቂያ፣ የጀግንነትና የማንነት መግለጫ አድርገው ይጠቀማሉ። ከቃላዊ ትውፊቶች ተከታዮቹን እንደምሳሌ ማንሳት ይቻላል፤ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ እንቆቅልሽ፣ ተረት፣ ለቦ፣ ሸርማ፣ ድራንቻ እና የመሳሰሉት በቃላዊ ቅርጽ የሚነገሩ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ በግጥማዊ ቅርጽ የሚነገሩ ሲሆን አንዳንዶቹ ለምሳሌ፣ እንደ ተረት ያሉት በዝርው መልክ ይነገራሉ። ከዚህ በመቀጠል በቃላዊ ቅርጽ ከሚነገሩት የሀዲያ ህዝብ ትውፊቶች አንዳንዶቹን ወይም ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

## 6.1. *ሸርማ*

*ሸርማ /Sharimma/*፡ ወጣት ወንዶች እና ወጣት ሴቶች በገበያ፣ በሰርግ ቦታ፣ በግርዛት ስርአት፣ በበኣላት እና በመሳሰሉት አዉዶች በአንደበታቸው የሚወራወሩት ቀልድ ነው። *የሸርማ* የመነገሪያ ቅርጹ ዝርው/prose/ ሳይሆን ግጥማዊ ነው። በአንድ አዉድ ውስጥ እያሉ የሚያፈልቁት፣ በምልልስ መልክ የሚከወን ቃላዊ ግጥም ነው።

*ሸርማ*፡ በወጣቶች ብቻ ሳይሆን በአዋቂዎችም የሚዘወተር መሪር ቀልድ ነው። በዚህ ቀልድ የሚሳተፉ ትልልቆችም ሆኑ ወጣቶች ስለማንኛውም ጉዳይ ሊቀልዱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ክብሬ ተነካ ብሎ ማኩረፍ፣ ወይም መናደድ አይቻልም።





አንዱ ሌላው ላይ ሲቀልድ ታዳሚ ከመሳቅ፣ ከመጫወት ውጭ ለሌላ ነገር የትኛውም ወገን አይነሳሳም። *ሸርማ* ዘር እያነሱ መንቀፍን፣ ማዋረድን ስለሚያካትት አዲስ አድማጭ የሆነ ሰው ከአሁን አሁን ተደባደቡ ብሎ ሊጨነቅ ይችላል። ነገር ግን ማሸነፍ የሚቻለው በአካላዊ ትንቅንቅ ሳይሆን ተገጥሞ በሚወረወር የቃል ግጥም ብቻ ነው። ተራ በተራ በግጥም (በ*ሸርማ*) ሲቀላለድ መልሶ መቀለድ ያልቻለው እንደተሸነፈ ይቆጠራል።

*ሸርማ*፡ ሌላ ገጽታም አለው። ጀግኖች በጦርነት ወይም በአደን ወቅት የሚያደርጉትን ፎከሮ ወይም ሽለላ መውጋትንም የሚያመለክት እሳቤም ሊሆን ይችላል። በዚህ አገባቡ ቀልድ የሚለውን እሳቤ አይወክልም፤ አገልግሎቱ ፉከራ እንደማለት ነዉ። በመቀጠል የሚቀርበው *የሸርማ* ምሳሌ በወጣት ወንዶችና ሴቶች መካከል የሚኖረውን ግጥማዊ ጨዋታ የሚያመለክት ነው። ቀልድ አዘል ግጥሞቹ የተቃራኒውን ወገን ደካማ ጐን ወይም ስስ ብልት በመፈለግ በንግግር መግረፍ ላይ ያነጣጥራል። ይህንን በሚመለክት ተከታዮቹን ምሳሌዎች[105] ይመልከቱ።

| *ካ ካ* | *አንተ ልጅ* |
|---|---|
| ሂምና በገድ ቤዕ ጆራ<br>Hiimina bagad bee'i jor | ለምሽት ጦር የሌለህ |
| ሀጥና ጆጆር ቤዕ ጆራ<br>Hixina jajar bee'i jor | ለሳር ማጭደ የሌለህ |
| ሀቅና ሜሳን ቤዕ ጆራ<br>Haqqina meesaan bee'i jor | ለእንጨት ጠገራ የሌለህ |
| ገቴና ጀገር ቤዕ ጆራ<br>Gatteena jagar bee'i jor | ለማዳሪያ ጐጆ የሌለህ |

[105] ሀይሌ ቴጻሞ እና ግርማ ሱልዶዕሶ (2006፣237-267)

| | |
|---|---|
| ጨዕም አሌና ጤፎዕ ቤዕ ጆራ<br>Ca'mmaa'lleena xeffo'i bee'i jor | ልትቀምስ ቁራጭ የሌለህ |
| አባዕ ለንድቾኔ<br>Aba'i landichchonne | ከአባባ ልጅ ጋር |
| ኢንኔ መይቶላ! ዮሞ<br>Iinninne mayyitoolla yoommo | ከኔ ጋር ምን እያልክ ነው!<br>እላለሁ |

የዚህ ግጥም መልእክቱ ለወደፊት ህይወት የኑሮ እቅድ የሌለውን ፈዛዛ ወንድን መውቀሻ ነው፡፡ አንድ ሰው ኑሮዉን ለማሸነፍ ማድረግ የሚገባውን የእለት ከእለት ተግባር ማከናወኛ መሳሪያዎች፣ማጭድና ጠገራ እንኳን የሌለዉ ፈዛዛ ወንድ መሆኑን አንስታ፤ ሌላው ቀርቶ ራሱን የሚከላከልበት ጦር፣ ለማኖሪያ ደግሞ የራስ ጐጆ የለሽ መሆኑን በመጥቀስ ቀልድ መሳይ ስድቧን ስትሰድበዉ እሱም በበኩሉ ተከታዩን ምላሽ በግጥም ይሰነዝራል፡፡

| *ታ ታ* | *አንቺ ልጅ* |
|---|---|
| ለኡቤእ ክያን<br>La'u bee'i kiyyann | ያላወቀ አባትሽ |
| ለሮ አላሲሶኮ<br>Laro allaasiisookko | ከብት ያላግድሻል |
| ለቆ ቤዕ ክዩማ<br>Laqqo'i bee'i kiyyumma | ያላወቀች እናትሽ |
| ሊትማ ሊትሰሞ<br>Liitimma liitissammo | ወፍጮ ታስፈጫለች |
| ለቆዕኔ ኣል ሉዊ<br>Laqqoo'nn aa'll luww | ባለማስተዋል የወሰድሽው ነገር |
| ሉጡንጣ ተኮኮ<br>Luxuunxa takkookko | ድንገት ያመልጥሻል |

ግጥሙ የልጅቷን ፈዛዛነት፣ ዝንጉነቷንና ሞኝነቷን ለመግለጽ የተገጠመ ሲሆን ልጅቱ አስተዋይ አለመሆኗን ከመግለጹ በላይ እንደሴትነቷ የሚጠበቅባትን ሀላፊነት ለመውሰድ ወይም ለመወጣት እንደማትችል የሚያጋልጥ ነው፡፡





በሌላ በኩል አንዲት ለትዳር ጓደኝነት የተጠየቀች ልጅ፣ የጠያቂዋን በእድሜ ከሷ ጋር አለመመጣጠኑን ለመግለጽ ስትፈልግ 'እኩያህን ፈልግ' የማለት አይነት ምላሽዋን በተከታዩ ግጥም ታቀርባለች፡፡

| *ካ ካ* | *አንተ ልጅ* |
|---|---|
| አቦኣም ኦሶ<br>Abo'aam ooso | ሽበታም ልጆችን |
| አቶረሴና<br>Atoorasseena | ለጫዉታቸው |
| አኖኦ ያ<br>Anno'o yaa | አባቶች ናቸው ብዬ |
| አረቃ በዶሞ<br>Araqa baddoommo | እጅግ እፈራለሁ |

ይህንን ነቀፌታ የሰማ ጠያቂ ዝም ብሎ አያልፍም፡፡ እሱም በበኩሉ በተከታዩ ግጥም ምላሽ ይሰጣል፡፡

| *ታ ታ* | *አንቺ ልጅ* |
|---|---|
| አኑናም ለንዳ<br>Anuunam landa | ጡታም ልጃገረዶችን |
| አሞኦ ያ<br>Amo'oo yaa | እናቶች ናቸው ብዬ |
| አመድምና<br>Amadimmina | ጓደኛ ሳደርግ |
| አረቃ በዶሞ<br>Araqa baddoommo | እጅግ እፈራለሁ |

የዚህ ግጥማዊ ምላሽ መልዕክቱ፣ የልጅቱ አካላዊ ቅርጿ ከኮረዳነት ደረጃ አልፎ የእናትነት ቅርጽ እንደያዘ እና የሚስብ ተክለ-ሰውነት እንደሌላት መግለጽ ነው፡፡

ሸርማ ላይ ሁልጊዜ ነቀፌታ ላይኖር ይችላል። ወንድ ልጁ በሴቷ መልክ ሲማረክ ለአካላዊ ቅርጿ አድናቆትን ሲቸር ይችላል። ሆኖም ሴቷ በሱ አቋም ከልተማረከች የግድ የውዳሴ ግጥም አትቸረውም። ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ ሁለት ግጥሞች ቀጥለው ቀርበዋል።

| *ታ ላንዶ ላንዶ* | *አንቺ ልጅ አንቺ ልጅ* |
|---|---|
| ኪክ ኢነ ምሺሶኮክ<br>Kiikk iina mishisookkok | ያንቺ የምያምረኝ |
| ቆቦአ ለቦ ዱፋ<br>Qobbo'o laboo duufa | ጉሎ መሳይ ባትሽ |
| ቆማ ለቦ አኑና<br>Qooma laboo anuuna | ቅል መሳይ ጡቶችሽ |
| ቆላ ሞኦ እሌ<br>Qolaa mo'oo illee | በቆረጣ የሚያዩ አይኖችሽ |
| መቅሬ ሆንሱምተኔ<br>Maqire honsummita'inne | አብረን ብንወል |
| ቁሉጢሶላ<br>Quluxisoolla | ልቤ ይከጅላል |

| *ካቤቶ* | *አንተ ልጅ* |
|---|---|
| ሀጁ ዌንጌሬላ<br>Hajju wengeereella | ኮስማና ቀበሮን |
| ሆጉ ሎመን ጋዋ<br>Hoogu lommann gaawwa | የሽማግሌ ጋያን |
| ሀገይ ሊሳን ጐጐ<br>Hagay liisaa'nn googo | የክረምት የሊሳና መንገድን |
| ሁንደም ለቦ ጆራ ዮሞ<br>Hundam laboo joraa yoommo | ሁሉንም መሳይ አስቀያሚ ነህ እልሃለሁ። |

የልጅቷን ውበት አድንቆ ልቧን ሊረታ ያሰበ ወጣት ሳይሳካለት ቢቀር ዝም ብሎ አያልፋትም፤ ክፍ ሲል ለተሰነዘረበት ነቀፋ ተከታዩን ግጥም ይወረውራል።





| *ታ ታ* | *አንቺ ልጅ* |
|---|---|
| ሀቡስዕን ግብራ እትች<br>Habusi'nn gibira ittichch | እንደ ጂኒ ግብር በል |
| ሄዶርዕን ቁንቁናም ጐደብ<br>Heedoorri'nn qunqunaam godab | እንደጅግራ ሆድሽ ቅንቅናም |
| ሀመሽችዕን ቁጳም አለብ<br>Hamashshi'nn quphaam alab | እንደ እባብ ለንኮፋም ምላስ |
| ሂንጫኮታዕኔ ሂሞ ገስቶዮ<br>Hincakko'itai'nn hiimo gassitooyyo | ቢጠጉሽ አንድ ሌሊት አታሳድሪም |

ክፍ ሲል የፍቅር ጥያቄ ለቀረበላት ልጅ ተናጋሪው ውጫዊ መልኳን አይቶ ያሞገሳት ሴት በመለሰችዉ ምላሽ መማረሩን ይገልጻል። በሰውነት ውስጥ ተቀርቅሮ እንደሚቀር ለንኮፍ ወይም መርዝ የምላስዋ ሀይለኛነት እንዳንገፈገፈዉ እና ቢጠጓት ወይም አብረዋት ለመኖር ቢጀምሩ የማታሳርፍ ነገረኛ እንደሆነች መልሶ መተንፈሱን ይገልጻል።

አንድ መልክቀና ወጣት ከሴት ልጅ ጋር ሲወቃቀስ፣ ሴት ልጅ የወንድዬው ተክለ ሰውነት እንከን የማይወጣለት መልከመልካም መሆኑን በማመን፣ ነገር ግን በስራ ትጋቱ የሚታማ፣ ሰነፍ መሆኑን በማንሳት ደካማ ጐኑን በተከታዩ ግጥም ወጋ ታደርጋለች።

| *ካካ* | *አንተ ልጅ* |
|---|---|
| ሁኩ ዱፋዮ<br>Hukku duufayyo | በወፍራም ባት ሳይሆን |
| ሆክ ኡሊቸዮ<br>Hokk uullichchayyo | ቀጥ ባለ ቁመና ሳይሆን |
| ሆንጐር ቆጫዮ<br>Hongoor qooccayyo | በዘንካታ ተፈጥሮ ሳይሆን |
| ሀማዕ ደኖዮ<br>Haama'i danoyyo | በደማም ቁንጅና ሳይሆን |
| ሀገይ በጦኔ<br>Hagayy baxonne | በክረምት ስራ |

| | |
|---|---|
| *ሀምሌኤኔ ሀመኮአኮ*<br>Hamile'enne hamakkokk | በሀምሌ ታምተሃል |
| ሄዱዋ ኣዕላ ሄሽታ ኮርቼ<br>Heedduwwa aa'lla heeshitta korche | መጥረቢያህን አንስተህ<br>አርፈህ ቆፍር |
| ዮሞ<br>Yoommo | እልሃለሁ |

የሀምሌ ወር በተለይ ለወንዶች ብርቱ ስራ የሚጠብቃቸው የዘር ወቅት ነው። ያንን የዘር ወቅት በአግባቡ ያልተጠቀመ ቤተሰብ በቀጣዩ አመት ከረሃብ ሊያመልጥ አይችልም። በግጥሙ የተነሳው ወጣት፣ መልኩን አሳምሮ የሚሄድ እና ስራ የማይወድ በመሆኑ በሴቷ ተብጠልጥሏል፤ ለዚህም ነው መልክ ብቻ አሳምረህ አትኑር፤ መጥረቢያህን አንስተህ አርፈህ ቆፍር የሚል መልእክት ያስተላለፈችለት።

በአጠቃላይ *ሽርማ* በጨዋታ መልክ አንዱ ሌላውን መስደብ፣ ማናደድ፣ መተቸት ወይም አንዱ በሌላ ላይ መቀለድን የሚያሳይ ቢሆንም፤ በሌላ ገጽታው *የሽርማ* ፋይዳ በባህሉ ተቀባይነት የሌላቸውን ስነምግባሮችን (ለምሳሌ፣ ስራፈትነትን) የሚያወግዝ በመሆኑ አንድ ሰው እንደ ማህበር አባልነቱ ሊኖረው የሚገባውን መልካም ስነምግባር እንዳይጥል የማድረግ አስተዋጽኦ አለው ማለት ይቻላል።

## 6.2. *ድራንቻ*

*ድራንቻ /Diraanchcha/*፣ የአንድ ሰዉ የጀግንነት ተግባር፣ ሀብት፣ ስኬት፣ ጉብዝና፣ ችሎታና ማህበራዊ ቦታ የሚነገርበት ግጥማዊ ዜማ ነዉ። ይህም ብዙ ጊዜ የሚዘወተረዉ አመሻሽ ላይ እንደ ጊዜ ማሳለፊያ በመጠቀም ሲሆን፣ በዚያዉ ወላጆች ለልጆቻቸዉ የዘር ሀረጋቸዉን አመጣጥ ለማስጨበጥ ተብሎ ነዉ። በተጨማሪም አባቶች *ለይዳራ* /Aydaara/ ወይም ቦርዴ ሲጠጡ ድራንቻን ያዘወትራሉ።





በሀዲያ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ ያለዉ ሰዉ ሲሞት፣ በለቅሶ ስነስርአቱ ያደረጋቸዉ ስራዎችና ለህዝቡ ያበረከተዉ አስተዋጽኦ እየተዘረዘረ ይነገራል፤ ይወደሳልም። ከዚህ በተጨማሪም ሀዲያዎች በስርግና በሌሎች በአላት እና አጋጣሚዎች በድራንቻ ስሜታቸዉን መግለጻቸዉ የተለመደ ነዉ። *ድራንቻ* በህይወት ያጋጠመን ሀዘንና ደስታን መንገሪያ ነዉ፤ በተጨማሪም ጀግና አባቶች የሚሞገሱበት ቃላዊ ቅርጽ ነዉ። በሌላ በኩል *ድራንቻ*፣ ሰዎች ከአንዳች ችግር የወጡበትን መንገድ ለተከታይ ትዉልዳቸዉ ማሳወቂያም ነዉ። ረሃብ የነበረበት ዘመንና የባህሉ አባላት ለከብቶቻቸዉ የግጦሽ መሬት ፍለጋ የተንከራተቱበት ወቅትም ሳይሸሽግ በግጥማዊ ቅርጹ (በድራንቻ) ይነገራል። ድራንቻ፣ በመልካም ዘመንም እንዲሁ የነበሩበት የእርካታ ስሜት ማንጸባረቂያም ነዉ።

ምሳሌ፣

| *ሄለም ሀዲያ*[106] | *የደላዉ ሀዲያ* |
|---|---|
| ዋዳ ሀቅ ጪማ<br>Waaddaa haqqi ciimaa | በረግረግ ሳሮችና በጥቅጥቅ ደኖች |
| ዋጮእ ግራራ<br>Waaco'i giraarii | ባለብዙ ቅርንጫፍ ግራር |
| ወዕሙኬሚ... ገባባ<br>Wo'imukkemee..yii...Gabaaba | የሞላበት ገባባ |
| አዳሜሚ... ደርባኣ<br>Adaamemee...yii...darba'a | የወተት ላሞችን አሰማርቶ |
| ኦርዴኤሚ መገራ<br>Orde'emee...yii... magara | የኦርዴ ግርጌ |
| ኦሌኤሚ ባል ጩባ<br>Ole'emee...yii...baalli cebba | የኦሌ ሸለቆ |
| ኦዶኦሚ ሶእል ኡላ<br>Odo'emee...yii... soo'll uulla | የተቀረዉ የሶሮ አካባቢ |
| ኣጥ ባደዋቾ<br>Aaxxi badawwaachcho | ባደዋቾ የሀዲያ ደቡባዊ ክፍል |

106 Braukamper, Ulrich and Tilahun Mishago (1999:41).

| | |
|---|---|
| ኤሉዊሜ ባዶጎ<br>Eeluwwemee…yii…Baadoogo | አጠቃላይ ባዶጎ |
| ሸሻምሜ ሻሾጎ<br>Shashaamemee…yii…shaashoogo | ባለቁጤማ ሻሾጎ |
| ሹይ ሀመሽቾ<br>Shuuyyi hamashshichcho | ራጅሙ ሀመሽቾ |
| ሻር ቤኤሚ ወንጀላ<br>Shaar bee'emee…yii…wonjalaa | ስጥ ያለዉ ወንጀላ |
| ሀጣሜሚ ቃላኣ<br>Hixaamemee…yii…qaala'aa | ባለብዙ ሳር ቆላ |
| ሃራራሜ ሰንጌኤ<br>Haraaremee…yii…qaala'aa | ሰፊዉ የሰንጌ ሜዳ |
| ሀቅ ቦሾአና<br>Haqqi Boosho'annaa | ባለ ብዙ ዛፍ ቦሾአና |
| ሃባሜሚ ሞቾሶ<br>Haabaamemee…yii…moochchooso | በሚያምር ሞቾሶ ዉስጥ |
| ሃብቼሚ ደቀዩ<br>Habichchemee…yii…daqayye | እና የሀብቾ ሜዳ |
| ሆሱኬሚ ለእሌካ<br>Hosukkemee…yii…la'lleka | የተሰማሩትን ከብቶች |
| ሀምባሞሜ አጋቴ<br>Himbaamomee…yii…agaate | ትኩስ ወተት ጠጥቶ |
| ሄላሜሚ ሀዲያ<br>Heellammemee…yii…hadiyya<br>ሄላሜሚ ሀዲያ | የደላዉ ሀዲያ ረክቶ ተደስቷል |

ከፍ ሲል በቀረበዉ አጭር ድራንቻ ዉስጥ ተናጋሪዉ የሀዲያን አካባቢዎች የመልከአ ምድራዊ አቀማመጡን ገጽታ ዉበት በማድነቅ፣ የከብቶቹ መሰማሪያና ከከብቶቹ የሚገኘዉን ምርት ትሩፋትን የሚዘረዝርበት ብሎም የህዝቡን የእርካታ ዘመን ገላጭ ነዉ።

## 6.3. ግጦኦ

በሀዲያ ባህል ግጥም የከፍተኛ ስሜቶች መግለጫ ነዉ፤ ደስታ፣ ሀዘን፣ እልህ፣ ቁጣ፣ ፍቅር፣ ነቀፋና ዉዳሴ በግጥም ይገለጻሉ። ግጥም፣ በሀዲይሳ ግጦኦ /Gixo'o/ ተብሎ የሚጠራ





በአጠቃላይ በሀዲያ ታሪክ ታዋቂ ከሆኑት ገራዶች መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

አሸዕን ገራዳ (Asha'n Garaada)

ገደጵ ገራዳ (Gada'phph Garaada)

ወላጵ ገራዳ (Wola'phph Garaada)

ጉዶል ገራዳ (Gudoolla Garaada)

ቀቤዕን ገራዳ (Qabbee'n Garaada)

ዲደዕ ገራዳ (Diida'i Garaada)

ሰገዕ ገራዳ (Soga'i Garaada)

ጐጋል ገራዳ (Gogaal Garaada)

ዲሆዕ ገራዳ (Diiho'i Garaada)

ሀላጵ ገራዳ (Halaaphph Garaada)

ገንዝ ገራዳ (Ganz Garaada)

ሀደቦ ገራዳ (Hadaboo Garaada)

ሀዱዕም ገራድ (Hadu'm Garaada)

ሀገዕ ገራድ (Haga'i Garaada)

## 2.8. የሀዲያ ብሄር የኢኮኖሚ ሁኔታ ዳሰሳ እስከ 1974 ዓ.ም.

የሀዲያ ብሄር በረጅም ታሪኩ በኢኮኖሚ አንጻር ቅይጥ ግብርና ይጠቀም እንደነበረ የተለያዩ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ። ብራውከምፔር እና ጥላሁን (1999:24) የሀዲያን ትውፊታዊ ማስረጃዎች በመጠቀም ስለ ሀዲያ ኢኮኖሚ ሲያብራሩ፣

ሲያብራሩ፣ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ሀዲያ በሁለት እንቅስቃሴዎች የተመሰረተ ኢኮኖሚ ነበረው። እነዚህም የከብት እርባታና የገብስ እርሻ ናቸው። በመሆኑም የሀዲያ ህዝብ በእርሻ ስራ ለረጅም ዘመናት ቢሳተፍም እንደ ዋነኛ ምርት ግን ትኩረት ሰጥቶ ይሰራ የነበረው በገብስ እርሻ ብቻ ነበረ። ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በኂላ ባሉት ዘመናት ግን ከገብስ እርሻ በተጨማሪ ሴሎችንም የእርሻ ምርቶች ማምረት መልመዳቸው ይነገራል።

በተሰይም ለረጅም አመታት የቀጠለው አንጻራዊ ሰላም በአንድ አካባቢ ተረጋግተው እንዲቀመጡ ማስቻሉ ተጨማሪ የእርሻ ሥራዎችን እንዲለምዱ ካስቻሉ ምክንያቶች አንዱ ሲሆን እንደሚችል ይገመታል። ከዚህ ውጪ ግን የሀዲያም ሆነ ሌሎች የአካባቢው ህዝቦች ቁጥር እየጨመረ መሄድ ሰፊ የግጦሽ መሬት እየተጣበበ እንዲመጣ ማድረጉና በእንስሳት ሀብት ላይ በተለያዩ ወቅቶች የሚከሰቱ በሽታዎች የሀብቱን ብቸኛ አስተማማኝነት ጥያቄ ውስጥ መከተታቸው ለአዳዲስ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ዕድል ፈጥረዋል።

በሀዲያ ህዝብ ረጅም ታሪክ በተለይም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በነበሩት አጠቃላይ ዘመናት የበርካታ ከብት ባለቤትነት የሀብት መገለጫ ብቻ ሳይሆን ለባለቤቱ ክብርና ማዕረግ የማስጠት ማህበራዊ ፋይዳ ነበረው። ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ከብትን የሀብትና የማህበራዊ ቦታ መገለጫ አድርጎ መጠቀም በአሁኑ ወቅት በተወሰኑ የሶሮ /sooro/ እና የባዶጎ /Baadoogo/ አካባቢዎች መቀጠል ችሏል።

ከዚህ አንጻር በሀዲያ ልጅ ሲወለድ፣ በተለይም ወንድ ልጅ ከሆ፦ ከብት የሀብትና የክብር ፋይዳ እንዳለው ቀስ በቀስ





ማህበረሰቡ በአጠቃላይና ወላጆች በተለይ ያስተምራሉ። በመሆኑም ለከብት ተገቢውን ዋጋ በመስጠትና ወደፊት የብዙ ከብት ባለቤት ለመሆን በመመኘት እንዲያድግ ይደረጋል። ይህ ማህበረሰቡ የሚሰጠው ተመሳሳይ ትምህርት ወንድ ልጅ ከተወሰነ እድሜ በኂላ ለሚያጋጥመው ትዳርና ራሱን ችሎ ለመኖር ከህጻንነት ጀምሮ እንዲዘጋጅ በማድረግ የነጻነት / independence/ መንፈስ እንዲያዳብር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ከማስተማሪያ መንገዶች ዋነኛው በኦሽቾ (ooshshichcho) ማለትም በህጻንነት እድሜና በቤትቾ /beetichcho/ ለወንድ እና ለንድቼ /landichchee/ ለሴት ዕድሜ፣ ማለትም በልጅነት ዕድሜ መካከል ለሚገኙት ልጆች በቤተሰብ መሰረታዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች አቅማቸው በፈቀደ መጠን ለሚያደርጉት ተሳትፎ በምርት ወቅት እንደማበረታቻ የሚሰጣቸው ሽልማት ወይንም ስጦታን መነሻ በማድረግ እያባዙ በወጣትነት ዕድሜ የከብት ባለቤት የሚሆኑበት እድል መፍጠር ነው። ለምሳሌ፣ እህል በሚሰበሰብበት ወቅት ለልጆች ተሳትፎ ወላጆችና ማንኛውም የመንደሩ ሰው ፎጮኦ /Foocco'o/ ወይም ትንሽ ከእህሉ በሁለት እጃቸው እየዘገኑ ልጆቹ መሸከም በሚችሉት እቃ ወይም በሰበሱት ልብስ ይሰጣቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ በአውድማ ሆን ተብሎ እንዲተርፍ የተደረገውንም እህል ልጆች አበራይተውና አዘጋጅተው እንዲከፋፍሉ ይፈቀድላቸዋል። ለዚህ ለፎጮኦ በሚያደርጉት ጥረት እግረ-መንገዳቸውን የእርሻ ስራ ይማራሉ።

የፎጮኦን ስጦታ፣ ልጆች ለቤተሰብ ፍጆታ አገልግሎት እንዲሰጡ የማይጠየቁ ሲሆን እህሉን በመሸጥ አብዛኛውን

ጊዜ ሴት ዶሮ ገዝተው እንዲያረቡ ወላጆች ይመክሯቸዋል። ዶሮዎችን እቤት ውስጥ ከሚጣል እህልና እንክርዳድ በመቀሰብና በማስፈልፈል በርከት ያሉ ዶሮዎች ባለቤት ይሆናሉ። እነዚህ ዶሮዎች ለገበያ ቀርበው ጥሩ ገቢ ማስገኘት የሚችሉበት ዕድሜ ሲደርሱ በመሸጥ በጎችን ወይንም ፍየሎችን እንዲገዙ ይደረጋሉ። የተገዙትን በጎች ወይም ፍየሎች ልጆች ከራሳቸው እኩል ስለሚንከባከቧቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ተባዝተው ይሸጡና ጥጃ /Wee'ichcho/ እንዲገዙ ይደረጋል። በዚህ ሂደት ልጆች የንብረት ባለቤት በመሆን ለወደፊት ህይወታቸውና ለሃላፊነት እራሳቸውን እንዲያዘጋጁም ይበረታታሉ።

በሀዲያ የአንድ ግለሰብ የከብት ብዛት እያንዳንዱን ከብት በመቁጠር በተደረሰ ሙሉ ቁጥር አይነገርም። ይልቁንም የተለያየ ብዛት ያላቸውን የከብት ስብስቦች ታሳቢ በማድረግ የከብት ብዛትን የሚወክል አራት የተለያዩ መጠሪያዎችን ይጠቀማሉ። እስከ 20 ከብት አንድ ግለሰብ ሲኖረው ይህ በጥቅሉ *ፎርገሳ* /Foorgassa/ ተብሎ ይጠራል። እስከ 80 ከብት አንድ ግለሰብ ሲያረባ የግለሰቡ የከብቶች ብዛት በጥቅሉ *ጉበንታ* /Gubanatta/ ተብሎ ይጠራል። የአንድ ግለሰብ እስከ 100 የሚደርሱ ከብቶች በጥቅሉ *ጥቤ* /Xibbe/ የሚል መጠሪያ ይሰጣቸዋል። እስከ 1000 ለሚደርሱ ከብቶች አንድ ግለሰብ ባለቤት ከሆነ፣ ከብቶቹ በጥቅሉ *ኩማ* /Kuma/ ተብሎ ይጠራል።

የአንድ ግለሰብ የከብቶች ብዛት ሁለቱን ከፍተኛ ቁጥሮች/ ጥቤና ኩማ/ ሲደርሱ በሀዲያ ህዝብ ባህል የግለሰቡን ደረጃ ለማክበርና የክብር ማዕረግ ለመስጠት የሚያስችል ባህላዊ ስነ ስርአት ይደረጋል። ይህ ባህላዊ ስነ ስርአት *ወገና* /Wogana/





ተብሎ ይጠራል። *ወገና* የሚለዉ ቃል በጥሬ ትርጉሙ[43] በከብቶች ላይ በስነ-ስረአቱ ወቅት የሚረጨዉን በማርና በወተት የተበጠበጠ ዉሃን የመርጨትን ስነ-ስርአት ያመለክታል።

የወገና /Wogana/ *ሥነ ሥርዓት* የሚካሄድበትን መሠረታዊ ምክንያት የሀዲያ ሽማግሌዎች ሲያስረዱ፤ አንድ ግለሰብ መቶና ከዚያም በላይ የሆኑ ከብቶች አርብቶ ለማስቆጠር በርካታ የሆነ ፈተናዎችን ማለፍ የሚያስችል ልበሙሉነት፣ ቁርጠኝነትና ጽናት እንዲኖረው ይጠበቃል። ከዚህም በተጨማሪ ለከብቶች ግጦሽና ውሃ ፍለጋ ወቅትን ጠብቆ ወደተለያዩ ቦታዎች መዘዋወር ይጠበቅበታል።

የቤት እንስሳትን በተለይም ከብቶችን ይዞ ቋሚ የመኖሪያ አካባቢን በጊዜያዊነት በመልቀቅ ግጦሽና ውሃ ወደሚገኝበት ሩቅ አካባቢ የሚደረገው ጊዜያዊ ስደት /ጉዞ/ ደርበኣ /Darba'a/ ተብሎ ይጠራል። ከዚህ አስተሳሰብ የተነሳ መቶና ከዚያም በላይ ከብቶች በገንዘብ ከገበያ በመግዛት ወይም በሌሎች ከልፋት ነጻ በሆኑ መንገዶች ባለቤት በመሆን የወገና *ሥነ ሥርዓት* እንዲደረግና ተገቢውን ማዕረግ እንዲሰጥ መጠየቅ በሀዲያ ህዝብ ዘንድ እንደ ነውር ይቆጠራል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የሶሮ ባለባቶች የሆኑት ግራዝማች ሃይሌና ቀኛዝማች ቅንጣሞ[44] ምንም እንኳን ከመቶ በላይ ከብቶች ባለቤት መሆን ቢችሉም ባለቤትነቱ ከከብቶች ጋር ተንከራተው፣ አርብተውና የተለያዩ ፈተናዎችን አልፈው ያገኙ ስላልነበረ ባለመቶ ከብት ወይም ጥባሞ /Xibbaamo/ መባል ቢፈልጉም፣ የሀዲያ ሴራ /Seera/ ነፍጓቸዋል።

[43] ይህን ትርጉም የነገረን ዘነበ ዮሃንስ ካንዲዶ ነዉ።

[44] ይህንን አስተያየት የሰጡት የግራዝማች ሃይሌ ልጅ የሆኑት የተከበሩ አቶ ጌታቸዉ ሃይሌ ናቸዉ።

ለወገና /Wogana/ *ሥነ ሥርዓት* ወይንም ከመቶ /Xibba/ ጀምሮ የከብት ሀብትን ለማስቆጠር አቅም የፈጠረ የሀዲያ ከብት አርቢ ለሥነ ሥርዓቱ ከሁለት ዓመታት በፊት ጀምሮ አቅዶ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅበታል። በዚህ ከሁለት ዓመታት በላይ የሚፈጀው የዝግጅት ጊዜ ለወገና ሥነ ሥርዓት የሚያስፈልጉ ነገሮች ለምሳሌ፤ ቅቤ፣ማር፣ ለእርድ የሚሆኑ በሬዎች፣ ለሥነ ሥርዓቱ የሚሆኑ አዳዲስ ቤቶችና ድንኳኖች ይዘጋጃሉ።

ዝግጅቱ በብቃት ተዘጋጅቶ የሚያበቃበት ጊዜም ተሰልቶ ለወዳጅ ዘመድ የሥነ ሥርዓቱ ማስፈጸሚያ ቀናት ተወስኖ ጥሪ ይተላለፋል። ጥሪ ሲተላለፍ በሥነ ሥርዓቱ ወቅት ወዳጅ ዘመድ ይዞ የሚመጣውን ስጦታ ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜ በመስጠት ይሆናል። የመቶና ከዚያም በላይ ከብት አስቆጣሪው /Woganaancho/ ዘመዶች በምኔ /Mine/ ወይም በሞሎ /Moollo/ ተደራጅተው የተለያየ መጠንና ዓይነት ያለውን የከብት ስጦታና ወጭታ /Wocitaa/ ያዘጋጃሉ።

*በወገና እለት የወገናንቾ* ከብቶች በአጠቃላይ በአንድ *ጋድራ* /Gaadira/ ወይም በረት ውስጥ እንዲሰበሰብ ይደረጋል። የከብቶች ቆጠራ ሥነ ሥርዓት የሚካሄደው ቀድመው የወገናና ሥነ ሥርዓት በመፈጸም የከብት ባለሃብትነትን ክብር ባገኙ የሀዲያ የተከበሩ ሰዎች (*መሃራኖ* /Mahaaraano/) ይሆናል።

ቆጠራው የሚካሄደው በአካባቢው በሚገኘው ትልቅ ወንዝ አጠገብ ሲሆን፣ ለዕለቱ ቆጠራ የሚሆኑ ጤነኛ የሆኑትና ከጥጃ ውጪ የሆኑ በጥሩ አቋም ላይ የሚገኙ አጠቃላይ





ከብቶች በሚቱ ወደ ወንዙ መነዳት ይጀምራሉ። ወደመቁጠሪያ ቦታ ለመሄድ ከብቶቹ እንዲንቀሳቀሱ የባለሀብቱ ከብት የተሰበሰቡበትን *ጋድራ* /Gaadira/ የሚከፍተው *የወገንቾ* ወይም የአስቆጣሪው የመጀመሪያ ልጅ ወይም ዎና /Wona/ ሲሆን፣ ቀድሞ ከጋድራ የወጣውን ከብት ይሸለማል። ከሁሉም ከብቶች በመጨረሻ ከጋድራ የወጣው ከብት ደግሞ የወገናንቾ የመጨረሻው ልጅ ወይም *እልሙቾ* /Ilmuchcho/ እንዲወስደው ይደረጋል።

ከብቶቹ ወደሚቆጠሩበት ወንዝ ሲጓዙ ከከብቶቹ ባለቤቶች መካከል ባል /Aro'o/ በበቅሎ ተቀምጦ ሚስት /Mi'nama/ በፈረስ ተቀምጣ ይንቀሳቀሳሉ። የዕለቱ ሥነ ሥርዓት ታዳሚዎች በጉዞ ወቅት የሚከተለውን ዘፈን እየዘፈኑ ይጓዛሉ።

*መሴሄ አወንሴሄ*

*Massebee Awansebee*

*እየሄድን እየመራችሁን*

በዚህም ለሥነ ሥርዓቱ ያላቸውን ጉጉትና ክብር ይገልጻሉ። ከብቶቸ ተጉዘው ቆጠራው ወደምካሄድበት ወንዝ ሲደርሱ ወደ ወንዙ እንዲገቡና እንዲሻገሩ በማድረግ ለቆጠራው ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

ተቆጥረው መቶና ከዚያ በላይ ወይም ሺህና ከዚያም በላይ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ከብቶቹ ላይ ወተት፣ ማርና ቅቤ ተበጥብጦ ይርከፈከፋል ወይም ይረጫል። እዚያው በከብቶቹ ባለቤት ቁመት ልክ ጉድጓድ ተቆፍሮ ወተት እንዲሞላበት

በማድረግ ግለሰቡ ወተት በተሞላበት ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ እንዲሰምጥ ይደረጋል። በዚህም ወቅት የሀዲያ ህዝብ ምን ያክለ የተትረፈረፈ የእንስሳት ሀብት እንዳለው ለማመልከት የሚከተለው ዘፈን ይዘፈናል። በዘፈኑ ወቅት የግለሰቡ ዘርና ዝና ይሞገሳል።

*ሸንበለለዮኔ*

*Shambalalayyonne*

*የተትረፈረፈ ሀብት ነው!*

በ`ለቱም ለተገኙ ታዳሚዎች *የጨለለቃ* /Calalaqaa/ ደረጃ ወይም በሀዲያ ባህል ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ *ሉባ* /Luba/ ወይም ግብዣ ይቀርባል። ግብዣው በተመሳሳይ ደረጃ ለተከታታይ በርካታ ቀናት ይቀጥላል። የሀዲያ ተዋቂ ባለማዕረጉች ፣ የቀደሙና በከብት ሀብት የክብር ማዕረግ ያገኙ ግለሰቦች፣ የየጉሳው ተጠሪ ሽማግሌዎች አዲሱን የከብት ባለሀብት መርቀው አዲሱን ማዕረግና ማህበራዊ ቦታውን ያጸድቃሉ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ግለሰቡ በከብት ብዛት የደረሰበት ደረጃ የሚያመለክት ተቀጥላ ማዕረግ ከስሙ ጋር አብሮ እንዲጠቀም ይፈቀድለታል። በመሆኑም ባለመቶ ከብት ወይም ባለሽህ ከብት (*ጥባሞ* /Xibbaamoo/ ወይም *ኩማሞ* /Kumaamo/) እንደቅደም ተከተለቸው መለያው እንዲሆን ይደረጋል። ግለሰቡ በህዝቡ ውስጥ በሀብቱ ምክንያት ሊሰጠው የሚገባውን ማህበራዊ ደረጃ ለማመልከት ባሰብዙ ክብር (*መሃራንቾ* /Mahaaraancho/) የሚል ማዕረግ ይሰጠዋል። የማዕረጉን አሰጣጥ አስመልክቶም *ሄቦቶ* /Hebbootto/ የሚል ባህላዊ ጭፈራ ይጨፈራል። የመሃላኖ /Mahaallano/ ማዕረግ አሰጣጥን አስመልክቶ ብራውካምፔሪና ጥላሁን (1999፡ 56) ሲያብራሩ የሚከተለውን ብለዋል።





- ሜንት ሶግተኒ ኡት ኦቲ፣ ለምም መቶ
  Meent sogitanii utti ootii, lamim mato
  "የሴት ምክርና የእሾህ አጥር፣ ሁለቱም አንድ ናቸው"

- ሜንት ዎሻ አመዱላስ፣ ለሶ ሞኦዮ
  Meent woshsha amadulas, laso moo'oóyyo
  "ሴት ወሬ ከያዘች፣ ኊላዋን አታዩም"

- ሜንትች ዳኖምና፣ አዳዕም ሲኬችና፣ እሆዮ
  Meentichchi daannoomina, adaa'mmii sikkechchina ihooyyo
  "የሴት ዳኝነትና፣ የቁልቋል ምርኩዝነት ሩቅ አያስኬዱም"

*ሊ ስለህጻናት የሚነገሩ አሉታዊ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣*

- ኦሲ ቀመሪ፣ ዎኦ አጉኮክ
  Oosii qamarii, wo'o agookkok
  "ልጅና ጦጣ፣ የሚጠጣው ውሃን ነው"

- ኦሲኔ አጋኮ ሽፍ፣ እዮዮ
  Oosiinne aagakko'i shif, iyyooyyo
  "ከልጅ ጋር የገቡት መሸሽጊያ/መደበቂያ፣ አይዝም"

- ኦሲ ኢቴ ዮዮ፤ ኦሪ ግቤ ዮዮ
  Oosii itee yooyyoo, orii gibee yooyyo
  "ልጅ ብላ አይልም፤ ጦርነት ሽሽ አይልም"

- ኦሲኔ ዳያንች፣ ለሳንች በጠንቻ
  Oosiinne daayyanchi, lasaanchi baxxanchcha
  "ከልጅ ጋር መብላት፣ መጨረሻዉ መቀራመት ነው"

## 3. በባህሉ የሚወደሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

### *ሀ. እውነተኛ መሆንን የሚያበረታቱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣*

- *ሀንቃ ወጨከኣ፣ ሂሙ ቤዮኔ ገርማ*
  Hanqa wocakka'a, hiimubeyyonne garimma
  "እውነትን ተናግረው፣ የመሸበት ማደር"

- *ሀንቅ ዋአኔ ፣ባጢል ሀቡሰኔ*
  Hanq Waa'ane, baaxiil habusane
  "እውነት የእግዚአብሄር ነው፤ ሀጢአት የጂኒ ነው"

- *ሀንቅ ዋዕ ቤቶ*
  Hanq, Waa'i beeto
  "እውነት፣ የእግዚአብሄር ልጅ ነው"

- *ሀንቅነዕ ሶደን፣ ቦሎሉኩያ ዋሮኮ*
  Hanqina'ii soodannii, bololukkuuyya waarookko
  "እውነትና ንጋት፣ እየደመቀ ይመጣል"

### *ለ. ትዕግስተኛ መሆንን የሚያበረታቱ ምሳሌያዊ አነገጋገሮች፣*

- ሌሁ ቤኤክ፣ ለሞም አፎኮ
  Lehu bee'ek, lamom afookko
  "ያልሞተ፣ ሁለቱንም ይደርሳል"

- *መንኔ ገሬና፣ ዊሽች መን ጭሮ እቶኮ*
  Manninne gareena, wishichchi mann ciro itookko
  "ከሰው ጋር ሲኖር፣ ውሻ የሰውን አይነምድር ይበላል"

- ዱብ እሀኮዕኔ፣ *ዶም* እሀከሞዮ
  Dubbi ihakko o'nne, doom ihakkamoyyo
  "ቁጥቋጦ ሳይሆኑ፣ ጫካ አይሆኑም"





- *መካ አፈኬቤኤ፣ ምግሎኦ እተከሞ*
  Makka afakkeebe'e, migllo'o itakkamo
  "*መልካም ቀን እስኪመጣ፣ምግሎ(ጎመን መሳይ ሳር) ይበላል*"

### *ሐ. መተጋገዝን የሚያሳዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣*

- እፈዕል ቁት፣ አንግ ቁትና ዱቅሶኮ
  Afa'i quut, ang quutina duugisookko
  "ጀርባ ጉባጣ፣ ለእጅ ጉባጣ ያጉርሳል"

- አንጋ አበል፣ ሱም አበልና ዱቅሶኮ
  Anqa abballi, suum abballina duuqisookko
  "እጀ ለምጻም ለአፈ ለምጻም ያጎርሳል"

## 4. ሌሎች ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ከዚህ ቀጥለው የቀረቡት ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ራሳቸውን የቻሉና ባንድ ጐራ ለመመደብ የማያመቹ፣ በየራሳቸው አውድ የሚነገሩ ናቸው።

*ለምሳሌ፣*

የሚጠበቅበትን ሀላፊነት ያልተወጣንና የማይረባ ቦታ የተገኘን ሰው ሰመግለጽ፦

- ደሞና ኤበኮ አምቡል፣ *ሙዴኡኮ*
  Damona eebakko ambul, mude'ukko
  "እንዲያጠቃ ያመጡት በግ፣ ራሱ ጠባ"

ሰውን ከተገቢው በላይ አትመን ለማለት፦

- ሄሬች አሬ አመዕንታ፣ አሮእና ሱጦ አግሶኦ
  Heẹreechchi are amma'nita'a, aro'ina suuxo agisso'o
  "የዋርሳዋን ሚስት ተማምና፣ ለባሏ ኮሶ አጠጣች"

ችግር ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ መጠንቀቅን አስመልክቶ፡-

- ኡዊ ዋሩካሬ፣ እንቅ ኤጌዶዮ
  Uwwi waarukaare, inqi egedooyyo
  "ትውከት ከመጣ፣ ጥርስ አያግድም"

የነገር ፍጻሜ ከጅማሬ ይልቃል ለማለት፡-

- መር ጋዶ ብትቴ፣ ዋዕል ጋዶ ብሬ
  Mar gaado bittitte, waa'll gaado bire
  "የሚሄድን ጦር አታሞግስ፣ ተመላሹን እንጂ"

ብልህ አይበቀልም ለማለት፡-

- ባል ጦጳኮክ ፈረሾ፣ ባዶ ህጐኮክ ለች መንቾ
  Baalle xophookkok farashsho, baado higookkok lachchi mancho
  "ፈረስ ገደል ይዘላል፣ ብልህ በቀል ይተዋል"

የራስ ያልሆነ ነገር ላይ ልብን ስለ አለመጣል፡-

- መን ሉቺ መተ ሀቅ ዌያኪ፣ ኡሼጥሶዮ
  Mann luchchii mat haqqi weyyakkii, usheexxisooyyo
  "የሰው ንብረት እና ነጠላ ጋቢ፣ አያሳርፍም"

ሰውን በምላስ (በንግግር) ሳይሆን በተግባር እርዳው ለማለት፡-

- ጡዳ ኡዎ ቤዕ ኦለክች፣ ምኔ ሀራስታ በጤ ዮኮ
  Xuda uwwu bee'i ollakkichchi, mine haraasitta baxee yookko
  "አንድ ሀረግ የማይሰጥ ጐረቤት፣ ቤትህን አስፍተህ ስራው ይላል"





ወሬ የማውራትን ረብ የለሽነትና ጉዳት ለማሳየት፡-

- አቶራች ሎበከት፣ አሮዕኔ ቀሮ ፍሶኮ
  Atoorachchi lobakat, aro'inne qaro fisookko
  "የተንዛዛ ወሬ፣ ከባል ጋር ያለዉን ዝምድና ያጋልጣል"

የራስ ያልሆን ነገር አትፈልግ ለማለት፡-

- መን ሉዋንእ ባሌ፣ ዳጳኩኡያቴ ህገከሞክ
  Manni luwwanai baallee, daaphpha'akkuuyyatte higakkamok
  "የሰውን ንብረትና ገደል፣ እያዩ ያልፉታል"

ለአደራ ታማኝ መሆን ወይም ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባ ለማስገንዘብ፡-

- ሀደራ እለጌኔ፣ ቀቾ አፈሬኔ
  Hadaraa illagenne, qachchoo afareen
  "አደራን ከፊት፣ ልጅን ከጀርባ"

- ኤጌራንች ቀዊ፣ እስም ገማንቾ
  Egeraanch qawwi, isim gamaanchcho
  "የእረኛ ሞኝ፣ ራሱ ሌባ ነው"

ደሃ ጥበብን ቢናገርም አይደመጥም ለማለት፡-

- ቡጥች ቆሮም፣ ብቄ ቤዶኮ
  Buxxichchi qooroom, biqe beeddookko
  "የድሀ እውቀት /ጥበብ/፣ ሳይገልጠው ያልቅበታል"

ችግር/ጭንቅ/ ውስጥ የገባ ሰው የሚያደርገውን አያውቅም ለማለት፡-

- በቁች ብኡኮክ፣ ኮራዕን ዎሮኔ አንጋ አግሶኮ
  Baquchchi bi'ukkok, kooraa'n woronne anga aagisookko
  "በቅሎ የጠፋበት፣ ኮራና[108] ውስጥ እጁን ይከታል"

[108] ኮራና፣ በሀዲያ ባህል ከሸክላ የተሰራ በጣም አነስተኛ የቅቤ ማንጠሪያ እቃ ነዉ፡፡

ወረኛ ስለራሱ አያውቅም ለማለት፡-

- ያከሞክ፣ ያና ኢታላ
  Yakkamoki, yanna üttaalla
  "የሚባልበት፣ ማለትን ይወዳል"

ስአንድ ጥፋት ሌላውን አስተማሪ ቅጣት መስጠትን በሚመለከት፡-

- ሉካንቾ ቢብሰኬና፣ ፈረሻንቾ ሆለከሞ
  Lokkaancho biibisakkeena, farashshaancho hollakkamo
  "እግረኛውን ለማስበርገግ፣ ፈረሰኛውን ያባርሩታል"

አንድ ወላጅ ልጆቹ አስተማሪ ኑሮ መኖር እንደሚገባዉ እና ያንን ምሳሌነት የሌሰን ኑሮ የሚኖር ከሆነ ልጅ ከወላጅ የከፋ ኑሮ እንዲኖር እንደሚያደርገው ለማስገንዘብ፡-

- ኢያከአ ገሜአኮአክ፣ ድላ ገሜኦኮ
  Iyyakka'a game'akkok, dilla game'ooko
  "አዝለው የሰረቁት፣ ወርዶ ይሰርቃል"

ሀላፊነት የማይሰማውን ባል ስመንቀፍ ፡-

- አሮዕ ጆር፣ ገለዕ ኢቀሞሃሬ ኦሰሮኮ
  Aro'i jor, gala'i iiqamoohaare osarookko
  "የማይረባ ባል፣ ምጣድ ሲሰበር ይስቃል"

አንድን ስራ (የራስን ስራ) ለመስራት ሌላዉን መጠበቅ አያስፈልግም ለማለት፡-

- አንችችኮ ከዶኔ፣ ባሌዕ ከዶዮ
  Annichchi kado'nne, baale'i kadooyyo
  "በሰቤቱ ሳይደንስ፣ ሳባው አይደንስም"

- ጀቦ ኩረኮዕኔ ቀራር ሲደሞዮ
  Jabbo kurakko'nne, qararaari sidamooyyo
  "በሽታን ሳይነግሩ፣ መድኃኒት አይገኝም"





ስራፈት ዋጋ ቢስ ተግባርን ይፈጽማል ለማለት፡-

- በጥ ቤኢት፣ ቡአ ሙቶአ
  Baxi bee'et, bu'o muto'o
  "ስራ የፈታች፣ ቡላ ትከትፋለች"

ትጋትን ለማወደስ፡-

- ሶድና ይተሞቴ፣ ሶደራሮ ፍተሞ
  Soodinaa yitamote, soodaraaro fittamo
  "ለነገ የምታስብ፣ ማልዳ ትወጣለች"

ስስታም አትሁን ለማለት፡-

- ኦደዕ ቅቶዕኔ፣ ጪኢ ቅቱኮ
  Oda'i qitoo'n, cii qitukko
  "ሾላው ሳይሰለት፣ ወፍ ለሰተ"

## 6.5. ሄስ ሄሳ ቀሬ፤ የሀዲይሳ እንቆቅልሽ

*ሄስ ሄሳ ቀሬ /Hees beessa qard/* (እንቆቅልሽ)፣ በጥያቄና መልስ ቅርጽ የሚከወን ሲሆን አላማው ህጻናት ጊዜ ለማሳለፊያነት ብለው የሚያደርጉት ጨዋታ ነው፡፡ ይህም ህጻናት አካባቢያቸውን በሚገባ እንዲያዉቁ፣ እንዲመራመሩ፣ የማሰብና የፈጠራ ችሎታቸው እንዲያድግ የማድረግ ፋይዳ ያለው ቃላዊ ጨዋታ ነው፡፡ በመሆኑም ጨዋታው ከአዝናኝነቱ በዘለለ ህጻናት ተፈጥሮንና አካባቢያቸውን እንዲለዩ የሚያደርግ እና አእምሮን የሚያሰላ በመሆኑ ትምህርታዊ ፋይዳው /instructional siginificance/ የላቀ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በልጆች የቋንቋ ወይም የቃላት እድገት ላይም ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

ሄስ ሄሳ ቀሬ፣ በባህሉ የሚቀርብበት ስርአት አለው፡፡ ክዋኔውም የጠያቂና የመላሽ ምልልስን ወይም ጥምረትን ይጠይቃል፡፡ አንድ ጠያቂ፣ የጠየቀውን መላሹ መመለስ ቢሳነው፣ትክክለኛዉን መልስ ከመንገሩ በፊት አገር ስጠኝ

ብሎ ሲጠይቀዉ ተጠያቂዉ፣ ለጠያቂው በቃሉ ብቻ መሬት ይሰጠዋል። ተጠያቂው በተደጋጋሚ መልሱን ባይመልስ ጠያቂው መሬቱን ተቀብሎ ብቻ አያቆምም፤ ተሸናፊው ላይ የስድብ ናዳ ያወርድበታል። ይህ ስድብ በሀዲይሳ *ዱርበሻ* (Duurbasha) በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ በአቀራረቡ አብዛኛውን ጊዜ ግጥማዊ ቅርጽን ይከተላል። በዚህም ምክንያት አቀራረቡ ጆሮገብ ወይም የሚጥም ነው። *የሄስ ሄሳ ቀሬን* ክዋኔ በሚመለከት ቀጣዩን ምልልስ ይመስከቷል።

| *የሀዲይሳ ምልልስ* | *የአማርኛ ቀጥተኛ ፍች* |
|---|---|
| *ጠያቂ:* ሄስ ሄሳ ቀሬ[109]<br>Heess heessa qare | "ተረት ተረትን ይዉሰድ" |
| *መላሽ:* ሀቅ ኤሬራ ቀሬ<br>Haqq ereera qare | "እንጨት ኤሬራ[110] ይዉሰድ" |
| *ጠያቂ:* እሲ እሰቃንቺ ሆጌ<br>Issii issaqaanchii hooge | "ጠያቂና መላሽ ይሸናነፉ" |
| *መላሽ:* ኤያ ሆጌ፤ ከባ እሰቂ<br>Eyya hooge ; kaba issaqqe | "እዎን ይሸነፍ፤ አሁን ጀምር" |
| *ጠያቂ:* ሰንዶኦ ያኮ ፌለክቾ<br>Sando'oo yakko fellakkichcho | "ለንዶ የተበላችውን ፍየል" |
| ሰሳ አጵሰከማሬ<br>Sasa aphphisakkamaare | "ሶስቱ ሲመቷት" |
| ሰዴንተዬ ቀተሞ<br>Sadeentayye qatamo | "ሰማኒያ ትወልዳለች" |
| *መላሽ:* ቦቆላ<br>Boqqola | "በቆሎ" |

*[109]* *ሄስ ሄሳ ቀሬ* የሚለዉ በሀዲይሳ የእንቆቅልሽ ጨዋታ ማስጀመሪያ አነጋገር ነዉ፤ ይህም በአማርኛ 'ተረት ተረት' እንደማለት ነዉ።

*[110]* *ኤሬራ፣* በሀዲያ ባህል በሴቶች ከቆዳ የተሰራ ቀሚስ /ለበሳ/ /labasa/ እና ወጭት ላይ የሚደረግ ጌጥ ሲሆን መልኩ ነጭና ጠንካራ ሆኖ ቀጫጭን መስመሮች ያለዉ ነገር ነዉ።





| | |
|---|---|
| *ጠያቂ:* ለቅቶዮ ኡላ ኡዌ<br>Laqqittoyyo uulla uwwe | "አላወቅክም፤ አገር ስጠኝ" |
| *መላሽ:* ጊምብቾ ኡዋሞ<br>Gimbichcho uwwammo | "ጊምቢቾ ሰጥቻለሁ" |
| *ጠያቂ:* እቱሞ እታሩሞ[111]<br>Itummo itaarummo | "በለሁ በለሁኝ" |
| አሜች ኩኣሰ ክ አቆኔ<br>Ameechch ku'aasa ki aqonne | "የአሮጊትን ሽንት ባንተ አፍ" |
| አድች ቂንጤራ እ አቆኔ<br>Addichchi qenxeera I aqonne | "የግደር እንገር በእኔ አፍ" |
| ዋሪ ቀቅኔ<br>waar'a qaqinne | "በጥሩ አርጩሜ" |
| ወዳኖኔ<br>wodanonne | "በልብህ ላይ" |
| አላች ብጭኔ<br>Allaachch biccinne | "በእረኛ በትር" |
| አፈሬኔ<br>Afarenne | "ጀርባህ ላይ" |
| አት ዊሽች ቆንጦለኔ<br>At wishichch qonxolanne | "አንተ በዉሻ ድንክ ላይ" |
| ሳዕልታ ኤጌሬ ይቶቶ<br>Saa'llitta egere yitootto | "ጋልበህ ጠብቀኝ ትላለህ" |
| አኒ ዊጤእ ፈረሸኔ ሳዕላ<br>Anii wiixxe'i farashshonne saa'llaa | "እኔ እረጅም ፈረስ ላይ ጋልቤ" |
| ሆቅ--- ሆቅ ዮሞ<br>Hoq hoq yoommo | "ሆቅ---ሆቅ እላለሁ" |
| *መላሽ:* ከባ እሰቂ[112]<br>Kaba issaqqe | "አሁን ጀምር" |

[111] ይህ *ዱርበሻ* ወይም በተሸናፊዉ ላይ የስድብ ናዳ ማዉረድ የሚጀመርበት ደረጃ ነዉ። አጀማመሩም ዱርበሽ- ዱርበሽ-ዱርበሽ ብሎ ሶስቴ በመደጋገም ነዉ።

[112] መላሽ ስድቡን ከሰማ በሁዋላ እንደገና ጫዋታዉን ለማስጀመር *ከባ እሰቂ* /አሁን ጀምር/ በማለት ይጋብዛል።

ጠያቂ፡ አበዕ ሄመድ — "የአባባ ጥቋቁር"
Abba'i heemadd
ኡል ቱንሶ በዶዮ — "ጨለማን አይፈራም"
Uull tunso baddooyyo
መላሽ፡ ዌሳ — "እንሰት"
Weesa

በጠያቂና በመላሽ መካከል የሚከናወነው እንቆቅልሽ በዚሁ መልክ የሚቀጥል ሲሆን፣ የጠያቂና የተጠያቂው ሚና ምላሽ ሲመለስ ይፈራረቃል። በመካከል ለሚኖረዉ ሽግግርም እሰቋ /ጠይቀኝ/ በማለት አንዱ ሌላዉን ይጋብዛል። ከዚህ በመቀጠል በባህሉ የተለያዩ ጉዳዮችን ከሚዳስሱ እንቆቅልሾች መካከል የተወሰኑት እንደተጨማሪ ምሳሌ ቀርበዋል።

| ሄሰ ሄሳ ቀሬ፣ /እንቆቅልሽ/ | የአማርኛ ቀጥተኛ ፍች |
|---|---|
| አባ ቢረኔ ኦንት ግራራ<br>Abba'i biranne onti giraara | "በአባ ሜዳ አምስት ግራሮች" |
| መጣራ/maxxaara/ | "ጣት" |
| አማጥ ሀልች እይ ገሩኮ<br>Amaaxxi hallichchi iyyi garukko | "የጠገበች አህያ ክንሽክሟ አደረች" |
| አረኣ /Ara'a/ | "አልጋ" |
| አባዕ በገድ ኡሉዕማ ጐጂ<br>Abba'i bagad, ullu'mma gojji | "የአባባ ጦር እደጃፍ ላይ ግትር" |
| ሱማ /summa/፣ አገና /aganna/ | "ስም፣ ታሪክ" |
| አመክ ጆራ፣ ኦስ ሀኔኔ ሹሜሎኦ<br>Amak jora, oos harenne Shume'llo'o | "የእናት ክፋ በልጆቿ ላይ ሸናች" |
| ጀበና /jabanaa/ሲና /siina/ | "ጀበና" እና "ሲኒ" |





| | |
|---|---|
| አገከም ቤዕ ዎኦ<br>Agakkam bee'i wo'o | "የማይጠጣ ውሃ" |
| እንዲዳ /indiida/ | "እንባ" |
| አመደከም ቤዕ ጡዳ<br>Amadakkam bee'i xuda | "የማይጨበጥ ሀረግ" |
| ሀመሽቾ /hamashshicho/ | "እባብ" |
| አግሳ ፍሶ ቤዕ ጐጫ<br>Aagisaa fissoo bee'i gooca | "አስገብቶ የማያስወጣ በር" |
| መጬ /mace/ | "ጆሮ" |
| ባዱለኔ ለምና ጐብ<br>Baadullanne lamina gobi | "ጥገት መሬት ላይ ለሁለት ጉብ" |
| አኑና /anuuna/ | "ጡት" |
| ቦቅሎክ ቤትች ቢራ ወዕም ለሮ አላሮኮ<br>Boqqi lokki beetichchi biira wo'mmi laro allaarookko | "እግረ-ሽፋፋ ልጅ፣ ሜዳ ሙሉ ከብት ያግዳል" |
| ሙቁሬዳ /Muqureeda/ | "መቁያ" |
| ዱዕን ገቦኔ ለም ጐጭ ምኔ<br>Duu'n gabonne lam gooc mine | "ከተራራው ጥግ ባለሁለት በር ቤት" |
| ሰኔ /sane/ | "አፍንጫ" |
| ኢቅዶ ካ እዶ ክሮ ኡሳ<br>Eqidoo ka idoo, karoo usa | "ይኼኛውንና ያኛውን ማዶ የሚያስር ገመድ" |
| ድሪሮ /Diriiro/ | "እንቅልፍ" |
| ፊታ ግግሮቤ ሉቾ<br>Fiitaa giggiroobee luchcho | "እብቦ የማይረግፍ ነገር" |
| አቦኦ /Abo'o/ | "ሽበት" |

| | |
|---|---|
| እዩም ኦስ ሁንድም ሆሮሮ ጉዶ | "ወንድሞቼ ሁሉ ባለእኩል |
| Iyyummoos hundim, horroro gudo | ቁመት ናቸው" |
| ገውጄኤ/ሜጤቀና | "ጉልቻ" |
| (/gawje'e/mexeqanna/) | |
| ለም አባይ ሆሮር ጉዶ | "ሁለት ወንድማማች |
| Lam abbaayyi horoor gudo | ቁመታቸው እኩል" |
| ቡዶ/ ሃለንጣ/ Buudo/hallanxa | "ቀንድ /የእህያ ጡት/" |
| መራ መራ ሆጐ ቤዕ ሉቾ | "ሄዶ ሄዶ የማይደክም ነገር" |
| Maraa maraa, hoogoo bee'i wchcho | |
| ዎኦ /wo'o/ | ዉሃ |
| ሳዕልታ ፍተም እዳይቾ | "ተሳፍራ የምትሄድ ሙሽራ |
| ሹሩኩይ ጌሲሶ ሀማሞታ | እና እየጮኸ የሚያሯሩጥ |
| Saa'llita'a fittam idaayyichchoo, | አጃቢ." |
| shuurukkuuyyi geessiisoo hamaamootaa | |
| ሌሻ /leesha/ ዊላኖ /Wi'llaano/ | ራሳ እና ለቀስተኞች |
| ሻ ዲራሞ ቤኤክ | "ገሉ የማይፎክር" |
| Shaa diraamoo | |
| ዋኣ /Waa'a/ | "እግዚአብሄር" |

## 6.6. ለቦቶ /Labbooto/

ለቦቶ ፣ በሀዲያ ህዝብ ባህል የጊዜ ማሳለፊያ ከሆኑት ቃላዊ ጨዋታዎች አንዱ ነዉ። ለቦቶ የቃሉ ፍች «ትመስላሰህ» ወይም «ትመሲያሰሽ» የሚል ሲሆን ያንን ቃል የሰማ ታዳሚ ለጨዋታዉ እንደተጋበዘ ይገነዘባል። ጨዋታዉ መነሻ የሚያደርገዉ፣ ጨዋታዉ እየተደረገ ባለበት ባንድ ወቅት (ቅጽበት) በአካባቢዉ በሚታየዉ ነገር ወይም እቃ ሲሆን የዚያን ነገር አስቀያሚ መልክ ወይም ባህርይ ላንድ ሰዉ በማዉረስ ነዉ። በጨዋታዉ ማንኛዉም ነገር ቢባል በሌላዉ ወገን ጥላቻ ወይም ኩርፊያ አይኖርም። ለቦቶ፣ በሁለት ሰዎች





መካከል ተራ በተራ የሚደረግ ሲሆን፣ ተናጋሪዉ አካባቢዉን በጥልቀት ወዲያዉኑ በመመርመር ያንን ሁኔታ ገላጭ ስያሜ ይሰነዝራል። መላሹም ካልመጣለት ይለፈኝ በማለት ሊናገር ይችላል። ተጋባዡም ጨዋታዉን መቀጠል ሲፈልግ መሃ? (ምን?) ብሎ ይጠይቃል። ከዚያም የሚመስልበትን ነገር ይነግረዋል፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ሁለቱም ምልልሱን እየተለዋወጡ ቃላዊ ጨዋታዉ ይቀጥላል። ጨዋታዉም በፍጥነት አስቦ የመናገር ችሎታን የሚጠይቅ ነዉ። ለዚህም አስረጅ የሚሆኑ ምሳሌዎችን እናንሳ።

| ለቦቶ | ቀጥተኛ ፍችዉ |
|---|---|
| 1. ለቦቶ ------------------------------ | ትመስላሰህ? |
| Labootto | |
| መሃ? ------------------------------ | ምን? |
| Mahaa? | |
| ምላሽ:- ክንክነኮ ምቁ ------------------------------ | የተጋጠ |
| Kankanako'i miqe | አጥንት |
| 2. ለቦቶ ------------------------------ | ትመስላሰህ? |
| Labootto | |
| መሃ? ------------------------------ | ምን? |
| ምላሽ:- ኮረ ሆረኮኦ ቡላ ------------------------------ | ኮርቻ የተነሳበት |
| Koora hoorakko'i bula | በቅሎ |
| 3. ለቦቶ ------------------------------ | ትመስላሰህ? |
| Labootto | |
| መሃ? ------------------------------ | ምን? |
| ምላሽ:- ሾካ ገቱ ጉጉማ ------------------------------ | ነዶ የተረፈ ጉቶ |
| Shokkaa gatu guguma | |

4. ለቦቶ ---------------------------------------- ትመስላለህ?
Labootto
መሃ? ---------------------------------- ምን?
ምላሽ:- ኬፈና ሆጉ ሌሻ ------------------ ከፈን ያጣ ሬሳ
Keefana hoogu leesha

5. ለቦቶ ---------------------------------------- ትመስላለህ?
Labootto
መሃ? ---------------------------------- ምን?
ምላሽ:- ዊሽች እራንቾ ------------------ የዉሻ አራስ
Wishichch iraancho

6. ለቦቶ ---------------------------------------- ትመስላለህ
Labootto
መሃ? ---------------------------------- ምን?
ምላሽ:- ሁርባታ ግግስኮ ጨና ---------------- እህል የተራገፈበት ስልቻ
Hurbaata gigissakko'i cana

7. ለቦቶ ---------------------------------------- ትመስላለህ?
Labootto
መሃ? ---------------------------------- ምን?
ምላሽ:- እተኩኡያ አሴአኮ ኦሶ -------------- ሲበሉ የላኩትን ልጅ
Itakku'uuyya asse'akko'i ooso

8. ለቦቶ ---------------------------------------- ትመስላለህ?
Labootto
መሃ? ---------------------------------- ምን?
ምላሽ:- በካእል ኡሉማኔ ጠደኮ ቆቤኤ ---------የሀዘን ቤት ደጃፍ ላይ የተረሳ ቆብ
Bakaa'll ullummanne
xadakko'i qoobe'e





9. ለቦቶ ---------------------------------------- ትመስላለህ?
Labootto
መሃ? ---------------------------------- ምን?
ምላሽ:- ኦስ አንጊ ኡቡ አተካና --------------- ከልጅ እጅ ላይ የወደቀ አተካና
Oos angii ubu atakaana

10. ለቦቶ ---------------------------------------- ትመስላለህ?
Labootto
መሃ? ---------------------------------- ምን?
ምላሽ:- ኩሳ ግንደኮአ ዲሀ --------------- ኪዳን የተነሳበት ጎጆ
kusa gindakko'i diiha

## ማጠቃለያ

የሀዲያ ህዝብን ታሪክና ባህልን አቢይ ትኩረቱ ያደረገዉ ይህ መጽሀፍ በዉስጣዊ ይዘቱ፣ ህዝቡ ከጥንት እስከ ሀይለስላሴ ዘመን የተጓዘባቸዉን የህይወት ጉዞ ዱካና የዱካዉን አሻራ ለማሳየት ሞክሯል:: እንዲሁም የሀዲያ ህዝብ የህይወት ፍልስፍናዉ፣ እምነቱ፣ ወጉና አጠቃላይ የአኗኗር ስርአቱ የገለጻዉ አካል ነዉ::

በአንድ ህዝብ ባህላዊ ገጽታዎች ላይ፤ በአለምአቀፋዊነት (globalization)፣ በዘመናዊነት፣ በትምህርት፣ በሃይማኖት፣ በማህበረ-በህላዊና ኢኮኖሚያዊ ለዉጦች ምክንያት የቅርጽ ለዉጥ ሊከስትበት ይችላል:: የባህል ለዉጡ ፈጣንና ሰፊ ከሆነ ደግሞ ያንድን ብሄረሰብ ወይም ህዝብ መለያ ገጽታዎችን እስከመሸርሸር ብሎም እስከማጥፋት ሊደርስ ይችላል:: የዚህ መጽሀፍ ዋና ትኩረት በሆነዉ በሀዲያ ህዝብ ይህ ሁኔታ ሲታይ፣ በመረሳት ላይ ያሉ አንዳንድ ባህላዊ ገጽታዎች እንዳሉ ተስተዉሏል:: ለምሳሌ፣ ቀደም ሲል በተለያዩ ክዋኔዎች፣ ግጥሞችና ዜማዎች እጅግ ደማቅ የነበረዉ የለቅሶ ስነስርአት በአሁኑ ጊዜ እየጠፋ ያለ መሆኑ፣ በፊልምና በጽሁፍ ሰንዶ የማቆየትን ስራ አስቸኳይ ያደርገዋል:: በሌላ በኩል በሀዲያ ባገቡ ሴቶች ጥቅም ላይ ይዉል የነበረዉ የቋንቋ አጠቃቀም (በሉዊሻ) በአሁኑ ጊዜ በመጥፋት ጫፍ ላይ ያለ ባህላዊ ገጽታ ነዉ:: እንደዚሁም የሀዲያዎች ጥንታዊ ሃይማኖት (ፈንዳነኖ) በሌሎች ሃይማኖቶች ተጽዕኖ(ጫና) እየጠፋ ያለ በመሆኑ የተስፋፋ ስራ በአፋጣኝ መስራትን የሚፈልግ አካባቢ ነዉ::

በሌላ በኩል የስም አወጣጥ የአንድን ግለሰብ ወይም ብሄረሰብ ማንነት ገላጭ ቢሆንም በተለያዩ ዘመናት በሚከሰቱ ማህበረ-ፖለቲዊና ሃይማኖዊ ለዉጦች ምክንያት ለለዉጥ የተጋለጠ ነዉ:: በመሆኑም በሀዲያ በተለያዩ ትዉልዶች መካከል ያለዉ የስያሜ ገጽታን በንጽጽር መፈተሽ ቢቻል ማንነትን ከማቆየት አንጻር ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረዉ ይታመናል:: ከዚህም በመነሳት ይህ መፅሀፍ በትዉልድ መካካል ያለዉን ክፍተት በመሙላት የህዝቡ እየጠፉና እየተረሱ ያሉትን ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶች ነፍስ እንዲዘሩ ያግዛል ማለት ይቻላል::





## ዋቢ መጻህፍት


Alebachew Kemisso. 2009. "Change and Continuity in History Curriculum: an assessment of themes and perspectives in Ethiopian history courses of AAU (1961- 2006)". MA Thesis, Addis Ababa University.

Bahru Zewde. 2005. *A History of Modern Ethiopia 1855 – 1991.* Addis Ababa, Addis Ababa University Press.

Bahru Zewde and Siegfried Pausewang(eds). 2006. *Ethiopia, The Challenges of Democracy from Below.* United Printers, Addis Ababa, Ethiopia.

Bender, M.L. (ed.) 1976. *The Non Semitic Languages of Ethiopia.* East Lansing: Michigan State University.

Braukamper, Ulrich 2004. "Islamic History and Culture in Southern Ethiopia: collected essays Munster", LIT VERLAGE Munster.

________. and Tilahun Mishago.1999. *Praise and Teasing: narrative songs of the Hadiya in southern Ethiopia.* Germany: Frobenius Institute Frankfurt an-Maim.

________. 1980. Geschichte der hadiya sud- Athiopiens von den Anfangen bis zur revolution 1974. Steiner.

________. 1973. "The Correlation of Oral Traditions and Historical Records in Southern Ethiopia: a case study of Hadiya/Sidamo past." In: *Journal of Ethiopian Studies,* XI (2): pp 29- 62.

David Philipson. 1998. *Ancient Ethiopia, Aksum: its antecedents and successors.* London: British Museum Press.

Dirshaye Menberu. 2004. *Abagole Nunamo 1894 to 2001 Keleheywot Church Ethiopia.* Dictionary of African Christian Biography.

Donald N. Levine. 1993. *History of the Oromo of Ethiopia.* California: African Sun publishing.

Ergogie Tesfaye. 2008. "The Assessment of Abduction from Gender Perspective in Hadiyya Society: the case of Misha Woreda." M.A. Thesis. Addis Ababa University, Institute of Gender Studies.

Eike Haberland. 1964. *The influence of Christian Ethiopian Empire on the Southern Ethiopia.* In: second International conference of Ethiopian studies, Manchester.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Population Census Commission. 2008. *Summary and Statistical Report of the 2007 Population and Housing Census of Ethiopia.* Addis Ababa. Central Statistical Authority.

Gedeon Addise. 2008. "A Socio-economic and Cultural History of the Hadiyya (1941-1991)". M.A. Thesis. Addis Ababa University.

Hadiyya Zone Finance and Economic Development Coordination Main Department. 2006. *Hadiyya Zone Socio- economic Profile.* Addis Ababa: Nigid Matamiya Dirigit.

Haile Bubamo Arficio. 1975. "Some Notes on Traditional Hadiya Women." In: *Journal of Ethiopian Studies,*11(2): 131-154.

________.1972. "The Linguistic influence of Hadiya on North Ethiopia." Addis Ababa (unpubl. manuscr.).

________.1971. "Some Notes on the Fandaano Religion in Hadiyya (South-western Shawa)". Addis Ababa. Paper presented to the First Annual conference of the Historical Society of Ethiopia. (unpubl. manuscr.).

Haile Tephamo and Girma Suldo'lo(eds).2006. *Hadiyyi Suu'm Saga'l Usha* (The Oral Literature of the Hadiyya), Waachchamo(Hossana).

Kibamo Addise. 2007. "A Political History of Hadiya(1890-1941)". M.A. Thesis. Addis Ababa University.





Minala Aduga, 1997. "The role of the women during the campaign of Adwa, 1895/1896". In: international conference on the centenary of the Adwa victory. Addis Ababa, Institute of Ethiopian Studies.

Samuel Handamo. 2009. "Language Use in Shone Town: a sociolinguistic study". M.A. Thesis. Addis Ababa University.

Sergew Habla-Sellase. 1972. *Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270.* United Printers, Addis Ababa.

Taddesse Tamirat. 1972. *Church and State in Ethiopia 1270 – 1527.* Great Britain: oxford University Press.

Tilahun Amanuel. 2009. "Customary Criminal Justice System of the Hadiyya". BA Thesis, Addis Ababa University, Faculty of Law.

Ullendorff, E. 1966. *The Glorious Victorious of Amde Tsion, King of Ethiopia.* In: Bulletin of African and Oriental Studies, V. 29. London.

ሳጽሶ ጌ. ድሌቦ:: 1982:: *አብዮታዊ የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ በከምባታና ሀዲያ አዉራጃ ከ1971 እስከ 1975::* አዲስ አበባ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት::

መሃመድ ታደሰ:: 2009:: *ሓዞ፤ በምድረ ጉራጌ የገደባኖ፣ ጉታዘር፣ ወሰኔና አገምጃይ አጥቢያ ሕዝቦችን ያማከለ የፖለቲካ ታሪክ እስከ 1983 ዓ. ም.*

ባዩ ይማም:: 2008:: *የአማርኛ ሰዋሰዉ:: እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ.ማኀበር*

ተስፋዬ ሀቢሶ:: 1993:: "ከምባታ እና ሀዲያ፤ የአስተዳደር አካባቢ እና የብሄረሰቦች ታሪክ አንዳንድ ገጽታዎች":: አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ (ያልታተመ)::

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ:: 1993:: *የግራኝ አህመድ ወረራ::* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

________:: 1968:: *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ*: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

አመለወርቅ ሀንዳሞ:: 2006:: "ትዉፊታዊ ግጭት አፈታት ስርዓትና ተዉኔታዊ አላባዎቹ በሀዲያ ብሄረሰብ":: የዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል::

አበበች ኤርጎጎ:: 2008:: *የሀዲያ ባህላዊ ምግብ አዘገጃጀት*::

አየለ መሎሬ::1993::"የሀዲያ ህብረተሰብ የሰቅሶ ስነስርአት":: የዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል::

ኤርሲዶ አንታሴ:: 2006:: *የሀዲያ ብሄር የባህል መሰረታዊያን*:: ሆሳዕና፣ የሀዲያ ዞን ማስወቂያና ባህል መምሪያ::

ኤዳሞ ሄሬጎ ::1998:: "ሜጤ፤ በሊቢዶ/ ማረቆ ባህልና ታሪክ ላይ የተደረገ ጥናታዊ ጽሁፍ" (ያልታተመ)::


ጌታሁን ላምቤቦ:: 1987:: "የስም አወጣጥ በሀዲያ ብሄረሰብ":: የዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል::

ይልማ ዴሬሳ:: 2007:: *የኢትዮጵያ ታሪክ በአስራ ስድስተኛዉ ክፍለ ዘመን*: አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ





## አባሪ 1



________:: 1968:: *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ*: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

አመለወርቅ ሀንዳሞ:: 2006:: "ትዉፊታዊ ግጭት አፈታት ስርዓትና ተዉኔታዊ አላባዎቹ በሀዲያ ብሄረሰብ":: የዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል::

አበበች ኤርጎጎ:: 2008:: *የሀዲያ ባህላዊ ምግብ አዘገጃጀት*::

አየለ መሎሬ::1993::"የሀዲያ ህብረተሰብ የለቅሶ ስነስርአት":: የዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል::

ኤርሲዶ አንታሴ:: 2006:: *የሀዲያ ብሄር የባህል መሰረታዊያን*:: ሆሳዕና፣ የሀዲያ ዞን ማስወቂያና ባህል መምሪያ::

ኤዳሞ ሄሬጎ ::1998:: "ሜጤ፤ በሊቢዶ/ ማረቆ ባህልና ታሪክ ላይ የተደረገ ጥናታዊ ጽሁፍ" (ያልታተመ)::


ጌታሁን ላምቤቦ:: 1987:: "የስም አወጣጥ በሀዲያ ብሄረሰብ":: የዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል::

ይልማ ዴሬሳ:: 2007:: *የኢትዮጵያ ታሪክ በአስራ ስድስተኛዉ ክፍለ ዘመን*: አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ







## አባሪ 1



# አባሪ 2









# አባሪ 3

የሀዴያ ማህበረሰብ እ.ኤ.አ. በ 1500 ዓ.ም ገደማ



# አባሪ 4

የአገር ግዛት ሚኒስቴር

የሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ጥበቃ ።
MINISTRY OF INTERIOR
PUBLIC SECURITY DEPT.

አስቸኳይ

ምሥጢር

ቁጥር ፡ [illegible]

አዲስ ፡ አበባ ፡ 19.. ዓ.ም

የፖ ፡ ሣ ፡ ቁ ፡ / P. O. Box 35

የስልክ ፡ ቁ ፡ / Tel. No. 10855 / 10856

ለፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ መምሪያ
አዲስ አበባ ።

በከምባታ አውራጃ ገዛት ጉዳል የሚባለው ጎሣ የሰሜ [illegible] ለማኖሩት የሃዝባች ሥራ እኛሬ በሚባለው ቤት አማገዶት የ [illegible] የሰውና ልዩ ልዩ ወንጀል በመፈጸም ላይ ይገ... [illegible] የደረ [illegible] በዶል በሰረው በመዘርዘር [illegible] ሕዝቦች ነን የሚ [illegible] በር ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወ [illegible] ገዛት ሚኒስትር [illegible] ገልበው እንደደረሰ የተደረገውን እና [illegible] ።

እንደጉዳዩ ከበዶነት በ [illegible] በጥበቅ በመከ [illegible] ደረሰበት [illegible] ውጤት እን [illegible] እንጠበቃለን ።

ከሰላምታ ጋር ።

24-3-63

ለጠቅላይ ገዛት ጽ/ቤት
አዲስ አበባ ።

// ከማመልከቻው አራት ገጽ ገለበጥ ጋር //





ለክቡር ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት
ያገር ግዛት ሚኒስትር
አዲስ አበባ ።

ክቡር ሆይ

አመልካቾች በከምባታ አውራጃ ገዛት የምንገኝ የአማራ ክፍል አገር ተወላጆች የምናመለክተው ጉዳይ ስለደረሰብን ከፍተኛ ችገር ነው ።

1 / እኛ አመልካቾች አያቶቻችንና አባቶቻችን እኛም በዕድሜ በደረስን እስከሁን ለ [illegible] ጉሥ ነገሥታችንና ከበርና ለአገራችን ነፃነት በዐር ሜዳ በመዋል በወሰኛው ወረራ ዘመን በአርበኝነትና በስደተኝነት የሙተው ሙቶ ያለነው ደማችንን አፈሰናል በአውራ አስተዳደር በፖሊስና በጦር ሠራዊት በልዩ ልዩ የመንግሥት ሥራ ላይ ከፍተኛ አገልግሎት ሰጥተናል ስለደረገነው ገልጋሎት ለአያቶቻችን ለአባቶቻችን ለኛም እንደክፍ አገልግሎታችን አርስትም ሀነ ማደሪያ ተሰጥቶን እንገለገልበታለን ።

2 / ይሀን ሁሉ አገልግሎት የሰጠነው እንደክፍሉ አስተዳደር በደመወዝ ሜዳሆን በጊዜው ያስተዳደር ሁኔታ በተሰጠን አርስትና ማደሪያ በገበር እንጂ ሌላ አበል አልነበረንም ።

3 / በአዲሱ አስተዳደር ገርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለመላው ሕዝባቸው የእኩልነት መብት ሰጥተው ተጆ የገበር መሬት ሆኖ የሚገበርበት ለባለገሩ አስመርስት ሆኖ ለመንግሥት እንደ ገበር ተደረገ ይህ ከሆነለት በኋላ በአውራጃ በአውራጃው ገዛት ነዋሪ ሕዝብ ክፍ ነፍሶ እየተበደለ ከመገበረው ጉዳ በተር በአገሩ የከምባታና የጉዳሉ ጉዳዮች ስለሆኑ ነዌነት ሰው ሁሉ ስለሆነ ልጆቻቸው ከልጆቻችን ጋር ዘቤና ምን ትምህርት ስለተሰተሩ በዙዎች የጉዳል ተወላጆች በአውራጃው ገዛት በትምህርት ቤት በገቡ የውጭ አገር ሰዎች ሚሲዮኖች አ [illegible] ተረዳ በብዛት በሕከምና ሥራ ላይ ስለሚገኙ በአማራው ሕዝብ ላይ በተጻፈው አስተዳደር ገበር ና መልክና በመሆን የነበረውን ጭ በማስታወስ ለመበቀል ሲሉ ሕመም ደርሰበቻው በሕክምና ስመረቻት በሌሎ በሚባለው ተበሉ በሙሉዮና ዉና ዳቢያ የሚኖኙትን የአማራ ጉዳዮች በክነና በልዩ ልዩ ተታሚ መዶነት በሊታወቀ ዘዴ ሕይወታችን እንዲያው የተደረጉ ወንዶቻችን በርከት ያሉ ናቸው

4 / የወሰተ ዘዴ ተንኮል እንበክቸው የአማራውን ጉዳ እስከ መጨረሻው ከአውራጃው ገዛት በልዩ ልዩ ምክንያት ለማስወጣትና በአያት በአባቶና በራሱ ደም ያገኘውን አርስትና ማደሪያ ለማስለቀቅ በመሬት የሰረረ ዉበና ጉዳል የተባለው ጉዳ በሙሉ በመሸሽ በአደጋ አማ ራው ሰከበ ምክር እንዲያመሰክርለት አማራው ሰከበ በንብት በምስክርነት የሚቀርበው ጉ ዳል እንደመሰከርበት አማራ የሆነ ሰው ቢመት ጉዳል እንዲያተበር የርስት እና... [illegible] ወው በየጊዜው መዳስ እየተደረገ በከምባታ አውራጃ በለነው የአማራው ክፍል ጉዳዮች ላይ የደረሰብን በደል የሰው በተለይም በአውራጃው ገዛት በመንግሥቱ ሥራ ስዉ [illegible] የ ማራ ጉዳዮች ከአገር ለማስወጣት የጉዳሉ [illegible] ብቻ በሥራ ላይ እንዲያደርጉ [illegible]
[illegible] ጉዳ የሆነውን የመንግሥት ሠራተኛ የጉ

- 2 -

እንዲያውም የሰማረውን ንዋ በክስና በልዩ ልዩ ምክንያት ከአውራኛው ገዛት ለማስወጣት በአውራኛው ገዛት በቀኛ/ ሥዩም አኖሬ ሰብሳቢነት የጉዲላ ብላቶችና ደገሬ ሽማግሌዎች በየጊዜው በመሰብሰብ ገንዘብ በማዋጣት አዲስ አበባ እየመው ለንጉሱ ነገሬ ለልገበቸው ሰዎች በማስረዳት ሃሣባቸው እንዲደርስላቸው በማድረግ ላይ ናቸው በዚሁ መሠረት አሁን በቀርቡ በአውራኛው ገዛት ያሉ የሰማረው ንዋ የሆኑ የነ ብት ሠራተኞች በሙሉ እንዲነሱ ከሸዋ በሹሙንቱ ጋር በመነጋገር እንዲዘዋወሩ አስደርገዋል፤ የሚተረት በአገዛዝና በና ብት ያሉት ቅጥሬቸው ከ10 ያላነሱ የአውሬ ንዋ የሆኑ የነፍጠኛ ልጆች ስለተሬ እነሱን ለማስነሳት የጉዲላች ሰብሳቢ ቀኛ/ ሥዩም አኖሬ በወር 3 ጊዜ ከከተማ አዲስ አበባ ይመላሱ በመመላለስ ጊዜ ስናያቸው በየጊዜው ለአውሮፓን ከ10 ያላነሰ መላት ከ20 ያላነሰ በሙክ ማርና ፍቤ ያጉርፉሉ ይህ ሁሉ እኛን የሰማረውን ንዋ ከከተማ አውራኛ ለማስወጣትና ከርስታችን ነቅለው ለማብረር መሆኑ በገለጽ ይታወቃል ።

6ኛ/ በሥሬ ምክንያት እንዲዘዋወሬ የተደረጉት የነ ብት ሠራተኞች ውስጥ ሁሮቱ የነፍጠኛ ልጆች በአውራኛው ገዛት የተወለዱ የአማሬ ንዋዎች ናቸው፤ እነኝህ ሠራተኞች እንዲዘዋወሬ ጉዲሎች በጣም የጨረቡትና የደከሙበት ምክንያት በዱቤ የጉዲላ ንዋ የያዙቸው መሬቶች በዘዛት ስላሉ መንግሥት እንዳይጠብቅባቸው ደብተው ለመጨቆፍና የሚያውቅ ሰው ከሌላ ሌገ ለሠገን አይችሉም በማለትና ወደሬትም ላለ የሚያሰቡ ደርጊት ቢኖር በውስጥ እየቲነታቸው ለነዓይበታተሉዋቸው ነው አሁን በከተማ አውራኛ የጉዲላ ንዋ በመንግሥት ሥራ ላይ ከ20 በላይ ይገኛሉ እነሱን ገን የሚከብቸው የለም ።

7/ በሥሬ ላይ ያሉት ጉዲሎች እንደመብዛታቸው እንዱ የአማሬ ንዋ በሰቀ በሠረቀ ወይምጠሰኛውን ከሰ ፍርድ ቢያስረክሙ በፍርድ ማስፈጸሚያው መሠረት ለአማሬው ትእዛዙን በሥልጣን ያሉ የጉዲላ ንዋዎች ለማስፈጸም አይችሉም ።

በዚሁ አጸማቸው መሠረት አጸሚአቸውን ሙሉ ለመንግሥታቸውና ለአገሬቸው ደክመው በርሻና ላይ ያሉ አዝዎንቶች ለአገልጋሉታቸው በተበዛቸው መሬት ላይ የሰፈረ ጪሰኞች ጉዲሎች ስለሆኑ አበል እየከለከሉዋቸው አቅም በማጣት የሚለምኑ በረሃብ የሞቱም ይገኛሉ ።

ይህ ሁሉ በደል ሲደርስ የቻልውና ወደሬትም የሚደርስብን በመንግሥት በኩል ስለዚህ ጉዳይ አርምጃ ካለመወሰዱም የጉዲሎች ሃሣብ አ.ሐ. በሚገኙ ባለሥልጣኖች ተደጋፊነት ስለገኘነው ነገር ገን ይህን ለመበቀል ደለነው ደግሬ ንዋዎች በየበኩላችን መበለክል እንደናደርገ ዐበ ተፈጥሮ ጸሃታ ቢሰጠን መንግሥትን ቀር እናሰኛለን፤ በማለት እስከሁን በትዕግሥት የቆተናል ።

8/ በትዕግሥት ማሰሬችን እንደፍርሃት ተቆጥር በዛሬ የሚያደርሱብን በደል አስአቸው በዬሩ ሆና በቀኛ/ ሥዩም አኖሬ ሰብሳቢነት በሙሉ በአውራኛው [illegible]
[illegible] ከምስቶች ብዙ ወር 6ዓ.ም ጠርተው አማሬ [illegible]
[illegible] ቃጭለነቸው ያስከበቀ አገር አዘዉ መጥቶ በሌርሰት ሆና ሰጠቀነን ቁጥ በደሉን የሰፍለደ መንግሥት እንደፈወበት ዉሊደገም ከ[illegible] በኋላ የገበር መሬት ነሺ ሰጠቁ በማደሪያና በርስት ያለው ጪኛ በአማርኛ አሁንም ይበቃ.

ለሌጭበለ ገልበጥ





3 —

በስዚህ እነኝህን ነጸ ለማውጣት እኛ እዚህ በመተባበር በየጊዜው በመሰብሰብ በመመከር ከአገር እንዲወጡ እናደርጋ ስለሰበሰቡኝ፤ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሲወጡን ሌሎች የሃሰት ምስክር ለማቆረት ነው በሰን መልስ እንሰጣለን በለውጢናገሬ ከምስቶች እኛ አማሬ ከከተማ ጉዲሎ በማለት በንዋ ልዩነት እንሰማማም ሁላችንም አንዱ ነን በዚህም ስብሰብ አንገኘም ብለው ከስብሰበው ሲነሱ ከጉዲሎች መከከል 1/ አቶ ዐደቶ ጋሬዳ 2/ አቶ ኢርቦሞ ታሪስ 3/ ነሬዝማች ሉሺ አበቀ 4/ ኛ/ ሰቢ ዜመቻ 5/ ነሬዝማች ቱሬት ብጋኙ ቀኛ/ በየነ በረና አቶ ጌታቸው ኃይሉ የኛዝማች ቱነ ጪሞ በበየ አቶ አርጋው ኃይለሚካኤል አቶ ሙበር ጪኔ እኛ በዚህ ነገር አንሰማማም በስብሰባም አንገኝም ስለዚሬውም ነንገርሀ እንተው ተወጣው በለው ተሰያዩ በዚህም ጊዜ በመንግሥት በኩል የሰበበሰውን ሁኔታ የተከተለ የለም ።

9/ ቀኛዝማች ሥዩም አኖሬ በዚህ የማይበቃሉቸው መሆኑ በመረዳት ጉዳዩም እንዳይገለበበቸው የሰበሰበውን ዓላማ በመለወጥ ከተማታና የጉዲላን ንዋ ለማጋጨት እኛ ጉዳሉ እየተዘበነ ልገወሬ አይገባም በታሪክ የጉዲላ ነገድ ሃደያ ነው የሚባለው ስለዚህ የአውራኛው ገዛት መጨረሻ ከከተማ መሆኑ ተርቶ የሃደያ አውራኛ ገዛት እንዲባል እናስደርግ ብለው ከሰረፉ በኋላ በዚሁ ተሬቃሚ ለዚሁ ጉዳይ ሃደያ የመባልን ስም ለማስ በሬደዮና በልዩ ልዩ ሁኔታ ለማስተዋወቅ ገንዘብ እንደሚአስፈርገው ከ$15.000 ብር ያላነሰ ገንዘብ ከሕዝብ ተሰብስበዋል፤ በዚህ ምክንያት ከከተማቶችና በጉዲላ ንዋዎች መካከል ከፍ ያለ የንዋ ልዩነት ሆና በወበ ላይ ይገኛሉ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በዩኒቨርሲቲና በክሎች የሚማሩና በልዩ ልዩ ሥራ ላይ የሚገኙ የጉዲላ ንዋዎች ጉዲሉ የመባል ስማቸውን ሃደያ ለማሰኘት በቀኛዝማች ሥዩም አኖሬ በአቶ ኃይሉ አርፍጨ በአቶ ገዛው ገብሬጊዮርጊስ በአቶ ኤርሚ ዓዓ በአቶ ከበደ ደርጨበ በተባሉና በሌሎች አማካይነት በየሣምንቱ ቅዳሜ በር ሃገህ ዛሬነው ትምህርት ቤት ውስጥ ከፍ ያለ ስብሰብ እያደረጉ በሚሰበሰቡትም ውስጥ አቶ ኃይሉ ዐሰደሚ ዝኤል የዩኒቨርስቲ መምህርና አቶ ኃይሉ አርፍጨ የተባሉ ሃደያ በመባል በኢትዮጵያ የሚጠሬው ንዋ ትልቅ ታሪክ ያለው የነገሥ ዘርነው ዘማንኛውም ንዋ ይበልጨል በኢትዮጵያ የሚገዛውም ንዋ ሃደያ ለመሆኑ የጀርመንና የእንግሊዝ ታሪክ ጸሐፊዎች ሺፈውታል እያሉ ከመሰብሰባቸውም ከሌረው አገር ቤት ሁረበ እየሄዱ ሕዝብ እየሰበሰቡ ሰብከው ተከታተይ አስተደረገበቸውም ይህን የመሰለ የዘር ልዩነት ማድረግ በሰሬው የማዉና የተሰማን ዓለማ የተከተለ ስለሆነ መንግሥት በብርቱ ሊያስብበት የሚገበ ነበርኛ ነገር ገን በሥነ ቸል እንደተባለ ስለልገበነ ማሰሰብ ገደ ሆነበን ይህን ሁሉ በመፍጠርና እንዲፈጠር ያደረገው ቀኛ/ ሥዩም አኖሬና በሲቢ በትምህርት ተሸሰለናል የሚሉ የጉዲላ ንዋዎች ሃሣብ ነው ቀኛ/ ሥዩም በወሰት ዘመን ለአገሬቸው ነጸነት በአርበኝነት የሚታገቱት ዘመድ መስሉ እቤቱ አስደሮ አምስተኝም አርበኞች እንደከበበ አርደ በመገደሉ ነጸነታችን ሲመለስ በበርር ራስ እደፍርበው ገዥነት እኙ ተይዞ ታሰር አ/ አዲስ አበባ ከመጠ በኋላ በሥሬት ተሰቀተ በኋላም ከቡር ደኛዝማች [illegible] ገዥ ሆነው ከምበታን ሲያስተዳድሩ ቀኛ/ ሥዩም የመሰለነት ሥራ በወይቀ ምት ሲተርልህ ሥራ ፈለገ አይገበህም በለው አዘውበት ሥራ ተከለከሉ ሲኖር ለጉዲላ ንዋ የአዘበ እንደረሱ ሆና በለተመረጠ ም ብት ከመጣ በኋላ የጀመረውን ሃሳብ ከነበ ለማድረስ [illegible] ሰት የለው ለጉዲላ ንዋ አርበት ተበተነ እያለ ከሕዝብ ጋር ሲሰራና ደበገበው በ52ዓ.ም [illegible] ከተረጋገጠበት በኋላ በ53ዓ.ም ያላገኙ ወዲያ ተለቀቀ እንደገናም ምርጫ ገብቶ እንደረሰ በመሆነ ከቀየ በኋላ ለ3ኛ ጊዜ ተወዳድሮ ተገኘሉ የከተማ ንዋዎች አውቀው ስላስመረጡት ከ[illegible]

- 4 -

ለወዱት በለሰው ወዳጅ ገዢት በምርጫ ቀልደት ሰው በመንግሥት ሥራ በወደተበት አውራጃ ሥራ አገ ባዝ በደሚ ትክዛዝ የተወ ነው ታሪፍ ሕዝቡና ሕዝቡን በማጋዘት ደም እንዲያረሰሰ ሆነ ተበሎ በክ ምበታ አውራጃ ገዢት የተመደበር ወረዳ ገዥ ሆኖ እንዲሠራ በመደረጉ ስለዚህ የተገለጸውን ሁኔታ ለመ ረዳም አስቻለውም

አሁን እኛ የምናመለከተው በከማሪው ጉዳያች ላይ ይህን ያህል በደል ሲደርስ በመን ግሥት የመንረስገውና ሲደረገ የሚገበው እርምጃ አስከሙን እንደሆነ በትግሥት አስከሁን ወበቀን ግመ ልበት ገደታችን ሆነ ከዚህ ትክሥታችን በኋላ የሚደበቀን ዕድል ምን እንደሆነ ማወቅ አልቻልነም።

ስለዚህ እኛ ትግሥት ደደረገነው መንግሥታችንና አገራችን በማመን የጋዛ ልዩነት ሣና ደርገ ነው ሆኖም ይህን በደላችንን መንግሥት ከተረዳልን የሕዝቡን ልዩነት የሚረዳን የኛ/ ሥዋ እኖሬ ስለሆነ አሁን ካለበት የወረዳ ገዢት እንዲነሣ 2ኛ ኳልሉ የወሀለ የጋዛ ሰው ሃደ እንደ ባል ሰበሰብ የሚያደርጉትን እንዲሄሉ እርምጃና ሃገሉ ወልደሚካኤል ከነበረ አበርቻቸው የተደር የደርጉ ስብሰባውን እንዲያደርው በከገር ቤት በከማሪው ሕዝብ ላይ ስለሚደረገበት በደል አንዱ አር ምኝ እንዲወሰድ እንዲያደርጉልንና ይህንኑ ለገርማድ ነገሥ ንግሥት እንዲያበሙልን በታላቅ ክመንት ይህ ከቤቶታችን እንዲያደርሰ አልርገናል ነገር ግን እኛ ለመልበቶች ለማችንን ገልፀን በዚህ ግመ ልበቻ ረርማችንን እንዲናገር በየስማችን ንዲቶች እየተከታተሉ በገበያ በመስበስና በመወሰር ከፍ ያለ በደል የሚያደርሱብን መሆኑን በማወቅ ነው።

ግልባጭ ፦

ላሕዝብ ጸጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት
ለፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ
አዲስ አበባ

ስለ ከበሬ ግልባጭ ፦





# አባሪ 5

ከከምባታ አውራጃ አብሮችን የሚሉ በማቸው ያለተገለጸበያች የሃዲያ ሕዝብ አሁረን አስተራችና ለማስጠቅ ከምባታን ለወዑን በመሰለና ላይ ወሆኑን በመዘርዘር ሬያ ቤትያ መግሬችን የሚታወስ ነው ። ተሬደመ የተባለው ወንጀል ወረዳም ከሰመሬሽመ መሰራያ ቤትያ በሚያደርገው መስታተል ለማረጋገጥ የሚችል ስለሆነ ይህንን ለመሥሪያ ቤትያ ትተን ለአቤቶታው መነሻ የሆኑት ነገሮች ምን እንደሆኑ በሚመለስን ለማበራሬት እንሞክራለን ።

1/ ያቦምባታ አውራጃ አበሮ ቅርብ ጊዜ ድረስ መንገዱ ያልተገባና ከአዲስ አበባ ጋር በተሳል የሚገናኝ በመሆኑ እንዲንዱ አገርና በበክሮ መርገን የሚያስበረ ቀቀማቸው መነሻትን ያጋቀ በለነበረ የመንገዱ ሥራ እንዲደናቀፍ በልዩ ልዩ ዘዴ የቀከረ እንደነበረ የታወቀ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ሊበ መንገዱ ወቀተለ እስተፋደረ ተበቀለት በሏ ዊ ኦር በማገኘቱ ዓይናቸውን ያወጣው ባለቀቁኝ የፈጠረ ባሬ ይመበሳል

2/ የነበ ማሥከርነት እንዲጠሬ ሕዝቡ ከበናፍርድ ቤት በማዘጋተር ሥራ እንዲበሬታና ሳንዳንዱ ከጉል ሰማደች ጋራ እንዲያበዛ ቀኛዝማች ሥዩም በዩሬ በሳበተማሬ ከቀቀማቸው ጋርየሚጋይ አዱራጉት መሆኑን ስለተገነዘበ በተጀመረው ወያሚ ሥራ ሕዝብ እንዲያወቀው ለማስናከረ ያሉት ይሆናል ።

3/ በኢንዋሽ ያ ሕዝብ እንዱነቱና አኩልነት የሚያሥኑ ጥቂቶች በያች የሚሠነዝሬት ከሰ ሁሉ ሽፍ በዱፍን የሚቀበሳቸው በሰሥልጣን ይኖራል በሚሉ ያለተጫረ ስሜት የተነበበ ይመስላል ።

4/ ባንሩ ተኛው በአውራጃው ከሚገኘ ሕዝብ በሰተ እልተኛ የሚሆነው የሐዲያ ሕዝብ በሌላ አውራጃያች ለሥዉሉ ተገቶትና በሰገ ሕበና ንሬጓ ጋዘተ እንደተደረገ ሁሉ የከምባታ አውራጃ <u>የሃዲያና የከምባታ አውራጃ ይበልለን ብሉ ሕዝብ ያመለከተው ም ከንደያ በማዱረን ባገሬ ዑበቀ በሰሥ የወ ፍ አሰመስሉ ሕዝቡን ለማበወት የተደረገ ነው ።</u>

ለከቡርነትዎ የምናመለከተው ከላይ የተጠቀሱት በገቸው ያልተገለጸ በያች ጋሰቀ ጋሰውን አያሠሬ ሕዝቡን እንዲያበጣብጡና ከሬ ምኞታቸውን በሥራ ከማገለፃቸው በሬት አስሬሳጊው ቀተቀ ር የከፍለያ መሥሪያ ቤት እንዲያደርጉቸው አያቦበበን ኢትዮጵያዊነታችን በሚያወዩቀን መሠረት በበሔራዊ ቀዋችን ጋር የሚጋዩ ነገር በከፍሰ እንደ እንዲያደርጉ ባለን አቋም ሁሉ የሚገቀ ር መሆኑን ለከቡር መሥሪያ ቤትዎ ለማረጋገጥ እንወዳለን ከተከበሩ ሁሉ ። ።

ኃይሉ ገብረ(ጽ)ክሊሰተ

ኃይሉ አርሬሞ

<u>ግልባጭ፣</u> ለክቡር ቢትወደደ ዘውዴ ገብረ ሕይወት የአገር ግዛት ሚኒስትር
ለክቡር ራስ መስፍን ስለሺ የሸዋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ

# አባሪ 6

<u>ግልባጭ</u>

ለክብር ሊቀሉኔል ተሰፋዬ ገዛው
የከምባታ አላባ ገዛት ፖሊስ አዛዥ
<u>ሆሳዕና ፡፡</u>

አመልካቾች የከምባታ አውራጃ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነታችን የምንከራ በቡተበብ ባይሆን በህብረተ ሰብ የምናምን በሥጋ ባይሆን በዘጋነታችን ደብ የምንበኘ ለክብርነትዎ የምናመለክተው በበርሃናዊ ለበናያ ተመለከተው ቁአንዳንዶች ባልተገሩና ባል ተመራረ ሰዎች አካምር ውስጥ ተቀርጸ ያለውን ለኢትዮጵ ያዊነታችን ጠንቅ የሚሆነውን አነጋገርና የጉሣ ዱምዋውን እንዲያጠፋልን በተሰረ እናመናለን ፡፡

<u>ክብር ሆይ ፣</u>

ጉዳዩ ከከምባታ አውራጃ ውስጥ የአውራጃውን ሕዝብ የሚያፍውቀ አንዱነቱንም የሚያናጋ የጉሣ አድግ በክብር ቀኛዝማች ሠዒም አናሬና በገበረ አባርቻቸው በአነ አቶ አበበ በሺር ወሬነት መጠንበሱ የሚያባዝን ሆና አገኘተናል ፡፡

በከምባታ አውራጃ ውስጥ የተለያዩ ጉሣዎች መኖራቸው የታወቀ ነው ፡፡ በተለይም ባሁኑ ጊዜ አስተዋዩና አርቆ ተመልካች ነገሥ ነገሥታችን ነርሻሪ ቀላማይ ጽሄለ ሥላቤ አህጉራችንን አፍሪያን አሰፍ ተርፍም በአክናሚው በማህበራዊ ኑሮ ዓለሙን አንዱ ለማድረግ በሚጥረበት ጊዜ በከምባታ አውራጃ ውስጥ የኢትዮጵያዊነትን ስሜት ለቆ በጉሣ የተሠረተ አድግ ለዛሬይቱ ኢትዮጵያ የማይስማማ መሆኑንና ለእንዲሁ ያለ ዓላማ ሥፍራም አለመኖሩን ክቡርነትዎ ያውቃል ፡፡

ቀኛዝማች ሠዒም አናሬ የደንጋና ቀንበር ወረዳ ገዥ ሥልጣናቸውን በመተማመን ባላታወቀ መንገድ መንደር ለመንደር እየዞሩ በሐዲየኛ እየተናገሩ በአውራጃው ውስጥ ያሉትን በአምስቱ ወረዳ የሚገኙትን ሐዲዮች እየሰበሰቡ በአውራጃው ውስጥ በሚገኙት ሥፍራዎች ላይ አንዲነበሱና ሐዲዮች ከጥንትም ባህልና ታሪክ አላቸው ከምባታ የተባለውን ጉሣ ዘሬያውን ከባኘሁ ነው ፡፡ ያሳኘሁ ስለዚህ አውራጃውንም የሐዲያ እናበኛለን ብቻ ሁሉም ነገር የሚሠራው በገንዘብ በለሆነ ገንዘብ በበሰበ በማለት የዚህን ከፍለ ባላ ባቶችና ቀንዱ የሆኑትን ሰዎች በጋቁ ሬት ከአምስት ጊዜ በላይ ሰበሰብ እንዳደረጉ የታወቀ ነው ፡፡

ደገምም ደንጋ ቀንበር ወረዳ ገዛት ና ከተማው ነዋሪ ቢሆን ቀኛዝማች ሠዒም ገን ሐዲዮችን ለማሰደበትና በዚሁ ደብ ብሎአቸው ገንዘብ እንዲሰበሰቡ ሐዲያ የተባለ ጉሣ የሚገኙበትን ብር የተባለውን ቀበሌ በሬዲዮ ቢያስ ታውቅ የደንጋ ቀንበር ወይም የበር ወረዳ ማለታቸው የሚታወስ ነው ፡፡ ገን የበር ወረዳ የሚባል በከምባታ አውራጃ ውስጥ ያልተሰመደና የማይገኝ መሆኑን ማንም ያውቃል ፡፡ ገን ቀኛዝማች ሠዒም ይህ የሚያደርጉ ሐዲያ ለተባለ ለሬባቸው ጉሣ ከኢትዮጵ ያዊነት ጋራ የሆነ ለአገራችን





—2—

የጦረነቱ ገዥ ቀኛዝማች ሠዒም የሕገ ወጡ አቶ አበበ በሺር ከነአባርቻቸው ጋር በሕገ ሬት ጥሬ እየመበሉ ነበረታቸው ያለው በባላገር ስለሆነ ሐዲዮችን እየበበ ሰቡ በንጉሥነና በሕገ በክል ለሚመጣ አኛ አለገላኘሁ እናንተ ገን በርቀበት በማለት የቃሬል ዱጋፍ እየበጡአቸው ከቀዲባ ጋጫሳ ወረዳ ጀርበና በደናቸ ከተባሉት ሥፍራዎች ሐዲያ የተባለ ጉሣ በአነርሱ ወሬነት የሚደረገው ሰበበባ መሆናቸው የአውራጃውን ሕዝብ በጣም አስቆጥቶታል የተደረጉትም ልዩ ልዩ ሰበበባዎች የመንግሥት ጋሥሬያ ቤት ያላ ቃቸው ናቸው የአድግ ሥራቸውም እንዳይታወቅባቸው ለመንግሥት ባለሥልጣኖች ሳባን ለማፍረት ነው የማነበበበው በማለት በሃብት ቃል ያበ ተባበሉሉ፡፡

ስለዚህ ክቡርነትዎን የምንለምነው የአውራጃውን ሕዝብ በሰላምና ጸጥታ ለመጠበቅ ከእግዚአብሔርና ከንጉሠ ነገሥቱ አደራ የተቀበሉ በለሆነ ይህ የተጀመረው አድግ ሥር ሰዶ ከሕዝብ ጋር የሚያበጣብጥ ከመሆኑ በፊት ልዩ ጊዶ ተጥሮ የነገሩን መነሻ አጥንተ አጥፊው ላይ ፍርዱ ሽንገ ሬት ቀርቦ እንዲቀጣና የከምባታ አውራጃ ሕዝብ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ተበምሶት ለአገራችን ዕድገትና ብልጽግና እንዲሠራ ያደርጉ ዘንዱ በማክበር እናመለክታለን ፡፡

ገልባጭ /—

1ኛ ለሸዋ ፖሊስ ጸ/ቤት
2ኛ/ ለጸጥታ ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ ፣</u>

### በሀዲይሳ የቀናት እና የወራት ስሞች

#### የሳምንቱ ቀናት ስሞች

1. ሰና/Sanna /:- ሰኞ
2. ማግሰና/Maagisanna /:- ማክሰኞ
3.ኦሮባ/Orooba/ ወይም ሀርጴኤ :- ረቡዕ/(በሌሞ ቀበልኛ/ዘዬ/)
4. ሀሙሳ/Hamusa/:- ሀሙስ
5. ሀርባ/Harba/ ወይም ጅማታ/Jimaata/(በሌሞ ቀበልኛ/ዘዬ/) :- አርብ
6. ሆፈአ/Hoffa'a/:- ቅዳሜ
7. አበአ/Abba'a/:- እሁድ

#### የወራት ስሞች

1. ሞሶሮኦ /Mosoro'o/:- መስከረም
2. ጥቅንታ /Xiqinta /:- ጥቅምት
3. ሀዳራ /Hidaara/:- ሀዳር
4. ጥሳሳ / Xisaasa/ወይም ከሎኦ /Kallo'o/:- ታህሳስ
5. ጥራ /Xirra/ ወይም ጥርሬ/Xirire/:- ጥር
6. ሰኰቲታ /Sakatiita/:- የካቲት
7. መጋቢታ /Magaabiita/:- መጋቢት
8. ሻሺጋ /Shaashiga/ ማዜኤ/Maaze'e/:- ሚያዚያ
9. ግልቦታ /Gilboota/:- ግንቦት
10. ሰኔኤ /Sane'e/:- ሰኔ
11. ሀምሌኤ / Hamile'e/:- ሀምሌ
12. ጦምናሴኤ / Xoominaase'e/
13. ቃቁሜኤ /Qaaqumme'e/:- ጳጉሜ

### የወቅቶች ስያሜ


| ፊቴ | ቢሌ | ቀራጦ | ሀገዬ |
|---|---|---|---|
| Fiitte | Bille | Qaraaxo | Hagayye |
| ጸደይ | በጋ | በልግ | ክረምት |

## የመረጃ ሰጪዎች ዝርዝር

| ስም |
|---|
| አባገዳ ሰጩቦ |
| ኢማም ጀማል |
| ዳኛ ዋሚሾ ሺፈራዉ |
| ወ/ሮ ዴሞ ሀዳ |
| አበጋዝ ሰ`ሶ ጠሰሞ |
| አቶ ጥላሁን ዱተሞ |
| ዳኛ ደጉ ሄልሶ |
| ዳኛ ዋቲሮ አበቦ |
| አበጋዝ ቲርካሶ |
| አቶ በየነ ላምቦሬ |
| ዳኛ አንሴ ጥሶሬ |
| ወ/ት አሰሚቱ አሰምቦ |
| ወ/ሮ አልማዝ ዳ`ሞ |
| አንጃንች ተሰማ ፎላ |
| ገደብች በቀሰ |
| ታደሰ ሽፈራዉ |
| አዝማች ደሳሰኝ ሎዳሞ |
| አቶ አስማየሁ ሊረንሶ |
| አቶ ኢያሱ መኬቦ |
| ደጃች ማቴዎስ ያዶሬ |
| ኢማም ደሴ |
| አቶ ቸርነት ኤርገኖ |
| አቶ ጴጥሮስ ዶጀሞ |
| ወ/ሮ አበበች ዲንዳሞ |
| ወ/ሮ አበበች ሆሲሶ |
| አቶ ዳኢሞ አበቦ |
| ዳኛ ጴጥሮስ ሀያዬ |
| አቶ ተሰፋዬ መኔቦ |
| ዳኛ ዋንኮሬ አንሰቦ |
| አቶ ኢጃጆ ሰንዶሬ |
| አበጋዝ ቲርካሶ አበሜ |
| አቦቼ ታኪሶ |
| ወ/ሮ ዳንኩላ ቀልቦሬ |
| አቶ ጡምደዶ ሽርጦሬ |
| ዳኛ ጤሙሮ ምጫሶ |
| አቶ ሳሙኤል በየነ |
| ገራድ ወ/ጊዮርጊስ ቂንጣሞ |
| ዳኛ አቦሴ ምልክሶ |
| አቶ ብርሃኑ ተሰፋዬ |
| አቶ አቦሴ ምልክሶ |
| አበጋዝ ሰገሰ ገፅኖሬ |
| አቶ ብርሃኑ ወልደጊዮርጊስ |
| አቶ አሰፋ ቡንጤ |
| አቶ ደሳሰኝ ዌጠ |
| አቶ ያዕቆብ በዛብህ |
| አቶ ታገሰ ኤረንጎ |
| አቶ አጫሞ ቦቄ |
| አምሳ አለቃ በቀለ ጊዴቦ |
| የተከበሩ ጌታቸዉ ሀይሌ |
| አቶ ሰለሞን ሰዩም |
| ወ/ሮ ሰዕዎ ጀከሞ |
| ወ/ሮ ጫፋሜ ባሻዉ |
| ፕ/ሮ በየነ ጴጥሮስ |
| አቶ ተመስገን አዳነ |
| አቶ ሀይሉ ኤራጎ |
| አቶ ኤርሰዶ አንተሴ |
| አቶ ጳዉሎስ ጫዕሚሶ |
| አቶ ፍራንስስ ማደሬ |
| አቶ ሙላቱ ተሰማ |
| ወ/ሮ ሽዋዬ ይስሶ |
| ወ/ሮ ዘነበች ኤርትሮ |
| ወ/ሮ ወርቅነሽ ዳዕሞ |
| ወ/ሮ ወርቅነሽ ሴርዶሎ |
| አቶ አየለ ሄሎሬ |
| ኮማንደር አድሴ |
| አቶ ተሰፋዬ ነጫ |
| አቶ ከበደ ሙሉጌታ |
| ዳኛ ጎዳና ሰምንቄ |
| ዳኛ በየነ ፊጤቦ |
| ዳኛ በየነ ላምቦ |



ቀኝ አዝማች ቂንጣሞ ሶቦቆ



አቶ ዳእም አበበ



ቀኝ አዝማች ጩፋሞ አምበሌ




አቶ ኤፍሬም አኮሼ



አቶ ኤርሣ ዳዳ




ገራድ ወ/ጊዮርጊስ ቂንጣሞ



ቀኝ አዝማች ስዩም አኖሬ



አቶ አበበ ቡሼሮ



የተከበሩ ጌታቸው ኃይሌ



ግራዝማች ኃይሌ ተፌሶ



ቀኝ አዝማች ሂርቦሬ አማዶ



አቶ አበራ ኃ/ጊዮርጊስ ወራቆ